* * *

ወ/ሮ አባይነሽ ያሰቡትን ቅድመ ዝግጅት ያጠናቀቁ ቢሆንም የፈሩቅ ሽታ በአካባቢው ሲገኝ አልቻሰም ። ፈሩቅን ሰማየት የነበራቸው ጉጉት በጣም ከፍተኛ ነበር ። ሆኖም ይህ ጉጉት ቀደም ሲል በፍቅር ዘመናቸው የነበረው ዓይነት ባለመሆኑ ሰዓመታት ሲያስፈራራቸው የነበረውን ሰው ለመገላገል መሻት ነበር ጉጉታቸው። በቤታቸው ውስጥ የፈሩቅ ሽርክና ያላቸውን ወንዶችና ሴቶች ሠራተኞች አባረዋል ። ቀደም ሲል ፈሩቅን በመፍራት ሸሽተዋቸው የነበሩ ወዳጆቻቸውን እራሳቸው ፈልገው ግንኙነቱን እንዲቀጥል አድርገዋል ። ከውጫዊ ለውጥ ሌላ በራሳቸው ላይም ውስጣዊ ለውጥ ተቀዳጅተዋል ። የድሮው ልክ የሌለው ፍርሀት ወሰን በሌለው ድፍረት ተለውጧል ።

ሲጠብቁት የነበረው ቀጠሮአቸው ጊዜው ደርሷል ። መሰናዶዋቸውን ሰማሰናዳት እጅግ ማልደው ነበር የተነሱት ። ያሬድና ተሾመ በቀጠሮው ሰዓት ሳሎን ተቀምጠዋል ። ወ/ሮ አባይነሽ በቤት ውስጥ ወዲያና ወዲህ ሽር ጉድ እያሉ የሚበላና የሚጠጣ ለእንግዶቹ ከማቅረብ ያለፈ ነገር ብቻቸውን ለማድረግ አልደፈሩም ። የነፍስ አባታቸው ያስፈልጓቸዋል ። ከቀጠሮ ሰዓት አንድ ሰዓት ያህል አሳልፈዋል ። ጭንቀት ቁጭ ብድግ አደረጋቸው ።

« ሂጂና አባን ምነው ሰዓቱ አልፏል ይምጡ እንጂ ብለሽ ጥሪያቸው ። ጎሽ ! እየጠበቅናቸው ነው » ሲሉ ካብትሽን ላኳት ። አባ ጊዜ ያጠፉ አይመስሉም ። ካብትሽን አስከትለው ከተፍ አሉ ። ወዲያው ሲደርሱ ሳሎን እንደገቡ ፣ « ትልቅ ይቅርታ ፤ ከቤተክርስትያን እንደገባሁ አንድ ዘመዴ የሆነች ሴት ቤት ውስጥ ስለቆየችኝ እሷን ሰማነጋገር ብዬ ነበር የዘገየሁት ። » ሲሉ ይቅርታ



ጠይቀው የተለመደ ሐይማኖታዊ ሠላምታቸውን አድርሰው ተቀመጡ። ወ/ሮ አባይነሽ ለነፍስ አባታቸው የሚጠጣ አምጥተው ፣

« አባ ቁርስ አድርገዋል ? » ሲሉ ጠየቋቸው ፣ በማቅማማት።

« እናንተ በላችሁ እንዴ ? » አሉና ፣ « መቼም ቄስና ዶሮ በጠጣ ቁጥር መብላት ይወዳል ። በይ እስኪ አምጪው ለውሃው አይከፋም » በማለት ጋቢያቸውን ማስተካከል ጀመሩ ። በመጀመሪያ እነ ያሬድ መብላት አልፈለጉም ነበር ። ወ/ሮ አባይነሽ በማሪያም በመማፀን አስገደዷቸው ። ከዚያ በኋላ የሚግደረደር አልነበረም ። በተሰይ ወ/ሮ አባይነሽ አዲሶቹን እንግዶች የታቦት ስም እየጠሩ በጉርሻ እያስጨነቁ ጋበዟቸው ። ከቁርስ በኋላ አባ ወደ ዋናው ጉዳያቸው ተመለሱ ።

« ቀጠሮአችን መቼም ደጉን እንጂ ክፉን የሚያርቅ ይሁንና ፣ ልጅቷ ተጠይቃ መልስ ሰጠች ? » አሉት ያሬድን እያስተዋሉት ።

ያሬድ በእጁ የያዘውን ብርጭቆ በእጁ አሸት አሸት በማድረግ « ሒሲና በነገሩ ተስማምታለች ። ሁሉንም ነገር ነግሬአት ከጥቂት ማመንታት በኋላ በእርቁ የተስማማች መሆንዋን ገልፃልኛለች ። ይህንም ለእናንተ እንዳደርስ ፈቅዳለች » በማለት አበሰራቸው ።

« እሰየው ! እሰየው ! መልካም መልካሙን ያሰማን . . . » ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ዘወር ብለው ፣ « እንኳን ደስ ያለሽ » አሏቸው ። ወ/ሮ አባይነሽም ፣ ከመቀመጫቸው ለአመል ያህል ብድግ ብለው አንገታቸውን ደፋ በማድረግ « በአምላክዎ » በማለት ተቀበሉ ።

« እንግዲህ ዋናው ነገር ካለቀ ዘንዳ እናትና ልጅቱን አገናኝቶ ማነጋገሩ አይከፋም ። ለዚህ እንግዲህ ሽማግሌም አያስፈልግም ። አንተው ትጨርሰዋለህ » በማለት ወደ ያሬድ አስተዋሉ ።

ያሬድ በነገሩ እያቅማማ « ዋናው መታረቁ ይመስለኛል ። መገናኘቱ ቀስ በቀስ ይሆናል ። » በማለት ወ/ሮ አባይነሽን ተመለከተ።

ወ/ሮ አባይነሽ አንገታቸውን እንደ ደፉ « አዬ . . . ኧረ. . . ለእሱ ግድ የለም ። ምን ይከናል ብለው ነው ? እሩቅም አይደል እዚሁ እያለን ከእንግዲህ እንጠያየቃለን » በማለት ሁኔታውን ማስማማት ጀመሩ ።

ያሬድ ሁሉንም ነገር ገልጾ ለመናገር አልፈለገም ። እንደ ሕሊና አባባል እርቁ ፍጹም እንዳልሆነ አድርጋ ነበር የተናገረችው ። በእሷ በኩል ይቅርታ ታድርግ እንጂ በወላጆችዋና በአስካበች ላይ የተዋለውን ግፍ የማትረሳ መሆንዋን ገልፃለች ። ያሬድ ይህን መናገር እንደመነሻ መልካም ነው ብሎ ያመነበትን ግንኙነት ማፍረስ እንደሚሆንበት ገመተ ። በመቆየት ቂም ስለሚፋቅ ቀሪውን ለጊዜ መስጠት እንደሚሻል አመነ ። ወ/ሮ አባይነሽ ያሰቡት ስለተሟላ በጣም በመደሰታቸው የመጠጥ ዓይነት ከቢራ ወደ ውስኪ እንዲቀየር ሀሳብ ሲያቀርቡ ያልተስማማው ያሬድ ብቻ ነበር ። አባ ብርጭቆአቸውን እየተመለከቱ « ይሻል ብለሽ ነው » በሚል ዓይነት ያስቀዱትን ጭልጥ አደረጉ ።

ያሬድ ብቻውን በቢራ ሲያዘግም ለሌሎቹ ጠርሙስ ውስኪ ቀረበና መኮምኮሙን ተያያዙት ። ጨዋታው እየደራ ቀደም ሲል የነበረውን የሥነ-ስረዓት ልውውጥ በቤተሰባዊ ሁኔታ ተለውጦ ሆድ ያባውን . . . እንዲሉ የዘወትር ፀባያቸውን ቀየረና የተደበቀውን ወጣ ማድረግ ጀመረ ። ወ/ሮ አባይነሽ ፣ « የጋብቻ ዝምድና አለኝ » ብለው ከሚያምኑት ከያሬድ ጋር የሆዳቸውን ጨዋታ ከፈቱ ። እሱም የሚናገሩትን ሁሉ « እህ . . እህ . . » እያለ ማዳመጡን ተያያዘው ። በመካከል አንገታቸውን ወደ ያሬድ ለገግ አድርገው ምስጢር ለማውራት እንደሚጥር ሰው ፣ « አንተዬ አንድ ነገር እጠይቅሃለሁ ብዬ አሁንም ሕሊና በዚያ መጥረቢያ ታመልካለች ? » ሲሉ የሚከነክናቸውን ጥያቄ ጠየቁት ። ያሬድም ይህን ጥያቄ ከወ/ሮ አባይነሽ እንደጠበቀው ሁሉ ከት ብሎ ሳቀና ፣

« አይ እማማ አምልኮት እኮ አይደለም » አለ ።

ወ/ሮ አባይነሽ « አምልኮ አይደለም ? » አሉት ። እራሳቸውን ወደ ጎን መለስ አድርገው በጉጉት እያስተዋሉት ፣

« ታሪኩ እንዲህ ነው ። በቀላሉ ፣ ሕሊና አባቷ ሲሞቱ ፎቶግራፍ አላገኘችም ። በእሱ ምትክ ያገኘችው መጥረቢያቸውን ነበር ። ይህ መጥረቢያ ከአባቷ ጋር ብዙ ጊዜ የቆየ በመሆኑ ስታየው የአባቷን ምስል ያስታውሳታል ፣ ይህ ጥንቆላ ወይንም አምልኮት አይደለም ። ማስታወሻ ማለት ነው ። እንደማንኛውም ወርቅ ፣ ልብስ ፣ ፎቶግራፍ ሊሆን ይችላል ። » በማለት አትኩረው የሚመለከቱትን ወ/ሮ አባይነሽን አስተዋላቸው ፤ የተናገረው ገብቶአቸው እንደሆነ ለማረጋገጥ በመፈለግ ዓይነት ።

ወ/ሮ አባይነሽ አፋቸውን ወደ ጎን በማጣመም እንደማሽሟጠጥ አድርገው « እሱስ አይደለም ፤ ቢቻል ማስጣል ነው። አምልኮት ባይሆን ኖሮ ይህን ያህል ከመጥረቢያ ጋር አጣብቆ የሚያንከራትታት ምን አለ ? » በማለት ጉዳዩን በቸልታ ለመጨረስ አሳጠሩት ። ንግግራቸው ለያሬድ አልተዋጠለትም ነበር ።

« ሕሊና አባቷን በጣም ነው የምትወደው ። በአባቷ የሚመጣባትን ሁሉ ትጠላለች ። ስለዚህም ነው መሰለኝ ከእርሶ ጋር በአንዳንድ ጉዳዮች መግባባት ያልቻላችሁት » በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ እውነተኛ የሚመስለውን ሀሳብ ገለጸላቸው ።

ወ/ሮ አባይነሽ ትንሽ አሰብ አደረጉና « ማን ዘመዱን የማይወድ አለ ? ሆኖም እኔ ምን ላድርግ ? አንድ እህቴን ከጉያዬ ፈልቅቆ የወሰደብኝ ስለሆነ አባትዋን መውደድ አልቻልኩም » ከማለታቸው ዓይናቸው እንባ አቀረረ ።

« በሕሊና ፊት ስለ አባትዋ ከተቻለዎት መጥፎ ነገር አለማንሳቱ ይመረጣል ። መጥረቢያውም ከዚህ የተለየ አይደለም » አላቸው ባለፈው እሁድ ያየው እንዳይደገም እየሰጋ ።

ወ/ሮ አባይነሽ በረጅሙ ተንፍሰው « መቼስ ምን ይደረጋል » ብለው ከመጠጡ ተጎነጩ ። አባና ተሾመ ለሰሐይማኖት እንስተው በክርክር መልክ ያወራሉ ። አባ የታቦት ሥም እየጠሩ « ኸረ ይቅር ይበልህ » እያሉ ተሾመን ለማላመን ሲሞክሩ ተሾመም

« ሰውን እኩል አድርጎ ከፈጠረ ታዲያ ለምን ያበላልጣል ? » በማለት አባ ለሚሉት ሁሉ በተቃውሞ ይመልሱላቸዋል ።

ጨዋታው ደርቶ ፣ መጠጡም እየተቀዳ ፣ ጊዜው እየመሸ መምጣቱን ያስተዋለ አልነበረም ። የመኪና ጡሩንባ ድምፅ የፈሩቅን መምጣት አበሰረ ። ወ/ሮ አባይነሽ የመሸበር ሁኔታ ሲታይባቸው በጉዳዩ ትንሽም ያልተደናገጡት ተሾመና ያሬድ ነበሩ ። የቀረበላቸውን መጠጥ በአንድ ትንፋሽ ጅው አድርገው ጨለጡና ብድግ ብለው ተሰናብተው ከቤቱ ወጡ ። ያሬድና ተሾመ ለመሄድ እንደተነሱ ወ/ሮ አባይነሽ « እባካችሁ ቆዩልኝ ይሄን ሰው ብቻዬን እንዳገኘው አልፈልግም » በማለት ተማፀኑዋቸው ። በሁኔታው ግራ የተጋባው ያሬድ ብቻ ነበር ። ተሾመ ጉዳዩን በጥቂቱም ቢሆን ከውጭ ሳይሰማ አልቀረም ።

« የትኛው ሰው ነው ? » በማለት ያሬድ እንደቆመ ወ/ሮ አባይነሽ ያልሰሙ መስለው ወደመኝታ ቤታቸው አመሩ ። ስለ ፈሩቅና ስለ ወ/ሮ አባይነሽ ግንኙነት በዚያች አጭር ጊዜ ውስጥ ተሾመ ያሬድን ሊያስረዳው ሞከረ ። ያሬድ የሚሰማው ነገር እጅግም ሊገባው አልቻለም ። በኋላ ተሾመን « ተነስ እንውጣ ። ታዲያ እኛ ምን ቤት ነን ? » አለው ። በዚሁ መካከል ወ/ሮ አባይነሽ ከመኝታ ቤታቸው በትንሽ ነገር የተጠቀለለ አንዳች ነገር ይዘው ተመለሱ ። ያሬድ በሀፍረት ወደ መቀመጫው ተመልሶ ወ/ሮ አባይነሽ በእጃቸው



የያዙትን ጥቅል ነገር ተመለከተ ። ወ/ሮ አባይነሽ ወንበራቸው ላይ ሆነው አስር ጊዜ የሳሎናቸውን በር ይከታተላሉ ። ጭንቀታቸውና የሽብር ሁኔታቸው ለያሬድ ሠላም አልሰጠውም ።

« ምነው ተጣልታችኋል እንዴ ? » ሲል ለስለስ ባለ አነጋገር ጠየቃቸው ።

ወ/ሮ አባይነሽ የያዙትን የተጠቀለለ ነገር ጨበጥ ጨበጥ እያደረጉና ከንፈራቸውን እየጠራረጉ « መጣላትስ አይደለም ። ሆኖም ከእሱ ጋር እናንተ ባላችሁበት የምንነጋገረው ነገር ስላለ ነው » አሉና ዓይናቸውን ወደ በሩ ወረወሩ ።

ፈሩቅ መኪናውን አቁሞ ወደ ቤት ወዲያውኑ አልገባም ። በመኪናው ላይ የተጫነውን ዕቃ እንዲያወርዱ አጠገቡ ለቆሙት የወጥቤት ሠራተኞች ከተናገረ በኋላ በቀጥታ ወደ ቡና ቤት ነበር ያመራው ። በቡና ቤቱ ውስጥ ለውጥ መኖሩን ወዲያው ተረዳ ። ግራ በመጋባት የሚያውቃትን ባሬስታ ጠጋ ብሎ « ምን ተፈጠረ እባክሽ ? » በማለት ጠየቃት ። ሴትዮዋ ከፈሩቅ ጋር እጅግም ቅርበት አልነበራትም ። አንገቷን ከምትሰራው ሥራ ለአፍታ ቀና አድርጋ « ምን ተፈጠረ ? » በማለት ፈገግ አለችና « ሰዎቹን ነው ? ሄዱኮ ጋሼ ፈሩቅ » አለችው ።

ፈሩቅ በሁኔታው መደናገጥ ብቻ ሳይሆን በጣም ተናደደ ። በማይሰማ ድምፅ እያጉረመረመ በጓሮ በር እየተንደረደረ ወጣ ። ወደ ሳሎን ሲገባ ተሾመና ያሬድ ተነስተው ተቀበሉት ። ፈሩቅ ቀጥ ብሎ እንደገባ ከተሾመ ጋር የእጅ ሰላምታ ተለዋወጡ ። ፊቱን ወደያሬድ መለስ አድርጎ ከላይ እስከታች እየገላመጠው ያሬድን አስተዋለው ። እጁን ዘረጋለት ። ያሬድ በአድራጎቱ ሲበቀለው ቢፈልግም በግድ ስሜቱን ተቆጣጥሮ ጨበጠው ። ፈሩቅ ቀጥሎ ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ዘወር አለና « ምነው ዛሬ ደግሞ ተክዛችኋል ? ውስኪ ተንተርሶ ትከዛ

በቤታችን ያልተለመደ ነገር ነው። ምን ሆናችሁ ? » ብሎ ፊት ለፊት ባለው ፎቴ ወንበር ላይ ዘርፈጥ ብሎ ተቀመጠ ።

« እፎይ » ብሎ በረጅሙ ተንፍሶ በእጁ ከፀጉሩ እስከ ፂሙ ፊቱን ዳበሰ ። ወ/ሮ አባይነሽ በቀኝ እጃቸው ምስጢራዊ ዕቃቸውን እንደጨበጡ ፣ ፈሩቅ ላይ አፍጥጠው ባልተረጋጋ ስሜት « እሺ ሲወጣም ወጣሁ አይባልም ። ከየት ነው ደግሞ ብቅ ያልከው ? » በማለት የመግቢያ ንግግርአቸውን ጀመሩ ።

ፈሩቅ የተፈጠረው ሁኔታ አዲስ ስለሆነበት ፣ ከዚያም በላይ እሰው ፊት ለመነጋገር ስላልፈለገ ፣ ለቀረበበት ጥያቄ ችላ ብሎ « ብርጭቆ የለም እንዴ ? » በማለት የውስኪውን ጠርሙስ ወደራሱ ጎተት አደረገው ። ወ/ሮ አባይነሽ የቀኝ እጃቸው የያዘውን ጥቅል ወደ ጉልበታቸው እያስጠጉ

« በመጀመሪያ የተጠየቅከውን መልስ ፣ለመጠጡ ትደርሳለህ» አሉት ።

« ደህናም አይደለሽ እንዴ ? ምን ተፈጠረ ደግሞ ? » አለና ወደ ያሬድ እየተመለከተ ፣

« ለጥያቄና መልሱ በኋላ እንደርሳለን ፤ አሁን እንግዶቻችንን እንሸኝ » ብሎ ብድግ አለ ።

« ተቀመጥ ! ባለህበት እንዳትንቀሳቀስ » ሲሉ ለረጅም ጊዜ እነ ያሬድ በጉጉት ሲጠብቁት የነበረውን ጨርቅ ከመቅስፈት ከላዩ ላይ እንደመግለጥ አደረጉት ። በእጃቸው የያዙት ጠቆር ያለ ሽጉጥ ነበር ። ያሬድና ተሾመ በድንጋጤ ከመቀመጫቸው ተነሱ ። ወ/ሮ አባይነሽ እነያሬድን በቁጣ መልክ « ተቀመጡ » ብለዋቸው የሽጉጡን አፈሙዝ ወደ ፈሩቅ አዞሩት « እንዳትንቀሳቀስ ! እለበለዚያ ደምህ ደመከልብ ነው የሚሆነው ። እኔ በዕድሜዬ ብዙ ደስታን ያየሁ ሰው ነኝ ፣ ባልፍም አይከፋኝም ። እምቢ የምትል ከሆነ አንድ ለእኔ አንድ ለአንተ ። » አሉት ፈሩቅን እየተመለከቱ ። ፈሩቅ ሲገልፀው



በማይችለው ስሜት ውስጥ እንዳለ ዓይኖቹን ወ/ሮ አባይነሽ ላይ ተከለ።

« ውሸት እንዳይመስልህ ። ይልቁንስ ያለምንም ደም መፍሰስ ሥራችንን ብንጨርስ ይሻላል » አሉት ። ሽጉጣቸውን በእጃቸው ጠበቅ እያደረጉ ። የነተሾመን ጭንቀት የተረዱ ይመስል « እናንተ ቁጭ ብላችሁ አዳምጡ ። ይህ ታሪክ እናንተንም ይመለከታል ። አትንቀሳቀስ ብየሃለሁ አንተ ወራዳ » ሲሉ ፈሩቅን በኃይለ ቃል አስጠነቀቁት ። ፈሩቅ በተቀመጠበት እየኮሰሰና የድሮ ቁመቱ እያጠረ፣

« የምን ቲያትር ነው ? አበድሽ እንዴ ? በመሣሪያ ጨዋታ የለም ። ይልቁንስ ባርቆብሽ እንዳታበላሽኝ » ሲል ተናገረ ።

« መባረቁን ተወው ። ስለዚህ የት ታውቃለህ ? እንክፍ ሳይባርቅ አዳፍንብሃለሁ ። ወስላታ ቀጣፊ ያ ምላስህ ከአንተ ተለይቶ አይሞትም » በማለት በርቀት ደረቱ ላይ ደገኑበት ። ፈሩቅ ተነስቶ እራሱን ለመከላከል ሙከራ አደረገ ። የወ/ሮ አባይነሽ ትዕዛዝ ከመሣሪያው የበለጠ ተሰሚነት ነበረው ።

« ተቀመጥ ! ተቀመጥ ነው ያልኩህ ወራዳ » በማለት እንደ ብራቅ ጮሁበት ። ለፈሩቅ ይህ አዲስ ፀባይ የእብደት ቢመስለውም ድርጊቱ ሁሉ ከመቼውም በበለጠ ወ/ሮ አባይነሽ ቆርጠው መነሳታቸውን አስገንዝቦታል ። በሁለት እጁ ራሱን ይዞ « ወይኔ ፈሩቅ ወንዱ መጫወቻ ሆንኩኝ » አለና ወደ እነ ያሬድ እጁን ዘርግቶ፣ « ምነው ሰዎች ዝም ብላችሁ ታያላችሁ ? ኧረ ገላግሉኝ » በማለት ተማፀነ ።

« አይዞህ እስከ መጨረሻው ትገላገለዋለህ ። በል አሁን በመጀመሪያ ስለ ሰረከው መጥረቢያ እስኪ ንገረን » አሉት ። ዝም አለ ። አፉ ተዘግቶ ምላሱ ተሳሰረበት ።

እራሱን ወደ መሬት አቀርቅሮ እጁን ደረቱ ላይ እንዳነባበረ አጎንብሶ ቀረ ። ወ/ሮ አባይነሽ የፈሩቅን ሁኔታ የተረዱ ይመስል

ጥያቄውን ቸል ብለው « ቤታችሁን የሰረሰረው ሌባ ይሄ ነው ። እኔንና ሕሊናን ለማጣላት ከመሠረቱ በነገር ሲያዋጋን የነበረው ይሄ ሾካካ ነው » አሉ ። ቀጥለውም ፈሩቅን በንቀት ዓይን እያዩ ።

« በል የመኪናውን ቁልፍ እዚያ ላይ ቁጭ አድርግ » ሲሉ አበቡት ፤ በግራ እጃቸው ጠረጴዛውን እያሳዩት ።

« የየትኛውን መኪና ? መኪና ላይ ነው ያለው ። » አለ በግድ የተሳሰረ ምላሱን ታግሎ ። ወ/ሮ አባይነሽ ያሬድን ተነስቶ እንዲፈትሸው አዘዙት ። ፈሩቅ ባላወቀው ምክንያት ፊቱን ዞር አደረገ። ባልጠበቀው ቅፅበት በተሰነዘረ ጥፊ ፊቱ ነደደ ።

ያለምንም ማንገራገር ኪሶቹን አስፈተሸ ። የመኪና ቁልፍ ግን አልተገኘም ። ወ/ሮ አባይነሽ ውስጣቸው በእልህ ተሞላ ። በድጋሚ የመጨረሻ ኃይላቸውን አሳረፉበት ። በዚህ ወቅት ፈሩቅ ጭካኔያቸውን በሚገባ ተረዳ ። ለትዕዛዙ ከመቅስፈት መልስ ሰጠ ። ራሱን ፈተሸ ። ከሱሪ ኪሱ ውስጥ በትንሽ የቆዳ ቦርሳ የታሰሩ ቁልፎችን አውጥቶ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠ ። ወ/ሮ አባይነሽ የሚፈልጉትን ያገኙ መሰሉ ።

« በል አሁን ትንፍሽ ሳትል ሰተት ብለህ ውጣ !አንተ ባለጌ !» ሲሉ ፈሩቅን አዘዙት ። ፈሩቅ ቃል አልተነፈሰም ፤ አላቅማማም ። እንደታዘዘው ትንፋሹን ውጦ ወደ ውጭ ገሰገሰ ። ከበስተጀርባው ሽጉጣቸውን እንደደገኑ እስከዋናው በር ድረስ ከሸኙት በኃላ ዘበኛ ቸውን ጠርተው « ሁለተኛ እዚህ ግቢ እንዳይገባ » ሲሉ የከረረ ትዕዛዝ አስተላለፉ ።

ይህ ከሆነ ብዙም አልቆየ ። በግቢው በር ላይ የድንጋይ ጋጋታ ዘነበ ። የቆርቆሮው ጩኸት ከጥይት ድምፅ ያስመሰግን ነበር።

ወ/ሮ አባይነሽ ከውስጥ ሆነው ሽጉጥ የያዘ የቀኝ እጃቸውን ከፍ አድርገው ሁለት ጊዜ ተኮሱ ። ወዲያው የድንጋዩ ጋጋታ ቀጥ አለ በመቀጠል የኡኡታ ድምፅ ተሰማ ።



* * *

ሕሊና በሯን ዘጋግታ ፣ ምግብ አበገጃጅታ ፣ የያሬድን መምጣት ከአልጋ ላይ ጋደም ብላ ትጠባበቃለች ። ሆኖም ያሬድ ከሄደበት ሳይመለስ ጊዜው እየመሸ ሲሄድ ሀሳብ ውስጥ ገባች ። ዛሬ ቀን ላይ ከወ/ሮ አባይነሽ ጋር ቀጠሮ እንደነበረው ታውቃለች ። ቀጠሮው በያሬድ ላይ የከፋ ነገር ያስከትላል የሚል ግምት አልነበራትም ። ቀኑ ወደ ምሽት ፣ ምሽቱ እየዘገየ ወደ ሌሊት እየተሸጋገረ ሲመጣ የሕሊናም አእምሮ መረበሽ ጀመረ ። በዚሁ ስሜት ውስጥ እንዳለች ራቅ ካለ ስፍራ ጩኸት ስትሰማ ልቧ ለሁለት ትርክክ አለ ። ጆሮዋን ቀና አድርጋ የጩኸቱን አቅጣጫ ለመለየት ሞከረች ። ለጊዜው መነፈሷ በመጠኑ ረጋ አለ ።

ብዙም ሳይቆይ የተኩስ ድምፅ ተሰማት ። ከነበረችበት ተሰፈንጥራ ተነስታ በሩን በርግዳ ወጣች ። ኃይለኛ ጩኸት ተቀበላት። ጊዜ አላጠፋችም ወደ ጎረቤት በረረች ።

« የኩቻ እናት ! አንቱ የኩቻ እናት ! » ስትል በሩን እያንኳኳች ተጣራች ።

« ማነው ? ምንድነው ? » አሉ የኩቻ አባት መብራት እያበሩ ። « እኔ ነኝ . . . እኔ ሕሊና ነኝ . . . ጋሼ » አለች እየተንቀጠቀጠች። የኩቻ አባት በሩን ከፍተው« ግቢ ምን ሆናችሁ? » አሉና ሕሊና ስትገባ በሩን ዘጉት ። የኩቻ እናት በውስጥ ልብሳቸው ላይ ጋቢ እንደደረቡ በድንጋጤ መናገር ያቃታት ሕሊናን እየተመለከቱ « ተጣላችሁ እንዴ » ሲሉ ጠየቋት ።

« አልሰማችሁም ! የተኩስ ድምፅ ! » አለችና ምላሷ ስለተሳሰረ ዝም አለች ።

« ማነው እሱ ? » በማለት ጎርነን ባለ ድምፅ ሕሊናን በድንጋጤ ዓይን እየተመለከቱ ጠየቋት የኩቻ አባት ።

ሕሊና ዓይኖቿ እንባ እያቀረሩ « እኔ እንጃ ጋሼ ያሬድ እስከአሁን አልገባም ። እንደዚህ አምሽቶ አያውቅም ። ቀን እንደወጣ ነው » እንዳለች ፤ እራሷን በሁለት እጆችዋ ይዛ « ወይኔ መከራዬ ! ወይኔ ወይኔ ! » ስትል ለቅሶዋን ለቀቀችው ።

የኩቻ አባት « ኧረ ዝም በይ ምን ይሆናል ብለሽ ነው ? ቆይ እኔ ሄጀ የት እንዳለ ፈልጌ ይገኘው እመጣለሁ » አሉና ወደ ጓዳ ገባ አሉ ።

« የት ነበር የሄደው ? አዲስ አበባ ከጓደኞቹ ጋር ሄዶ እንዳይሆን ? አይዞሽ ምን ይሆናል ብለሽ ነው ? » በማለት የኩቻ እናት ፊቷን ቀና አድርገው እየተመለከቱ አባበሏት ።

« ከዛች አረመኔ ጋር ቀጠሮ አለኝ ብሎ ነው የሄደው ፤ ምን ይታወቃል » አለች ሕሊና ። የኩቻ አባት ከጓዳ በር ልብሳቸውን ለብሰው ሽጉጣቸውን አቀባበሉና ወጣ አሉ ።

« ሕሊና ፤ ሕሊና » እያለ በጩኸት አንድ ድምፅ ተጣራ ። የኩቻ እናት « እስኪ ዝም በሉ» በማለት የሁሉንም ጆሮ ወደ ጥሪው እንዲያቀና አደረጉ ። ያሬድ ነበር ።

ሦስቱም ተያይዘው ወደነያሬድ ቤት ሲሄዱ በሩ ተከፍቶ የበረንዳ መብራት እየበራ ነበር ። ሁለቱ ጎረቤቶቹ ወደ ውስጥ ሲዘልቁ ሕሊና ያሬድን አልፋ ወደ መኝታዋ ሄዳ አልጋዋ ጫፍ ላይ ተቀምጣ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ። የኩቻ አባት ወንበር ሳብ አድርገው ተቀመጡና « ምነው እባክህ ሰው ይሰጋል አትልም ? » በማለት የግሳጼ ዓይናቸውን በያሬድ ላይ ጣል አደረጉ ። የኩቻ እናት የባላቸውን ቁጣ በመቀበል ዓይነት ራሳቸውን አወዛወዙ ።

ያሬድ እራሱን በሀዘኔታ እየነቀነቀ « እንዳስቸገርኳችሁ ይገባኛል የኩቻ አባት ! በጣም በጣም ይቅርታ . . . ሆኖም ያመሸሁት ከቁጥጥሬ ውጪ የሆነ ጉዳይ ስላጋጠመኝ ነው ። የኩቻ እናት ተቀመጡ » አለና ብድግ ብሎ ወደ ወንበሩ አመለከተ ። አይ



አልቀመጥም ፤ እንኳን በደህና መጣህ ! ቤቱ ክፍት ነው እንሄዳለን » አሉና ዓይኖቻቸውን ወደባለቤታቸው መለሱ ።

« እውነቷን ነው . . . በል ወቀሳው ለነገ ይደር ። ደግሞ መሽቷል ። እናንተም ተኙ » እያሉ ከተቀመጡበት ተነስተው ከባለቤታቸው ጋር ተያይዘው ወጡ ።

ያሬድ ክንዱን በጠረጴዛው ላይ ተክሎ በሁለት እጆቹ መሀል ፊቱን ቀብሮ ጥቂት ከተከዘ በኋላ ወደ ሕሊና ዞር ብሎ « በቃ አለፈ። ምን የሆንኩ መሰለሽ ? » በማለት ፈገግ አለ ። ሕሊና ቃል ሳትተነፍስ ከተቀመጠችበት ተነስታ እራት አቀረበች ።

« ሕሊና እራት አልፈልግም ፤ ጠግቤያለሁ ፤ ነይ ተቀመጭ» በማለት ጎኑ ያለውን ወንበር ሳብ አድርጎ ከጠረጴዛው ራቅ ብሎ ተቀመጠ ። አነጋገሩ የኩርፊያ ወይም የመቀየም መሰላት ። ልታሳዝነው አልፈለገችም ።

« የተቆጣሁ መሰለህ ነው ? አልተቆጣሁም ። እኔ ሲተኩስ . . . » አለችና የጀመረችውን ሳትጨርስ አቋረጠች ።

ያሬድ « እሮይ . . . » አለና ተነፈሰ ። « ተኩሱ ነው ያስደነገጠሽ ? እሱስ እኔንም አስደንግጦኛል ። » እላት ዝርዝር ሁኔታውን ለሕሊና ሳለመናገር ። ቀጠለናም « ባይሆን አንቺ እራትሽን ብይ ። እኔ ደክሞኛል ሄጄ ልረፍ » ብሎ ከመቀመጫው ብድግ አለ ።

« አንተ ካልበላህ ብቻዬን አልበላም » አለችው ንግግሯን ጫን አድርጋ ።

« እሺ አብረን እንብላ » አለና ተመልሶ ተቀመጠ ። እራት ስታዘጋጅ ወጡ ቀዝቅዞ ነበር ። ሕሊና « ቆይ ወጡን ላሙቅ » ብላ ከተቀመጠችበት ተነሳች ።

« ማሞቅ አያስፈልግም ። ገና እሳት አንድደሽ ? አይሆንም » አለና ያሬድ አስቀራት ። ሁለቱም እራታቸውን መብላት አይበለው አበላል ተያያዙት ። ያሬድ በተረፈው ወኔ በመጠኑ ሲያዘግም

ሕሊናም የተረበሸ ስውነቷን በማስገደድ ጥቂት ጎራረሰች ። እራት ተበልቶ እንዳለቀ እጃቸውን ታጥበው ፣ ሕሊና ዕቃውን በወግ በወግ አድርጋ እንደጨረሰች ያሬድ « የበላነው እስከሚንሸራሸር ትንሽ እንቀመጥ » የሚል ሀሳብ አቀረበ ። ሕሊና በሀሳቡ ተስማምታ አጠገቡ ተቀመጠች ። ሕሊና ከጎኑ ተቀምጣ ያሬድን በፈገግታ እያየችው « እኔኮ ሞኝ ነኝ ። የኩቻን እናትና አባት በጠበጥኳቸው ። አሁን ምን ይባላል ? » ብላ ፊቷን በቀኝ እጇ ሸፈነች ።

ያሬድ የሕሊናን ንግግር ችል ብሎ « ሕሊና እስኪ ንገሪኝ ? አክስትሽ መጥረቢያሽን ለመውሰድ ሞክረው ነበር ? » አላት ።

« ደግሞ ምን ነግረውህ ይሆን ? ቀደም ሲል ከእኔ ጋር የመጨረሻ ጥል የተነሳው በመጥረቢያው ነው ። » በማለት እንዴት በመጥረቢያው እንደተጣሉ ዘርዝራ አጫውታው ስታበቃ « ግን ምን አሉህ ? » ስትል ጠየቀችው ።

« አይ እንደዚሁ የአንቺና የአክስትሽን የጥል መነሻ ለማወቅ ያህል ነው ። » በማለት ጥያቄዋን ቀጭቶ ብድግ አለ። « የተረፈውን ሌላ ጊዜ እንጫወታለን ። ለዛሬ በዚሁ ይብቃን እንተኛ » አለና ወደ መኝታ ክፍሉ አመራ ። ልብሱን አወላልቆ ብርድልብሱ ውስጥ ገብቶ ስለ ምሽቱ ድርጊት አሰላሰለ ።

« መቼም ሴትዮዋ በጣም የሚገርሙ ናቸው ። ልክ እንደ ወንድ ያንን ግዙፍ ሰው አዝረጠረጡት ። ግን ለምን ነበር መጥረቢያውን ከሕሊና እንዲሰረቅ የፈለጉት ? ምስጢሩን ለመናገር ያልፈለጉበት የራሳቸው ምክንያት ይኖራቸዋል ። ግን ፈሩቅ ጉድ አድርጓቸዋል ። አሁንም ቢሆን መጥረቢያውን ሳያገኝ የሚተው አይነት አይደለም ። ፈሩቅም ትዕዛዛቸውን ቢፈጽም ኖሮ ይህ ሁሉ መከራ አይደርስበትም ነበር ። አይ ምስኪን ፣ መቼም እኔ ነኝ ያጋለጥኩት ። » የሚገርም ነው « የመጥረቢያውን ታሪክ ከሕሊና ጋር በማያያዝ ታመልከበታለች አሉኮ ። አምልኮትና ማስታወስ



የተለያዩ ነገሮች ናቸው ። የእኔ ሕሊና በመጥረቢያ አታመልክም ። ኡፉ ሕሊና . . . ሕሊና . . . ሕሊና መቼ ይሆን እውነተኛውን ጨዋታ የምንጫወተው ? እስከመቼ እንደዋሽሁሽ እኖራለሁ ። እስከመቼ . . . እስከመቼ . . . የዛሬ ሁለት ፣ ሶስት፣ አራት አመት ! አይሆንም አሁኑኑ ሄጄ ከጎኗ ተኝቼ ክንዷን ተንተርሼ . . . » ሌሊቱ እየተገባደደ ነበር ።

* * *

ያሬድ ከሕሊና የሚጠብቃቸው ብዙ ነገሮች የሉትም ። ከሕሊና አንድ ነገር ብቻ ነው የሚፈልገው ። እሱንም በራሷ ጊዜ እንድትረዳለት ይሻል ። ከዚህ አልፎ ሁኔታውን ገልጾ መናገር ግን ወኔው አልፈቀደለትም ። እሷን አዘውትሮ ማየትና ውበቷን በማድነቅ ከማምለክ የተሻለ አማራጭ አላገኘም ። በእርግጥ ሕሊና እንደምትወደው ያውቃል ። ይህ መውደድ ግን ከየትኛው ወገን እንደመነጨ አምኖ ለመቀበል አልሆነለትም ። ሕሊና በኑሮዋ ደስተ፣ በባህሪዋ አርቆ አሳቢ ከመሆኑዋ ጋር በትምህርቷ የከፍተኛ ውጤት ባለቤት ለመሆን በቅታለች ።

አንድ ቀን ያሬድ ከሥራ በጊዜ ወጥቶ ቤቱ እንደገባ ሕሊና ከትምህርት ቤት ስትመለስ መክሰሱን አቅርቦ ሲበላ ደረሰች ። ከዘወትር የሠላምታ ልውውጥ በኋላ ልብሷን ለውጣ እንደተመለሰች ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ተውጦ ውበቷን ካስተዋለ በኋላ ፣

« ሕሊና ! » አላት ።

« አቤት » አለችው ጥያቂያዊ በሆነ አቀራረብ ።

« አክስትሽ በጠና ታመዋል ። ምናለበት ሄደን ብንጠይቃቸው? » አለ ።

« መታመማቸውን ከሰማሁ ቆይቻለሁ ። ሆኖም ዓይናቸውን ለማየት አልፈልግም ። ጋሼ ያሬድ እኔን አትቀየመኝ ። አንተ

ልትጠይቃቸው ትችላለህ ። እኔ ሄጄ ለእሳቸው የማደርገው አንዳች ነገር አይኖርም ። እባክህ ጋሼ ያሬድ » ብላ ዓይን ዓይኑን እየተመለከተች ፣

« እንድጨነቅ አታድርገኝ ። እኔ ያንተን ጥያቄ እንቢ ማለት አልችልም ። ግን እሳቸውን ባላያቸው ደስ ይለኛል ። » ስትል ተለማመጠችው ። ኮስተር ብሎ ሒሊናን እያየ « ሒሊና ስሚ አባትሽንና ወ/ሮ አባይነሽን ያቀያየማቸው ጉዳይ ሥረ-መሰረቱ ከሀገራችን በሚገባ ተወግዷል ። ዛሬ ሁሉም ነገር መልኩን ቀይሯል፣ ለእናትሽ ሞት ፣ ለአንቺ ችግር ውስጥ መውደቅ ፣ እንዲሁም ለመላው ህብረተሰብ መጨቆንና መረገጥ መንስዔ የሆነው መሬት ከእንግዲህ ወዲያ ለግለሰቦች የሀብት መደለቢያ መሆኑ ቀርቶ መሬት ላራሹ ተብሎ ጭቁኑ ሕዝብ ሠርቶ የሚበላበት ፣ የወዙን የላቡን የሚያገኝበት ጊዜ መጥቷል ። ወ/ሮ አባይነሽም ሆኑ መሰሎቻቸው ከእንግዲህ ወዲያ ለግሌ የሚሉት ሀብት የላቸውም ሁሉም ሰው በእኩልነት የሚኖርበት መልካም ጊዜ ከፊታችን ተደቅኗል ። አብዮት ፈንድቷል ፣ በመሆኑም እያንዳንዳችን ልንደሰት ይገባናል ። አንቺንም የሚያስጋ አንዳች ነገር የለም ። ዛሬ ወ/ሮ አባይነሽ ሁሉንም ነገር አጥተው የአልጋ ቁራኛ ሆነዋል ። ምግብ በወጉ የሚያቀርብላቸው ሰው እንኳ የላቸውም ። ለደረጉት ጥፋት መቼም ከሰው ሁሉ በላይ ኖረው ከሰው በታች ሆነው መዋላቸው ሳይሞቱ በህይወታቸው እንዲሁ ሳይረዳቸው አይቀርም። እየከፈሉት ያለው የሚበቃቸው ይመስለኛል ። አንቺ ልጅ ነሽ ፤ ይቅር ልትያቸው ይገባል » ሲል ለመናት ። ሒሊና የጭንቀት ሁኔታ እየተለማት ወደ ያሬድ ተመለከተች ።

« ጋሼ ያሬድ አጥብቀህ ስለለመንከኝ ለመሄድ አስገደድከኝ ። ግን እዚያ ቤት ብዙ አልቆይም ። የእሳቸውን ዓይን ሳየው የሞቱትን ያስታውሰኛል። የሞቱትን ደግሞ በስቃያቸው ማስታወስ



አልፈልግም። ሠላም የነሳኋቸው ይመስለኛል » ስትል ዓይኖችዋን እንባ እየሸፈናቸው ተናገረች ።

ያሬድ ከዚህ በላይ መስማት አልቻለም ። የሒሊና መራር ንግግር ለራሱም የሬት ያህል ሆኖበት ነበር ። ከነበረበት ተነስቶ መኝታ ክፍሉ ገብቶ ተኛ ። አልጋው ላይ ተጋደሞ ስለወ/ሮ አባይነሽ ማሰብ ጀመረ ። ፈሩቅን ከቤታቸው ሲያባርሩት የነበራቸውን ቆራጥነት አስታወሰ ። በተለያዩ ቀናት ተጠርቶ ሄዶ ስለ ብዙ ነገሮች ሲያማክሩት የጤንነታቸውን መባባስ አስተዋለ ። በተለይ አንድ ቀን በጠና ታመው ሒሊናን ለማየት የፈለጉበት ቀን ትዝ አለው ። እሱና ሒሊና ከሳቸው ጋር አብረው እንዲኖሩ የለመኑት ሁሉ ትዝ አለው ። በወቅቱ አሳዝነውት ነበር ። ለምን ለሒሊና እንዳልነገራት ለማስታወስ ሞከረ ። « ሒሊና እሺ አትለኝም እንጂ እጠገብዎ ብትሆን እኔ በበኩሌ ደስ ባለኝ ነበር » ሲል ቃል ገብቶላቸው ነበር ። ሆኖም አለመንገሩ ልክ ነበር ። ሒሊና ለዚህ ፈቃደኛ የምትሆን አልነበረችም።

ስቅስቅ ብለው አለቀሱ ። « አያልቅሱ እማማ . . . ማልቀስ ለእርስዎ ጥሩ አይሆንም » አለና ያሬድ የለበሱትን ጋቢ አስተካከለላቸው ።

ሕሊና ምንም እንኳ ቂሟ በውስጧ ስርጾ የተቀመጠ ቢሆንም ካየችው ሁኔታ አንፃር ልቧ በጣም አዘነ ። በደሳቸው ሁሉ ተረሳት ። ወ/ሮ አባይነሽም መረጋጋት ጀመሩ ። እንባ በሀዘኔታ የሚያፈስላቸው አንድ ሰው አጠገባቸው በማግኘታቸው ከበሽታቸው ተጽናኑ ። ከእንግዲህ ብቸኛ አይደሉም ። ሕሊና ከጎናቸው አለች ። ወደ አጠገባቸው እንድትቀርብ በእጃቸው ምልክት እያሳይዋት « ነይ እስኪ ደህና አድርጌ ልይሽ ? » አሉ ። እሷም የወረደውን እንባዋን በያዘችው ነጭ መሀረብ ጠራርጋ ተጠጋቻቸው ። በእጃቸው ፀጉሯን ዳሰስ ዳሰስ እያደረጉ እንደገና ለቅሶአቸውን ሲጀምሩ « እቴቴ እባክዎት አያልቅሱ » በማለት ኮስተር ብላ ተመለከተቻቸው ።

« ፀጉርሽ የወርቂቱን ነው የሚመስለው ። እያደግሽ ስትሄጂ የበለጠ ወረቂቱን እየመሰልሽ መጣሽ » አሉ ቀስ ብለው በሚንቀጠቀጥ ድምፃቸው ። በሀፍረት ዓይን አንገታቸውን ዞር ሲያደርጉ ያሬድ አጠገባቸው ቆሟል ። « ምነው አትቀመጥም ? ያሬድ ደህና ነኝ » አሉት ። ፎቴ ወንበሩ ላይ ሄዶ ተቀመጠ ።

የሁለት ዘመዳሞች ከብዙ ቂምና ጥል በኋላ መገናኘት አስደሰተው ። ብቻቸውን ሆነው እንዲጫወቱ ፈለገ ።

« የምደርስበት ቦታ አለ ። ሕሊና እስክምመጣ እየተጫወታችሁ ቆዩኝ » አለና አስተያየት ሳይጠብቅ የመኝታ ቤቱን በር ከፍቶ ወጣ ። ወ/ሮ አባይነሽ ወደ ሕሊና ትኩር ብለው እየተመለከቱ « ሕሊና መቼም ያለፈው አለፈ ። ቂም እንደማትይዥብኝ አምናለሁ ። እኔን ያሳሳተኝ ያ መናጢ ነው ። ነገር በማመላለስ የራሱን ቦታ ለማመቻቸት ሲል እኔና አንቺን አቆራረጠን። መቼም አንዱ አምላክ ብድሩን ይክፈለው እንጂ » አሏት ።



ሕሊና በእጇ የያዘችውን መሀረብ እያገላበጠች በሀዘኔታ ታዳምጣቸው ነበር ። በወ/ሮ አባይነሽ አነጋገር ተገርማ « ሰው በመሞቻው ደግ ደጉን ነው የሚያሳስበው » ስትል አሰላሰለች ።

« ፀጉርሽ የእናትሽን ይመስላል » የሚለውን አነጋገር ከአባቷ የመጨረሻ ቀን አባባል ጋር በማመሳሰል የወ/ሮ አባይነሽ ቀን መቃረቡ ታሰባት ።

« ሰው ሲባል በአጠቃላይ ሲኖር እንጂ ሲሞት ማየት አልፈልግም » በማለት በህይወቷ የሁለት የሞቱ ሰዎችን በድን በአእምሮዋ ሳለች ። አንደኛው የአባትዋ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የአስካበች ነበር ። ሕሊና ቀና ብላ አክስቷን ለአንድ አፍታ ተመለከተች ። ለሁለቱም ሞት የአክስቷ ድርሻ እንደነበረበት ታውቃለች ።

« ሕሊና » ሲሉ አክስቷ ከሀሳቧ አባነኗት ። « እመት » አለቻቸው ።

« እንዴት ነው ኑሮሽ ፤ አይከፋሽም ? » ሲሉ ጠየቋት ።

« በጣም ደህና ነኝ ። ምንም አይከፋኝም ፤ ተደስቼ ነው የምኖረው » በማለት መለሰችላቸው ።

« አዎ ፤ ሰውነትሽ ያስታውቃል ። ምን ይከፋሻል አንቺ ውብ ወጣት ነሽ ለኔ ይብላኝ እንጂ ፈላጊ የሌለኝ » በማለት ፊታቸውን ዞር አድርገው በማይሰማ ድምፅ ለብቻቸው አጉረምርመው «ሕሊና የእኔ ልጅ ምናለበት እዚህ ብትኖሪና እስከዕለተ ሞቴ አንገቴን ቀና ብታደርጊው ? ለምድሩ ሳይሆን በሠማይ ቤት ይቀበልሻል ። ይኸው ቡና ቤቱንም ዘወር ብሎ የሚያየው ሰው በመጥፋቱ ተዘጋ ። እባክሽ ሕሊና ምንም ቢሆን የሥጋዬ ቁራጭ ነሽ። ቤቱ በቁሜ እንደ መቃብር አይዘጋብኝ ። ከሞትኩም ሁሉም ያንችው ነው ። ተማጠኚኝ » በማለት እንደ ህፃን ልጅ እየተንፈቀፈቁ በማልቀስ ለመኗት ።

እሷ ግን ለሰቅሶው ምንም ሀዘኔታ አልተሰማትም ። በውስጧ የሚፈላውን ቂም አውጥታ ልትዘረዝረው አልፈለገችም ። ትዕግስት እንደሚያሻት ተገነዘበች ።

« እባክዎትን አያልቅሱ እቴቴ ጥሩም አይደል » ስትል ተነፈሰች ።

« እባክሽ ፣ እባክሽ በፈጠረሽ እሺ በይኝ » ሲሉ በድጋሚ ተማፀኗት ።

« እቴቴ የእኔ መምጣት ምንም ነገር አይለውጠውም ። ተማሪ ነኝ ። ቀን ቀን ትምህርት ቤት ነው የምውለው ። በመጣም ለንብረቱም ሆነ ለእርስዎ ማድረግ የምችለው ነገር የለም » ብላ ፊቷን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ መለሰች ። « በዚህ ላይ . . .በዚህ ላይ. . . ከጋሽ ያሬድ ተለይቼ መኖር አልፈልግም ። የክፉ ቀን ባለውለታዬ ስለሆነ ልለየው አልችልም » አለቻቸው ።

ፊታቸውን በጋቢያቸው እየጠራረጉ ቀና ብለው አዩዋት ። « እኔ አሁን መቼ ተለያዩ አልኩ ። አብራችሁ መጥታችሁ እዚሁ እንድትኖሩ ነው ፍላጎቴ ። ቤቱ እንደሆነ ሠፊ ነው ። ቤትሽም ነው። ምን አለበት ባትጨክኚብኝ ? » አሏት ።

አዘነችላቸው ። ሀዘኔታዋ ግን ከልክ ያለፈ አልነበረም ። የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም ይባላል ። ዓይኖችዋን ጣለችባቸው ። ተያዩ ። የመኝታ ቤቱ በር ተንኳኩቶ ተከፈተ ። ያሬድ እራሱን ጎንበስ አድርጎ ወደ ውስጥ ገባ ። የያሬድ መምጣት ከነበረባት ጭንቀት ገላገላት ። ያሬድ ፊት አብራቸው እንድትኖር እንደማይጠይቋት እርግጠኛ ነበረች ። ወ/ሮ አባይነሽ ግን ያሬድ ተስተካክሎ እስኪቀመጥ ጊዜ አልሰጡትም ።

« ያሬድ እባክህ ልጄ አንተን እሺ ትልሃለች ። ለምንልኝ ። እኔን እንቢ አለችኝ ። እንደዚህ ሆኜ እያያችሁ ምንም ቢሆን ሥጋዋ ነኝ ስሞት ማልቀሷ አይቀርም ። እባክህ ለምናት » ሲሉ ተማፀኑት።



መልሱን የሰጠው ያሬድ አልነበረም ። ሕሊና ከተቀመጠችበት ተነሳች ።

« አክስቴ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ልንገርዎት ። እኔ እዚህ ቤት ለመኖር አልፈልግም ። ወደፊት እየመጣሁ ልጠይቅዎት ፈልጌ ነበር ። ግን የዚህ ዓይነት የማይሆን ጥያቄ በማቅረብ የሚያለቅሱ ከሆነ ለወደፊቱም አልመጣም ። » አለችና ወደ ያሬድ ዞራ « ወደ ቤታችን እንሂድ እየመሸ ነው » አለችው ። ወ/ሮ አባይነሽ የሕሊና ንግግር ሆዳቸውን አባባው ። እንደ ልጅ እየነፈረቁ ለቅሶአቸውን ቀጠሉ ። ያሬድ ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ጠጋ ብሎ « ለበሽታዎ ጥሩ አይደልም አያልቅሱ ። » እያለ ሲያባብላቸው ሕሊና የመኝታ ቤቱን በር ከፍታ ወጣች ።

* * *

ሕሊና በወ/ሮ አባይነሽ እና በእርሷ መካከል ለብዙ ጊዜ የቆየውን ጥል በተፈጠረው እርቅ እንኳ ልትረሳ አልቻለችም ። ያሬድም ሕሊናን ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ቤት እንድትሄድ ማድረግ አልቻለም ። ማድረግ የቻለው ነገር ቢኖር በራሷ ጊዜ እንድትጠይቃቸው መተው ነበር ። ያም ቢሆን እንደማንኛውም የማይግባቡት የጎረቤት በሽተኛ ደርሳ ከመመለስ የረዘመ ጊዜ አትቆይም ። እንደዘመድ አታማክራቸውም ፣ አታፅናናቸውም ። አንድ ቀን ያሬድ ከሥራ ተመልሶ ወደ ቤት ሲገባ ሕሊና መጽሐፍ ስታገላብጥ አገኛት ።

ከተቀመጠችበት ቀና ብላ « እንደምን ዋልክ ጋሼ ያሬድ ? » ስትል ሠላምታዋን አቀረበች ።አፀፋውን መልሶ ፊት ለፊቷ በሚገኘው ወንበር ላይ አረፍ አለ ። በመካከላቸው የነበረው ታጠናበት የነበረው ጠረጴዛ ብቻ ነበር ። ሕሊና ያሬድ ፊት ላይ የጭንቀት ዳመና ጥሎበት አስተዋለች ። የሆነ ችግር እንዳለ ጠረጠረች ።

« ምን ሆነሃል ጋሼ ያሬድ ? » ስትል ጠየቀችው ::

« ሕሲና አሁን እኔ ወደ ሌላ ቦታ ብዘዋወር ምን ታደርጊያለሽ? » በማለት ጠየቃት ፣ ሲያምጥ ሲያምጥ ቆይቶ :: ፊቷን መለስ ቀለስ አድርጋ አካባቢዋን ቃኘችና « ምን ዓይነት ጥያቄ ነው ? ከአንተ ጋር እሄዳለሁዋ ! » ስትል ግራ በተጋባ ሁኔታ አየችው ::

ያሬድ እራሱን በአሉታ ነቀነቀ :: « ሕሲና . . እሱን አይደልም የምልሽ ፤ እንደ ድንገት እኔ የምሄድበት ቦታ ብቻዬን ከሆነ ማለቴ ነው » አለ ::

ሕሲና በድንጋጤ ያሬድን አፍጥጣ አየችው :: « እኔ አብሬህ እንድኖር አትፈልግም ማለት ነው ? በቃህ ? » በማለት የታችኛውን ከንፈሯን ጣል አደረገች :: « ታዲያ የት እሄዳለሁ ? » በሚል ዓይነት አስተዋለችው :: እሱ ግን እንዲህ የምትደነግጥ አልመሰለውም :: ከመቀመጫው ተነስቶ ወደ ሕሲና ዞሮ አንገቷን በሁለት እጆቹ አቀፋቸው :: « ሕሲና እንደእሱ ማለቴ አይደለም :: እኔ አንቺን በህይወቴ ለደቂቃ እንኳን እንድትለይኝ አልፈልግም » አለ እንባ ያቀረሩ ዓይኖችዋን በዓይኖቹ እያባበለ ::

« ሕሲና እኔ አንቺን በጣም . . . እናፍቅሻለሁ :: ሆኖም ሕሲና » ብሎ በአንድ እጁ አንገቷን አቅፎ እራሷን ወደ ራሱ አስጠጋ:: « ወደ ውጪ ለትምህርት መሄዬ ነው » አላት ሲፈራ ሲቸር ::

ሕሲና ይህን አልጠበቀችም ነበር :: ከዚህ ውጭ ሁሉም ነገር ቢሆን አያስገርማትም :: ግን እንደ ወንድም የምትወደውና ለችግሯ ሁሉ የምታማክረው ከማንም በላይ የራሷ የቅርብ ተጠሪ የሆነው ያሬድ ከአጠገቧ ይለያል ብላ አልማም አስባም አታውቅም :: ጉዳዩ ዱብ ዕዳ ነው የሆነባት :: የያሬድን እራስ እንደተደገፈች ዓይኖችዋ



የቋጠሩትን እንባ በዝምታ አነባች :: ለዚህ አስደንጋጭ ዜና አስተያየት ለመስጠት አልተዘጋጀችም ነበር ::

ያሬድ የሕሲናን ለቅሶ ሲመለከት የሚያደርገው ቅጡ ጠፋው:: ከኪሱ መሀረብ አውጥቶ በጉንጮችዋ ላይ የፈሰሰውን እንባ እያደረቀ « ገና እኮ ነው :: ነገ አይደለም የምሄደው :: ይልቁንስ እንደ ልጅ ከማልቀስ ዝም በይና እንዴት አድርገን ኑሮአችንን እንደምንመራ እንነጋገር » አለና ቀና አደረጋት ::

ለመጀመሪያ ጊዜ አባቷ ከተለያት ወዲህ በህይወቷ በእጆችዋ የወንድ አንገት አቀፈች :: እጆችዋን በአንገቱ ዙሪያ ጠምጥማ ፣ ፊቷን ጉያው ውስጥ ቀብራ « አትለየኝ ጋሼ ያሬድ ! አትለየኝ እባክህ! እኔ በህይወቴ የምወዳቸው ሁሉ ተለይተውኛል :: ከአንተ ሌላ ማን አለኝ? ጥለኸኝ አትሂድ » በማለት መወትወት ጀመረች ::

ያሬድ የሕሲናን ፀጉር በሁለት እጆቹ እያሻሸ ፊቷን ወደ አንገቱ ጠጋ አደረገና « አልሞትኩም እኮ እንዲህ የሚለቀሰው ለሞተ ሰው ነው :: » በማለት ሕሲናን አባበላት :: ብዙ ከነፈረቀች በኋላ አፍንጫዋንና ዓይኖችዋን እየጠራረገች ወደ መቀመጫዋ ተመለሰች :: ያሬድ በዚያች ደቂቃ ውስጥ የተፈጠረው ሁኔታ እስከወዲያኛው እንዲቀጥል ምኞት ነበረው :: የሕሲናን ለቅሶ ግን ሊቋቋመው አልቻለም :: ሳሎን ውስጥ ጥሏት መኝታ ክፍሉ ገብቶ ልብሱን ማወላለቅ ያዘ :: ሕሲና ግን ብቻዋን ሳሎን ውስጥ መቆየቱ አስፈራት:: ያሬድ አሁኑኑ ከአጠገቧ የሚሰወር መሰላት :: መለየቷን ስታስበው ደግሞ ፈለገችው :: በሩን በርግዳ መኝታ ክፍሉ ገባች :: ያሬድ ደንግጦ አልጋው ላይ ዘፍ አለ :: እርቃኑ ስጋውን ነበር ::

« ሕሲና ምን ነካሽ ? ልብሴን ሳለብስ ? » አላት በቁጣ መልክ ::

« ልበስ አላይህም » አለችው ፊቷን አዙራ ። ያሬድ የስፖርት ቱታውን ሱሪ የሩጫ ያህል ካጠለቀ በኋላ ዘና ባለ አነጋገር « አሁን ማየት ትችያለሽ » አላት ፈገግ ብሎ ።

« ጋሼ ያሬድ ስላስደነገጥኩህ ይቅርታ አድርግልኝ ። ካንተ ጋራ ለመሆን ስለፈለግኩ ነው » አለች እሷም ፈገግ ብላ ። ፈገግታዋ ብቻ ሳይሆን ውበት በውበት ሆና ታየችው ። ውስጡ ታገለው ።

ሕሊና በሩን በርግዳ ወደ ያሬድ ክፍል ስትገባ ምንም ዕቅድ አልነበራትም ። ያሬድ ስለመለየት ካነሳበት ጊዜ አንስቶ የውስጥ ስሜቷን ለመግታት ያላትን ጊዜ ከእሱ ጋር ለማሳለፍ በመፈለጓ ነበር። ክፍሉ ውስጥ አልጋው ጫፍ ላይ አረፍ አለች ። ያሬድ ፣ ልቡ ውስጡ አታሞዋን እየደለቀች ፣ ሠውነቱ ሙቀት እያመነጨ ከጎንዋ ተቀመጠ ። ከወገቡ በላይ ዕርቃኑን ነበር። አያት፤ አየችው ፣ አፈረ ፣ ተያዩ ፤ የተፋፈሩ መሰሉ ። ያሬድ ካለበት ሁኔታ ማምለጥ ፈለገ ።

* * *

ያሬድ የሚጠጣውን ሻይ ተወት አድርጎ ሕሊና የምታደርገውን ይመለከታል ። ከረጢቷን ፈታ ፈታ አድርጋ ውስጡ የነበረውን መጥረቢያ ቀስ ብላ አወጣች ። ጠረጴዛ ላይ አስቀምጣ ፊቷን ወደ ያሬድ አዞረች ።

« እንግዲህ እኔና አንተ ልንለያይ ነው ። ሆኖም እንዳሰብከው የምንለያየው ለጥቂት ጊዜ ይሆናል ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ምን እንደምንሆን አናውቅም ። ስለዚህ . . . » ስትል እጆችዋን በመጥረቢያው እጀታ ላይ አሳርፋ « ለእኔ የዋልከው ውለታ በህይወቴ ከማንም ያልጠበቅሁትና የማላገኘው ነው ። ይህን ውለታህን



በገንዘብም በምንም የምመልሰው አይደለም ። አሁን ይህን መጥረቢያ ያወጣሁት የአንተን ውለታና የአባቴን ምክር ለማስታወስ ያህል ነው።

አባቴ እኔ እንድማር በህይወቱ የነበረው ምኞት ከፍተኛ ነበር። ሆኖም በአቅም ማነስ ምክንያት ምኞቱን ሳያሟላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ ። ይህ ምኞቱ ግን ዛሬ በአንተ ተሟልቷል ። እኔ ለእናት ለአባቴ ብቸኛ ልጃቸው ነኝ ። ወንድም አልነበረኝም ። የምወድህ ወንድሜ አንተ ነህ ። ምንም እንኳን አባቴ በህይወት ባይኖርም ምኞቱን እንዳሟላህለት ሁሉ የአንተም ምኞት እንዲሟላልህ በአባቴ ሥም ምኞቴን እገልጽልሃለሁ » ብላ ፈገግ አለችና ያሬድን ተመለከተችው ።

ያሬድ ይህን አነጋገር የጠበቀው ቢሆንም ከሕሊና አንደበት መስማት አልወደደም ። « ወንድሜ አንተ ነህ » የሚለው አባባል ስሜቱን ነው የጎዳው ። ለሱ ሕሊና እህቱ ልትሆን አትችልም ። እስከ ህይወቱ መጨረሻ በአንድ ጣሪያ ስር አብረው ኖረው እንክን የማይወጣለትን ፀባይዋንና ውበቷን ለራሱ ብቻ ለማድረግ ነበር የሚፈልገው ። ስሜቱን መግለፅ ባለመቻሉ እራሱን እየረገመ ፣

« ሕሊና ስለምኞትሽ በጣም ነው የማመሰግንሽ ፤ ተቀመጭ» አለና ጠረጴዛ ላይ ያስቀመጠችውን ሻይ የያዘውን ብርጭቆ ዞር ዞር እያደረገ አለተዋለው። ከጥቂት ጊዜ ዝምታ በኋላም ቀጠለ ፤

« ሕሊና እኔ ላንቺ ያደረግሁት ምንም የተለየ ነገር የለም ። ማንኛውም እውነተኛ ሰብአዊ ፍጡር ሊያደርገው የሚችል ነገር ነው። ሆኖም የአባትሽ ምኞት በእኔ ስለተፈፀመ በጣም ዕድለኛ ነኝ ። ፊትሽ ላይ ማድነቅ አይሁንብኝና የአባትሽን ምኞት ያሳካሽው በፅኑ እምነትሽ እና በጠንካራ ሞራልሽ ነው ። ለወደፊቱም በዚህ ዓላማሽ እንደምትቀጥይ ተስፋ አደርጋለሁ ። እኔ ከአጠገብሽ ስለይ ምንም እንኳን ብቻሽን ብትሆኚ ለሚያጋጥሙሽ ችግሮች ሁሉ ቀደም

ብለሽ የሰማሻቸውን የአባትሽን ምክር አስታውሺ » ብሎ ወደ መጥረቢያው ተመለከተ ::

« ሕሲና መማር የሚለው የአባትሽ አባባል በአጭሩ የሚያልቅ አይደለም :: በህይወታችን በምንኖርበት ጊዜ በዕድሜያችን ሁሉ ተፈፃሚነት ሲኖረው የሚገባ አባባል ነው :: ትምህርት አያልቅም :: በመሆኑም ምን ጊዜም የማያወላዳ ሀሳብ ሲገጥምሽ አባትሽን አስታውሺ » አላት :: ሕሲና የያሬድን ንግግር አንዴ ወደመጥረቢያው አንዴ ወደ ያሬድ እፈራርቃ እያየች በጥሞና አዳመጠችው ::

« እኔ በህይወቴ የምመኘው በድህነት እራሳቸውን ለማስተማር ያልበቁትን ወገኖቼን ተምሬ ለማስተማር ነው :: በዚህም የአባቴና የአንተ ምክር እስከአሁን እንደረዳኝ ሁሉ ለወደፊትም እንደሚረዳኝ እርግጠኛ ነኝ :: » ብላ መጥረቢያውን በሁለት እጆችዋ ከጠረጴዛው ላይ አንስታ በጥልቅ ስሜት አይታ መልሳ ወደ ከረጢቱ አስገባችው::



* * *

ወ/ሮ አባይነሽ ከህመማቸው አገገሙ :: የያሬድን ወደ ውጪ ሀገር መሄድ በእልልታ ነበር የተቀበሉት :: በስሙ ማግስት ሕሲናና ያሬድ በዚያው ሣምንት ምሳ እንዲጋበዙላቸው ጠሩአቸው :: ጥሪውን ሕሲና ለመጀመሪያ ጊዜ ለመቀበል አልፈለገችም ነበር :: ሆኖም በቅርቡ ከአጠገብዋ ለሚለየው ያሬድ ስትል ተቀበለች :: በቀጠሮው ቀን የክት ልብሳቸውን እንደለበሱ ወ/ሮ አባይነሽ ሳሎን ተቀምጠዋል፣ የነፍስ አባታቸውም ተገኝተዋል :: እነ ሕሲና ገና ወደ ሳሎን ሲገቡ ወ/ሮ አባይነሽ ትልቁ ፎቴ ወንበር ላይ ተቀምጠው የያሬድን ጉንጭ እንቀው እየሳሙ « እንኳን ደስ ያለህ !» ሲሉ ተቀበሏቸው ::

ምንም ቢደኸዩ ወ/ሮ አባይነሽ ለዚህ ጊዜ የሚሆን ማስተናገጃ መጠጥና ምግብ አላጡም :: እንደቀድሞው ለእሳቸው ተብሎ በአዋቂ የደለበ ጮማ በግ አይታረድ እንጂ ትንሽ ጠቦትም ብትሆን ደም መፍሰሱ አልቀረም :: ጠርሙስ ውስኪም ባይሆን አንድ ኡዞ አረቄና የተወሰነ ቢራ አልጠፋም :: ሆኖም ያሬድን ያስገረመው የመጀመሪያውን የእርቅ ድርድር የመሩት የወ/ሮ አባይነሽ የነፍስ አባት እንደ ወ/ሮ አበይነሽ ሁሉ ስጋቸው እርቆአቸው ፣ ግርማ ሞገሳቸው ተገፎ ፣እንደ ወተት ነጭ የነበረው ጋቢያቸው አድፎ . . . ማየቱ ነበር ::

ወ/ሮ አባይነሽ ከተቀመጡበት ተነስተው ወደ ጓዳ ሲገቡ ያሬድ በክፍሉ ውስጥ የነበረውን ዝምታ ለመስበር ፊት ለፊቱ በራሳቸው ሀሳብ ግንባራቸውን እጨማትረው ሽበት የወረረውን ፂማቸውን የሚያፍተለትሉትን « አባ ታዲያስ ኑሮ እንዴት ይዝዎታል ? » በማለት ለንግግር መንደርደሪያ የሚሆን ጥያቄ ጣል አደረገ :: እሳቸውም ከሀሳባቸው ጋር እያጉረመረሙ ትንሽ ዘግየት ካሉ በኋላ ፣

« የእኛ ኑሮ ምን ብሰኽው ፤ ኑሮ ጌታውን ይመስላል » አሉት ። ቀጥለውም « ምን ኑሮ ነው ? ልጅ በአባቱ ፤ ወንድም በወንድሙ ፤ እናት በልጅዋ ላይ ሲነሱ ። ይህን ምን ትለዋለህ ? የምፅአት ቀኑ እየተቃረበ ነው እንጂ እህ . . . ሀም. . . ሀም . . . እግዚዮ መሀረነ ክርስቶስ » ብለው ሁለት እጃቸውን ወደ ሠማይ ዘርግተው እራሳቸውን ወደ ኮርኒሱ አንጋጠጡ በልመና ዓይነት ።

ሁኔታቸውን በጥሞና ስትከታተል የነበረችው ሕሊና የሽማግሌው ንግግር ፈገግ አድርጓት ያሬድን አየችው ። እሱም ፈገግ ብሎ ነበር ። አንድ መሀከለኛ ዕድሜ ያለው ልጅ የእጅ ማስታጠቢያና ፎጣ ይዞ ከወ/ሮ አባይነሽ ኋላ እየተከተላቸው ወደ እነ ያሬድ ቀርቦ አስታጠባቸው ። ሁሉም ታጥበው ሲጨርሱ ካብትሽ በዝርግ ሰሀን ምግብ አቀረበች ። ወ/ሮ አባይነሽ « ብሉ እንግዲህ ቤት ያፈራውን መካፈል ነው » በማለት መጋበዝ ጀመሩ ።

« ታዲያ መቼ ነው መንገድህ ? » አሉ ወ/ሮ አባይነሽ ምግብ ተበልቶ አልቆ መጠጡ ከተጀመረ በኋላ ።

« እንግዲህ ገና ነው ። ብቻ በሚቀጥለው ሁለት ሣምንት ውስጥ ሳይሆን አይቀርም » አላቸው ።

« ምኑን ገና ሆነ ሁለት ሣምንትማ ነገም አይደል ? » አሉና ቀጠል አድርገው « ስንት ጊዜ ነው የምትቆየው ? » ሲሉ ጠየቁት። እሱም በፈገግታ « ብዙም አይደል ፤ አንድ አምስት ዓመት ያህል ነው የምቆየው » አላቸው በማቃለል ።

« እ . . . ! . . እ ! . . . እ . . . ! » አሉ ወ/ሮ አባይነሽ በማጋነን እራሳቸውን በሁለት እጃቸው ይዘው ።

« ይሄማ ዕድሜ ይፍታህ ነው ። ለመሆኑ ሀገሩ ሩቅ ነው ?» አሉት ።

« ሀገሩስ . . . አዎ ትንሽ ራቅ ይላል ፤ ምስራቅ ጀርመን ይባላል ። » አላቸው ።



ወ/ሮ አባይነሽ ትካዜ እንደገባው ሰው ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ቆዩና ወደ ሕሊና እያዩ « ታዲያ ሕሊና እስከዚያ የት ትቆያለች ? » ሲሉ ወደሚፈልጉት ነጥብ አመሩ ። ሕሊና ፊቷን ኮስተር አድርጋ ወደ ያሬድ እየተመለከተች በተቀመጠችበት መቁነጥነጥ ጀመረች ።

« ሕሊናማ እንደ ድሮዋ ተቀምጣ ትማራለች » አለ አጠር አድርጎ ።

« ገንዘቡስ አይቸግርም ? ገንዘቡስ ቢገኝ ሴት ልጅ ብቻዋን እንዴት አድርጋ ትወጣዋለች ? » አሉ ።

« ለዚህ ሁሉ ተነጋግረንበታል ። እኔ ውጭ በምቆይበት ጊዜ ደመወዜን እየተቀበለ ለሕሊና የሚያመጣላት ሀሰን የሚባለው ጓደኛዬ ተወክሏል » አለና እንደማሰብ ብሎ « ሕሊና ብቻዋን አትኖርም ። አንዲት ዘመድ የሆኑ ባልቴት አብረዋት እንዲኖሩ ተስማምተናል ። ከሚቀጥለው ሣምንት ጀምሮ ይመጣሉ » አላቸው ። ወ/ሮ አባይነሽ ያሬድ መርዶ ያረዳቸው ነበር የመሰላቸው ።

« ምነው በሞትኩት ! ካልጠፋ ዘመድ ባዕድ ለምን አስፈለገ ? የቤት ኪራይስ ካልጠፋ ቤት ለምን በነፃ ትገፈግፋላችሁ ? ይልቁንስ የሚሆነውን እናውራ ። እሷም ከሌላ ከማታውቀው ሰው ጋር አትኖርም ። ያም ቤት ምንም አያደርግላት ። እዚህ ትምጣና ከኔው ጋር ብትኖር ይሻላታል ። » አሉና « አይደለም ? » በሚል ዓይነት የነፍስ አባታቸውን አስተዋሉ ።

« እንዲያው እኮ ይገርማል ። . . . ለመቼ ነው እንግዲህ ዝምድናው ። ከአባይነሽ ወዲህ ለሷ የሚቀርብ ማነውና እንዲህ ወዲያ ወዲህ የምታደርጉት ነገሩን ። ኧረ ነውር ነው ፤ ስውስ ምን ይላል ? » ሲሉ አባ የነፍስ ልጃቸውን ሀሳብ በመደገፍ ተናገሩ ። ሕሊና ትዕግስቷን ጨርሳ ነበር ።

« ስለኑሮዬ የራሴ ምርጫ ነው ። እኔ ከአሁን በኋላ ቤት አለኝ ። ከማንም ጋር ተዳብዬ መኖር አልፈልግም ። በላይነሽን እቴቴም ያውቋቸዋል ። ለኔ ባዕድ አይደሉም ። ከማንም ዘመድ የበለጠ የሚሳሱልኝ እናቴ ናቸው ። » በማለት ቀስ ብላ በሰለሰለ አንደበት ተናገረች ።

ወ/ሮ አባይነሽ ቀደም ሲል የዚህ ዓይነቱ ንግግር ምን እንደሚያስከትል ስለአወቁ ሁኔታውን ለማረጋጋት « እንግዲህ እንደምርጫሽ ፤ ያበጀሁ መስሎኝ ነው » በማለት ግራና ቀኝ የተቀመጡትን ያሬድንና የነፍስ አባታቸውን ከቃኙ በኋላ ቀጠል አድርገው ፤

« ምን ትሆናለች ፤ ከእንግዲህ እንጠያየቃለን ። » ብለው ቀደም ብሎ የነደደውን እሳት ለማቀዝቀዝ ፈለጉ ። ሕሊና እንደልማዷ ጥላ የምትሄድ መሰላቸው ። ዝምታው ለጥቂት ጊዜያት ሠፈነ ። ሁሉም የተግባቡ ይመስል ያሬድና ሕሊና ተሰናብተው ወጡ ።



# ምዕራፍ አራት

ያሬድ ከኢትዮጵያ ከለቀቀ ስድስተኛ ወሩን ያዘ ። ሕሊና በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራቶች በያሬድ ናፍቆት ክብደቷ ቀንሶ ነበር። ሆኖም አጠገቧ እንደ እናት በሚንከባከቧት በወ/ሮ በላይነሽ ፍቅር የስምንተኛ ክፍል ፈተናዋን በደህና ውጤት አልፋ ዘጠነኛ ክፍል ገብታለች ። በት/ቤት ውስጥ ባሉት የትርፍ ጊዜ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በመሳተፍ ጉልበቷንና ዕውቀቷን ሳትቆጥብ ትሠራለች ። በመሠረተ ትምህርት በተማሪ አስተማሪነት ያለማቋረጥ በከፍተኛ ፍላጎት በመሳተፍ መሀይምነትን ለማስወገድ ግንባር ቀደም ሆናለች ።

ሕሊና በየጊዜው ከሚደርሳት የያሬድ ደብዳቤ ፤ ስለጤንነቱና ስለሚማረው የትምህርት ዓይነት እንደዚሁም ስለምስራቅ ጀርመን ዕድገትና ብልፅግና ተረዳች ከያሬድ የሚደርሷትን ደብዳቤዎች ሁሉ አከማቸች ። አልፎ አልፎም ደብዳቤው ሲዘገይባት ከቀድሞ ደብዳቤዎችዋ የተወሰኑትን በመምረጥ ደጋግማ ታነባቸዋለች ።

ከደብዳቤዎቹ ጋር የሚልክላትን ፎቶግራፎች በቀድሞው መኝታ ቤቱ ፤ አሁን ከወ/ሮ በላይነሽ ጋር በሚተኙበት ክፍል ግድግዳ ላይ በሚያማምሩ ፍሬሞች ሰቅላቸዋለች ። ከያሬድ ደመወዝ የሚጠቀሙት አንድ መቶ ሃምሳ ብሩን ብቻ ነበር ። ሌላውን ቀሪ ሦስት መቶ ሰባ ብር ወደ ባንክ በመውሰድ ታስቀምጣለች ።

አንድ ቀን ሀሰን እንደተለመደው የያሬድን ደመወዝ ይዞ ወደ ቤት ሲመጣ ሕሊና ትምህርት ቤት በመሆንዋ ተቀምጦ መጠበቅ ግድ ሆነበት ። ጥቂት እንደጠበቀ ከት/ቤት ተመለሰች ። ገንዘቡን ቆጥሮ ካስረከባት በኋላ ስለያሬድ ወሬ አነሱ ። ሕሊና በቅርብ የላከላትን ፎቶግራፍ « እንዴት ወፍሯል መሰለህ ? » በማለት ለሀሰን

ሰጠችው ። ጉርድ ፎቶግራፉን ከሕሊና ተቀብሎ ጠጋ አድርጎ ተመለከተው ።

« በጣም አምሮበታል » በማለት መለሰላት ። ሕሊና የተቀበለችውን ፎቶግራፍ አየት አድርጋ በከንፈሮቿ እየሳመች በደረቷዋ ላይ ጥብቅ አድርጋ ለጥቂት ሰኮንዶች ያህል ያዘችው ። ሀሰን በዚህ አድራጎቷ በጣም ተገረመ ። የሕሊናንና የያሬድ ግንኙነት ምን እንደሆነ እራሱን እንዲጠይቅ አደረገው ።

ከያሬድ ጋር ለረጅም ጊዜ በነበረው ጓደኝነት ከሕሊና ጋር ስላለው ግንኙነት አጫውቶት አያውቅም ። የተለየ ጥርጣሬም አልነበረውም ። ይህ ድርጊቷ ግን አስቦት ወደማያውቀውና እንግዳ ወደሆነበት የጥርጣሬ ስሜት ከተተው ። በቀጥታ ሕሊናን ለማነጋገር ውስጡ ገፋፋው ። ሆኖም ወቅቱና ሁኔታው ስለማይፈቅድለት በዝምታ አለፈው ።

« በይ እንግዲህ ትምህርትሽን በርትተሽ አጥኚ ። ያሬድ ሲመጣ ደስ እንዲለው ከድሮው የክፍል ደረጃሽ ዝቅ ማለት የለብሽም» አለና ከተቀመጠበት ተነሳ ። ቀጥሎም « ሕሊና የሚቸግራችሁ ነገር አለ ? » ሲል ጠየቃት ።

« ሰጋሼ ያሬድ ስትጽፍለት ምንም ችግር እንደሌለብንና በሠላምና በደስታ የእሱን መምጣት እንደምንጠብቅ ፃፍለት ። » ስትል ችግር እንደሌለባቸው በተዘዋዋሪ ነገረችው። እየሳቀ ወጣ ። ወዲያው ማዕድቤት ሥራ ላይ ያሉትን ወ/ሮ በላይነሽን ጠርታ « እቴቴ በላይነሽ ይኸው የወር ወጪ » በማለት አንድ መቶ ሠላሳ ብር ቆጥራ ሰጠቻቸው ።

ወ/ሮ በላይነሽ ዕድሜ ቢጫጫናቸውም ከቀድሞው ሁኔታቸው ሻል ብለዋል ። በቤቱ ውስጥ የሚሠራውን ሥራ ብቻ ሳይሆን ለቤት የሚያስፈልገውን ጥሬ ዕቃ በርካሽ ዋጋ ከሚገኝበት ገበያ ሄደው ይገዛሉ ። ሕሊና የማዕድቤት ውስጥ ሥራ እንድትነካ



አይፈቅዱላትም። እምቢ ብትል እንኳን ለይምሰል ያህል ስሀንና ብርጭቆ ማጠብ እንጂ ከጥላሸት ጋር ንኪኪነት ያለውን ሥራ ሁሉ የሚሰሩት ወ/ሮ በላይነሽ ነበሩ ። እራት በልተው ከጨረሱ በኋላ ወ/ሮ በላይነሽ ቡና አፍልተው የኩቻን እናት ጠርተው ከዚያም ከዚህም ያገኙትንና የመሰላቸውን ወሬ ተወራውረው መለያየት ልማዳቸው ነበር ።

ሕሊና ደግሞ ከእራት በኋላ ትምህርቷንና ጥናትዋን ትቀጥላለች ። የሕሊና በዕድሜ መብሰል ፣ በትምህርት መግፋት ለወ/ሮ በላይነሽ ደስታን ቢያጎናጽፏቸውም አዕምሮአቸውን የሚከነክናቸው ጥያቄ ግን አልጠፋም ።

አንድ ቀን ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ ምሽት ወ/ሮ በላይነሽ ቡና አፍልተው ፣ የኩቻ እናት ደግሞ ዘመድ ለመጠየቅ በመሄዳቸው ብቻቸውን ቡና እንዳይጠጡ ሲሉ ሕሊናን አስቸገሯት ። ሕሊናም ፍላጎታቸውን ለማሟላት ስትል ለይምሰል ያህል አንድ ሲኒ ቡና ተቀብላ ፊቷ አስቀምጣ ወሬ ጀመሩ ። ሣር ቢጤ እያገላበጡ በእናትነት ዓይን እያስተዋሉአት « ሕሊና . . . ልጄ ለምንድን ነው እስከአሁን ያልወሰድሽው ? » በማለት ጠየቋት ። ሕሊና በጥያቄው ግራ በመጋባት « እቴቴ በላይነሽ ምነው ምን አደረኩዎት ? የምን መውሰድ ነው ? » ስትል በድንጋጤ መለሰችላቸው ።

« አይ የልጅ ነገር ባል አግብቶ ዝም ብሎ መቀመጥ አለ ? ይህን የመሰለ ትዳር ለጥቶሽ በጊዜ ዱብ ዱብ አድርጎ ወንድምና እህት ማድረስ ነው » አሉ በቁምነገር ። ሕሊና ብብቷን የኮረኮሯዋትን ያህል ከት ብላ ሳቀች ።

« እቴቴ በላይነሽ ማነው እሱ ባሉ ? ከየት አመጡት ? » እንደገና ከልቧ ከት ብላ ሳቀች ።

« ምነው ሕሊና ! እኔን ነው የምትደብቂኝ ? » አሉና ጀበናውን ከምድጃው ላይ አነሱ ። ቅር ተሰኝተው ነበር ።

« አይ እቴቴ በላይነሽ ፤ አያውቁም ለካ . . . ያሬድን ነው የሚሉት ? እሱኮ ወንድሜ ነው » ብላ አፍጥጣ አየቻቸው ::

« ወንድምማ ከወንድም ይበልጣል :: ወንድም በሥጋ ? ማን ቢወልድ ማንን » አሉ ሽሙጥና መቀየም በተቀላቀለበት አነጋገር :: ሒሊና ከተቀመጠችበት ተንቀሳቀሰች :: የወ/ሮ በላይነሽን ጉልበት በሁለት እጆችዋ ተደግፋ « እቴቴ በላይነሽ መቼም ያውቃሉ :: በአባቴ ከማልኩ - የአባቴን ሥጋ ነው :: ጋሽ ያሬድ ለእኔ ንጹህ ወንድሜ ነው :: በእሱና በእኔ መሀከል የሴትና የወንድ ግንኙነት ቀርቶ አዝማሚያውም አልተፈጠረብን » ስትል ዓይን ዓይናቸውን አየች ::

« ታዲያ እሱስ ይሁንና እጮኛም የለሽ ? እንዲያው ለነገሩ » በማለት በመገረም እያዩ ጠየቋት ::

ሒሊና ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ « ምን ያደርግልኛል ? እኔ ከጋሼ ያሬድ ተለይቼ መኖር አልፈልግም :: ባል ፤ እጮኛ ለምን ብዬ ነው ? »

« የአንቺስ አፈጣጠር ለብቻው ነው :: ታዲያ ለምን ያሬድ ሲመሰስ አታገቢውም ? ለምን ሌላ ሰው ትፈልጊያለሽ ? እንደወንድምም እንደባልም ይሆንሻል :: ከእሱ የበለጠ ቁም ነገረኛ ሰው ከየትም አይገኝ » አሏት ::

« እቴቴ በላይነሽ ጋሼ ያሬድ ለእኔ እንደ እናቴ ልጅ ነው :: እንደባል ወይም እንደ ሌላ ባዕድ ወንድ ላየው አልፈልግም :: ባልና ሚስት ይጣላሉ :: አልፎ አልፎም ይደባደባሉ :: እኔ ለጋሼ ያሬድ ያለኝ መወደድ ልክ የአባቴን ያህል ነው :: ፊቱን ሳየው እንደ አንድ የእናት የአባቴ ልጅ ነው የምንሰፈሰፈው :: ስለዚህ ለእሱ ያለኝን መውደድ ባል ብዬ ለማገባው ሰው አይኖረኝም :: » አለችና እንባቷን አቀረቀረች ::

« እኛ በልጅነታችን ስንዳር ባሎቻችንን ወንድሞቻችሁ ናቸው እየተባልን ለብዙ ጊዜ ምንም ሳናውቅ አብረን ተቀምጠን ነው በኋላ



ባል መሆኑን የምናውቀው :: ብታገቢው ፍቅራችሁ የበለጠ ይጨምራል እንጂ ምን ይቀንሰዋል ? በወንድም ፍቅር ላይ የባልነት ፍቅር ሲጨመርበት የበለጠ መውደድ ያመጣል :: ይልቅስ ሞኝ አትሁኚ » አሉዋት ::

ሒሊና ሁሉንም ካዳመጠች በኋላ አጠገብዋ ያለውን ወንበር ሳብ አድርጋ ተቀመጠችና « ለርስዎ መሰለዎት እንጂ እኔ የሥጋ ወንድሜን የማገባ ያህል ነው የምቆጥረው ፤ ጋሼ ያሬድን ማግባት :: ደሞስ ጋሼ ያሬድ እኔን እንደ እህቱ ሲቆጥረኝና ሲሳሳልኝ ሚስት ካልሆንኩ ብዬ የምረክሰው በእኔ ላይ ያለውን እምነት ዝቅ ማድረግ አይሆንም ? » በማለት እየዘገነናት « እቴቴ በላይነሽ እንዳልቀየምዎት ሁለተኛ የዚህ ዓይነቱን ሀሳብ እንዳይደግሙብኝ » ስትል በልመና ዓይነት አስጠነቀቀቻቸው ::

* * *

ሒሊና ሳሎን ተቀምጣ አዲስ የደረሳትን ደብዳቤ እንባዋን ከዓይኖችዋ በመሀረብ እየጠራረገች አንብባ እንደጨረሰች ፊት ለፊቷ የተሰቀለውን የያሬድን ፎቶግራፍ ትክ ብላ አስተዋለች :: ዓይኖችዋን ከያሬድ ፎቶግራፍ ላይ ሳትነቅል በደብዳቤው ውስጥ ስላለፈረው ፅሁፍ አሰመች :: የጤንነቱን ሁኔታ በአጭሩ ካለፈረ በኋላ ያሬድ ሲመለስ ቤት ኖሮት ትዳር እንደሚመሰርትና ልጆቹን ለመንከባከብ ያለውን ፍላጎት ነበር በደብዳቤው የገለጸላት :: በሀሳብ ደብዳቤውን ደግማ አነበበችው ::

*ባለፈው ሳምንት የፈረንጅ ጓደኛዬ የሆነው ቶማስ ቤት ነበር ቅዳሜና እሁድን ያሳለፍኩት :: ባለትዳር እና የሁለት ልጆች አባት ሲሆን እሱና ቤተሰቦቹ በኑሮአቸው በጣም ደስተኞች ናቸው ::*

*አባትና እናቱ ጡረተኞች ሲሆኑ ባለቤቱ የምትኖረው በዚሁ ቤተሰቦቹ በሚኖሩበት ግቢ ቶማስ በሰራው ትልቅ ቤት ውስጥ ነው ። የቶማስና የባለቤቱ ፍቅር እና መተሳሰብ እንዲሁም ለልጆቻቸው ያላቸው ፍቅር ፍፁማዊ ነው ብል አልተሳሳትኩም። ታዲያ እነዚህን ደስተኛ ቤተሰቦች ሳይ ነው የእኔ የትዳር ወኔዬ የበለጠ በውስጤ ያንሰራራው ። ሒሊና ወደ ሀገሬ እንደተመለስኩ ሌላ ምንም ምኞት የለኝም ። ትዳር መስርቼ እንደቶማስ ያለውን ቤተሰብ ከማፍራት በስተቀር ። ወደ ሀገሬ ለመመለስ በጣም ነው የቸኮልኩት ። የተማርኩትን በሥራ ተርጉሜ ሀገሬ ካለችበት የድህነት አዘቅት ለማውጣትና የራሴን ህይወት ለመምራት ነው ። ሒሊና በዚያች የደሀ ጠረጴዛችን ፊት ለፊት ሁለታችን ብቻ ተቀምጠን አሁን ስለምልሽ ነገር ብናወራ ምንኛ በረካሁ ። ዳሩ ምን ያደርጋል ለማውራት የምፈልገውን በዓለም ላይ ያሉትን ወረቀቶችና ብዕሮች ባስተባብር ዓይን ለዓይን ተያይተን ከምናወራው የሚሰማኝን ስሜት ያህል አያረኩኝም ።*

*ለማንኛውም በርትተሽ ተማሪ ። ለሁሉም እንደርሳለን ። ወደ ሀገሬ ስመለስ ስለሁሉም ነገር አጫውትሻለሁ አንቺን ካልሰለቸሽ ። ለእማማ በላይነሽ የከበረ ሰላምታዬን አቅርቢልኝ ።*

*ያንቺው ያሬድ ።*



ሒሊና ደብዳቤውን አንብባ እንደጨረሰች ብዙም ሳትቆይ ወ/ሮ በላይነሽ ሳታስበው ከማዕድቤት የጓዳውን በር ከፍተው ገቡ ። ሒሊና የነበረችበትን ሁኔታ ከወ/ሮ በላይነሽ መሸሸግ አልቻለችም ። በርበሬ የመሰለው ዓይኗን ደም የለበሰው ጉንጯ ማልቀሷን በግልፅ ያሳዩ ነበር። ወ/ሮ በላይነሽ ምንም እንዳላዩ ሆነው የፊት ለፊቱን በር ገርበብ አድርገው ዘጉና ሒሊና አጠገብ ወንበር ጎተት አድርገው ተቀመጡ ። ፊቷን በሁለት እጃቸው ቀና አድርገው በእናትነት ዓይን ከላይ እስከታች እየተመለከቷት ፤

« ምን ነካሽ ሒሊና ? ምነው ተከፋሽ ? » በማለት ለስለስ ባለ ድምጻቸው ጠየቋት ።

ሒሊና ለወ/ሮ በላይነሽ ጥያቄ መልስ መስጠት አልቻለችም ። አንገቷን ወደመሬት አቀርቅራ ዝም አለች ። ሁኔታው ሠላም የነሳቸው ወ/ሮ በላይነሽም አጠገባቸው ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን ደብዳቤ በእጃቸው አገላብጠው አዩት ፤ ትርጉም ሊሰጣቸው አልቻለም። እንደገና ወደ ሒሊና ፊታቸውን መልሰው « ለመናገር አልፈለግሽም ? » በማለት ስሜቷን ላለመጉዳት ብድግ አሉ ።

« እቴቴ በላይነሽ ይቀመጡ ፤ ልንገርዎት ። » አለቻቸው እንዳያመልጧት እጃቸውን ይዛ ፤ ቀና ብላ እያየቻቸው ተቀመጡ አለቻቸው ።

ሒሊና የወ/ሮ በላይነሽን ፊት ለማየት አልደፈረችም ። ጆርባዋን ሰጠቻቸውና « እቴቴ በላይነሽ አይታዘቡኝ ። በጣም ከሚወዱት ሰው አብረው ለመኖር እየፈለጉ ሊለይዎት ምን ይሰማዎታል ? » ስትል ጠየቀቻቸው ። እሳቸውም የገባቸው ይመስል ሁኔታውን እንደቀላል በመውሰድ « ምን ታደርጊያለሽ ለመጀመሪያ ጊዜ ከባድ ነው ። ውሎ አድሮ ግን እየተረሳ ያልፋል ። እንኳን በህይወት ያለውን ቀርቶ የሞቱትስ ይረሱ የለ ? » በማለት ጥያቄዋን ቀለል አድርገው መለሱላት ።

ሰው ከሞተ ሞተ ነው ። ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መቃብር ሲገባ ይሰናበቱታል ። ሆኖም እየኖረ የሚለዩት ፣ የሚወዱት ሰው በየጊዜው ባዩት ቁጥር ምኞትዎ እየታደሰ ይሄዳል ። ይህ የቁም ስቃይ አይደለም ? » አለቻቸው ።

« እሱስ እንግዲህ እንደባለቤቱ ነው ። ሆኖም የሰው ዕድሜ የማይፍቀው ክፉ ነገር አይገኝም ። ለጊዜው ይመስላል እንጂ መውደድስ ባታውቂው ነው እንጂ ከዕድሜ ጋር እየከሰመ ይመጣ የለ» አሏት ።

« እንዴት አድርጌ ልንገርዎት ? እም . . . ም . . . » ብላ ጥቂት ካመነታች በኋላ « ጋሼ ያሬድ ደብዳቤ ፅፎ ነበር ። በደብዳቤው ላይ ወደዚህ እንደተመለሰ እንደሚያገባ ነገረኝ ። ይሄ ማለት ደግሞ እሱ ካገባ እኔ አብሬው ለመኖር አልችልም ከእርሱ ጋር አብሬው ለመኖር ደግሞ በጣም እፈልጋለሁ » በማለት ጮክ ብላ ድምጿን በማሰማት ተንሰቅስቃ ማልቀስ ጀመረች ።

ወ/ሮ በላይነሽ የሕሊናን ፊት ቀስ ብለው ወደራሳቸው አዙረው እቅፋቸው ውስጥ አስገብተው ጀርባዋን እንደ ሕፃን ልጅ መታ መታ እያደረጉ « አልቅሺ ፣ በማልቀስ ክፉ ነገር ይወጣል ይባላል » ሲሉ አባበሏት ። ሕሊና ለቅሶዋን ከጨረሰች በኋላ እንደ ትንሽ ልጅ እየተነፋነፈች « ምን አለበት ሳላውቀው ብቀር ኖሮ ። ባልማርስ ቢቀር ። ወይ ክፉ ነገር ሰርቶብኝ እንድጠላው ቢያደርገኝ » በማለት እንባዋን ከፊቷ ጠራረገች ።

« ክፉ ለመሥራት መጀመሪያውኑ ክፋትን መልመድ ያስፈልጋል ሕሊና ። ክፋትን ያለመደ ክፉ ነገር ልስራ ቢል ዩግነት ነው የሚሆንበት ። » አሉና « ሕሊና ለመሆኑ ሲፅፍ ማንን እንደሚያገባ ጠቅሷል ? » በማለት በጥርጣሬ ዓይን ተመለከቷት ። ትንሽ አሰብ አድርጋ « እሱን አልጠቀሰም ። ገና በሀሳቡ ብቻ ነው ለማግባት እንደሚፈልግ የገለፀልኝ » አለቻቸው ።



« ታዲያ አንችንስ ላግባ ቢል ምን ይታወቃል ? » ሲሉ ዓይናቸውን ከፈቱ ። ከአንገቷ ቀና ብላ ወ/ሮ በላይነሽን በክፉ ዓይኖቿ ቃኘቻቸው ። ለዚህ ጥያቄ መልስ አልሰጠችም ። ወ/ሮ በላይነሽ ከዚህ ቀደም የተባባሉት ትዝ አላቸውና ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው « እንግዲህ ጊዜ ይፈታዋል » አሉና ሕሊናን ሸሽት ተነስተው ወደ ማዕድቤት ሄዱ ። ሕሊና ጠረጴዛ ላይ ያስቀመጠችውን ደብዳቤ አነሳች ።

*        *        *

ወ/ሮ አባይነሽ መጠጥና መኝታ ቤቱን በኮንትራት ለሌላ ሰው አሳልፈው በመስጠት በየወሩ የተወሰነ ኪራይ ማግኘት ጀምረዋል። ይህም እንደቀድሞው የተትረፈረፈ የቅንጦት ኑሮ እንዲኖሩ ባያደርጋቸውም በቂ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል ። ሕሊና ለያሬድ ስትል አልፎ አልፎ ከወ/ሮ በላይነሽ ጋር በመሆን ትጠይቃቸዋለች ።

እሷም ወ/ሮ አባይነሽ የሚጠይቁትን ሁሉ ማሟላት እንደማትፈልግ ብትነግራቸውም ወደ ቤታቸው በሄደች ቁጥር አዳዲስ ሀሳቦችን ማፍለቃቸውን አልተውም ። በተለይ አንድ ቀን ልትጠይቃቸው ወደቤታቸው የሄደች ዕለት ከአንድ ሰው ጋር እንድትተዋወቅ ሲለምኗት በግዴለሽነት እራሷን አስተዋወቀች ። ሆኖም ትውውቁ ይህን ያህል ወ/ሮ አባይነሽን እንዲያስቡበት ያደረጋቸው ምክንያት አልገባትም ። ቀደም ባሉት ቀናት ስለ እድገቷ እንዳሰቡ ሁሉ « እንግዲህ በስለሻል ማለት ነው ። ምንም ቢሆን ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ ። እኛ በልጅነታችን ትዳር አንፈልግም ብለን ሀብት ንብረት ስንጋፍፍ ሜዳ ላይ ቆመን ቀረን ። » እያሉ የራሳቸውን ሁኔታ ከሕሊና ጋር ለማዛመድ ይሞክሩ ነበር ። በዚህ

አድራጎታቸው ሁለተኛ ቤታቸው አካባቢ ላለመድረስ ወስና ነበር ። ነገር ግን ያሬድ በደብዳቤው አደራ ስለማያበዛባት አደራውን በቸልተኝነት ማለፍ እንደማትችል ተገነዘበች ። ከተጋደመችበት አልጋ ብድግ አለችና « እቴቴ በላይነሽ » ብላ ተጣራች ። ወ/ሮ በላይነሽ ኩሽና ውስጥ እንጀራ እየጋገሩ ስለነበር ለአንድ አፍታ ወደ ዋናው ቤት ብቅ አሉና ፣

« ጠራሽኝ ሕሊና ? » ሲሉ ጠየቋት ።

« እቴቴ በላይነሽ አልጨረሱም ? አንድ ነገር ልነግርዎት ነበር» አለቻቸው ።

« አንድ ጊዜ ፤ የመጨረሻ እንጀራ ነው ያሰፋሁት ተመልሼ መጣሁ ። » ብለዋት የስራ ቀሚሳቸውን ከወገባቸው አካባቢ እያስተካከሉ ወደ ማዕድቤት ተመለሱ ።

ወ/ሮ በላይነሽ ሥራቸውን ጨርሰው ከተጣጠቡ በኋላ ሕሊና ወዳለችበት ክፍል ገብተው « አሁንም ትንሽ ቆይኝ » ብለው የሥራ ልብሳቸውን አወላልቀው ነጣ ያለ የአበሻ ቀሚስ መልበስ ሲጀምሩ ሕሊና ቀና ብላ ፣

« እቴቴ በላይነሽ አዲሱን ልብስዎትን ይልበሱ » አለቻቸው በሁለት እጆችዋ አቅፋቸው እንደመላፋት እያለች ። የአበሻ ልብሳቸውን በእጃቸው እንጠልጥለው « አሞሻል ? ምን ነካሽ ? » በማለት ፈገግ አሉ ።

« እቴቴ በላይነሽ ያሬድኮ ደብዳቤ ፃፈ ። » ብላ እየሳቀች ዓይን ዓይናቸውን አስተዋለች ። እሳቸው ቀደም ሲል ሊለብሱት የሞከሩትን ቀሚስ እንደገና እያጠለቁ « ለዚህ ነው አዲስ ልብስ ለበሺ የምትይኝ ? » አሏት ቀሚሳቸውን እያጠለቁ ።

« ጋሼ ያሬድ እቴቴን እንድንጠይቃቸው ስለፃፈልኝ አንድ አፍታ ደረስ ብለን እንድንመለስ ነው » አለች ።



« ምን አለ እንቺ ብቻሽን ብትሄጂ ? እዚያ ቤት መሄድ በጣም ነው የምጠላው » አሉ ።

« እይ እቴቴ በላይነሽ እኔን ደግሞ ከእርሶ ይበልጥ ነው የሚያስጠላኝ ። እንደዚሁ ቃሉን ለመሙላት ያህል ደረስ ብለን እንምጣ ብዬ ነው እንጂ » አለቻቸው ። ሕሊናና ወ/ሮ በላይነሽ ተያይዘው በራቸውን ዘጉና ወደ ወ/ሮ አባይነሽ ቤት አመሩ ።

የሾፌሮች ቡና ቤት የቀድሞ መልኩን መልሶ ተጎናጽፏል ። በአካባቢው ብዛት ያለው ሰው ውር ውር ይላል ። በውስጡም ብዛት ያላቸው ሠራተኞች ከወዲያ ወዲህ እያሉ ደንበኞቻቸውን ያስተናግዳሉ። ሕሊናና ወ/ሮ በላይነሽ በግቢው በር በኩል ገብተው ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲያመሩ ሕሊና ግራና ቀኝ ተመለከተች ።

መኝታ ቤቱ ታድሷል ። ወደ ቤት ሲገቡ ወ/ሮ አባይነሽ ብቻቸውን አልነበሩም ። አብረዋቸው በእሳቸው ዕድሜ የሚገኙ አንዲት አዛውንት ሴት ነበሩ ። ወ/ሮ አባይነሽ ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው እነ ሕሊናን በመሳም ከተቀበሉአቸው በኋላ ሕሊናና ወ/ሮ በላይነሽ ፎቴ ወንበር ላይ ቦታ ቦታቸውን ይዘው ተቀመጡ ።

« አያውቋትም እንዴ ? ይህች ነች እኮ የእህቴ ልጅ » በማለት ወደ ሕሊና እየተመለከቱ አዲሷን አዛውንት ሴት ከሕሊና ጋር በማስተዋወቅ « ሕሊና ነይ ሳሚያቸው ። የክፉ ቀን ጓደኛዬ ናቸው » አሉ ። ሕሊና ከመቀመጫዋ ተነስታ አዛውንቷን ሳመቻቸው። አዛውንቷም « ቆንጆ ልጅ አለዎት ። » በማለት የሕሊናን ውበት በማድነቅ ተናገሩ ።

« ምን ያደርጋል ። ታዲያ ይኸው አላገባም ብላ አሸንፋለች » በማለት ፈገግ ብለው ሕሊናን አስተዋሉአት ።

« ምነው ! ወ/ሮ አባይነሽ እስከአሁን ምን ነካዎት ? » አሉ አዛውንቷ ።

« ይሄ መከረኛ ትምህርት የሚባል ዘመን አመጣሽ አለ ። እማራስሁ ብላ እምቢ አለች ። » ሒሲና በሀፍረትና በንዴት ውስጧ ተቃጠለ ። ነገር ለመሸሽ ስትል ራሷን ለመቆጣጠር ታገለች ።

ወ/ሮ አባይነሽ ከጥቂት ዝምታ በኋላ ንግግራቸውን ቀጠሉ ፤ « በከተማው ያሉ የጨዋ ሰው ልጆች ፤ ሀብታም ነጋዴዎች እየመጡ ያስቸግሩኛል ። ይኸው ባለፈው ሰሞን የአቶ ጌታሁን ልጅ ማነው ስሙ . . . አዎ ! አለፈ ካላስተዋወቅሽኝ ብሎ ቁም ስቃዬን ሲያሳየኝ፤ እንግዲህ በሀገሩ ደንብ በሽማግሌ ይሁን ብለን ተስማምተን እንዲያው ዳር ዳሩን ስንነግራት ጊዜ እመቤቲቷ ከነጭራሹ አኩርፋ እኔን ለመጠየቅ እኳን አሻፈረኝ ብላ ቀረች » አሉ ።

ሒሲና ከዚህ በላይ ስሜቷን መቋቋም አልቻለችም ። « ለነገሩ የማገባውን ለመምረጥ ህግ የሚፈቅድልኝ ይመስለኛል ። ሆኖም አክስቴ ያልገባዎት ነገር አለ ። ከሁሉም በፊት እራስን ማወቁ ይቀድማል ። እኔ ትምህርቴን ሳልጨርስ ለግርድና ባል አላገባም ። ባገባም ቢጤዬን እንጂ ለገንዘብ ብዬ ባርነት አልገባም ። አክስቴ እውነት ትመራለች ። ነገር ግን ሀቅ መናገሩ ከሺ ውሸት የበለጠ ያረካኛል ። የእርስዎ ሀብት ከራስዎ ተርፎ ሰው ያስተዳድር ነበር ። ያ ሀብት ሲታመሙና ዕርዳታ ሲፈልጉ እየመነመነ መጣ ። በመጨረሻም አሁን ካለንበት ደረጃ አደረሰዎት ። አክስቴ ሁሉም ሀብት ያለው ከዚህ የተለየ አይደለም ። የማይሰረቅ ፤ የማይዘረፍ ፤ የማይመነምንና የማይነጥፍ ዘለዓለማዊ ሀብት ትምህርት ነው ። ትምህርት የራስን የዕውቀት አድማስ እያሰፋ ሀገርን ያበለጽጋል ። ወገንን ከድህነት ያወጣል ። ትምህርት እራሱ የብልጽግና ምንጭ እንደመሆኑ መጠን ሀብትን ያፈራል ። ስለዚህ አይሳሳቱ ። . . . ደግሞ እኔ እራሴ ነኝ ለራሴ ህይወት ወሳኝ ። በመሆኑም ከዛሬ ጀምሮ በእኔ ሥም ማንንም ቢሆን ሰባልነት ወይም ለመተዋወቅ እንዲነጋገሩ አልፈቅድልዎትም ። አሁንም ለመምጣት አልፈለኩም



ነበር ። ለጋሼ ያሬድ ስል ነበር አመጣጡ ። ነገር ግን ከእንግዲህ ወዲህ ሌላ እርቅ አይኖርም ። እኔ የእርስዎ የእህት ልጅ አይደለሁም ። እርስዎም ለእኔ አክስቴ አይደሉም ። ከዛሬ ጀምሮ እዚህ ደጃፍዎ ላልገኝ ቃል እገባልዎታለሁ » ብላ ከተቀመጠችበት ተነስታ ወ/ሮ በላይነሽን ሳትጠብቅ ወጥታ እየበረረች ወደ ቤቷ ሄደች ።

* * *

ወ/ሮ በላይነሽ ሒሲና መኝታ ቤቷ ውስጥ ገብታ ነበር የደረሱት ። መኝታ ቤት ገብተው ሒሲናን ካዩዋት በኋላ ለጥቂት ጊዜያት ባሉበት ቆመው በዝምታ አስተዋሉአት ። እሷም ንዴቷ ስላልበረደላት ለመናገር አልቃጣችም ። በዝምታ አልፋቸው ወደ ሳሎን በመሄድ በመጽሐፍ መደርደሪያ ካሉት መጽሐፍት አንዱን ወጣ አድርጋ ገለጠች ። መጽሐፉን ታያለች እንጂ እያነበበችው አልነበረም ። የገለጠችውን መጽሐፍ አትኩራ እየተመሰከተች የምታስበው ቀደም ሲል ስለፈጸመችው ድርጊት ነበር ። በአንድ በኩል በታላላቆችዋ ፊት ያን ንግግር ማድረግዋ ቢቆጫትም በሌላ በኩል በወ/ሮ አባይነሽ ላይ በወሰደችው እርምጃ ረካች ። ወ/ሮ በላይነሽ ከመኝታ ክፍላቸው ወጥተው ሒሲና አጠገብ ሄደው በመቀመጥ በዝምታ ተመለከቷት ። እሷም መጽሐፍዋን እየተመለከተች ትንሽ ከቆየች በኋላ ያለበት ሁኔታ ስለከበዳት በንግግር ለማቃለል ያህል « አጠፋሁ እንዴ እቴቴ በላይነሽ ? » በማለት ጠየቀቻቸው ።

ወ/ሮ በላይነሽ እራሳቸውን በአሉታ እየነቀነቁ ፤ በሀዘን ዓይን በመመልከት « ደግም አይደል ልጄ ታላላቆችሽን መግፋት » አሏት ።

« ምኑን ገፋኋቸው ? ገፉኝ እንጂ ። ከመቼ ወዲህ ነው እሳቸው የእኔን ደህንነት ፈላጊ ሆነው ትዳር ሲመሰርቱልኝ ያሰቡት ?

እንዲያው ለራሳቸው ብለው ነው እንጂ ነጋዴ አጋብተው የራሳቸውን ንግድ በጎን ለማቀላጠፍ ። ለውማ ቢሆኑ ኖሮ የኔን ትምህርት ከማጥላላትና በህይወቴ ምንም እንዳልሰራሁ ከመቁጠር አይዞሽ ፣ በርቺ ፣ ተማሪ ፣ አይሉኝም ? እሳቸው ዕድሜያቸውን በተንኮል የጨረሱ ምንጊዜም ቢሆን ሰውን ከመተናኮል ወደኋላ አይሉም። ከማን ቢቆጥሩኝ ነው ከእከሌ ነጋዴ ጋር አስተዋውቅሻለሁ ሀብታም ነው የሚሉት ? » በማለት ቁጣዋን እንደገና ለወ/ሮ በላይነሽ ለመግለጽ ሞከረች ።

« ለምን በክፉ ታስቢዋለሽ ልጄ ! እሳቸው ለአንቺ ደግ ለመዋል ብለው ይሆናል ። የአንቺን ሀሳብ የት አወቁ ? » በማለት ለማብረድ ሞከሩ ።

ሒሊና በንዴት ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ተነሳችና « የት ያውቃሉ የእሳቸውን ዘዴ ? እቴቴ በላይነሽ ! » አለች ድምጿን ዘለግ አድርጋ ። « እሳቸው የብዙ መጥፎ ቋሪክ ክምችት ናቸው ። በእሳቸው ዘንድ ደግነትና ሀቀኝነት ቦታ የላቸውም ። እንግዲህ የዛሬውን እርእስታቸውን ላብራራልዎት ። « አስፋ » የሚሉት እውነትም የሀብታም ነጋዴ ልጅ ነው ። ተወልዶ ያደገው እዚሁ አቃቂ ነው ። አሁን ትምህርት አንቢ ብሎ ከዘጠነኛ ክፍል ኮብልሎ በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቷል ። ይህ አስፋ የተባለው ከት/ቤታችን እንኳን ሁለት ሴት ልጆችን አገባችኋለሁ በማለት ከትምህርታቸው አሰናክሎአቸዋል ። አሁን የት እንዳሉ አይታወቅም ። አንደኛዋን ልጅ አውቃታለሁ ። ከዚሁ ከገጠር ነው የምትመጣው ።

« የአንድ ገበሬ ልጅ ነች ። በትምህርቷ ጎበዝ ነበረች ። ነገር ግን ምን ያደርጋል ፣ የዕድል ነገር ሆኖ ከዚህ ከአልባሌ ሰው ጋር አጋጠማት ። እንዲሁ በአንዳንድ ብርቅርቅ ነገሮች በመደለል ይዟት አሸሸ ገዳሜ ሲል ከረመና ልጅቱ እንደድንገት ስታረግዝ አባትነቱን ይክድና ዘወር በይ አላት ። ከቀን ወደ ቀን ሆዷ እየገፋ ሲመጣ ልጅቱ



ትምህርቷን ለማቋረጥ ተገደደች ። በመጨረሻም ከነአካቴው ሀገር ጥላ ሸሸች ። እንግዲህ ይህን ሰው ነው የጨዋ ልጅ ፣ ሀብታም ነጋዴ እያሉ ሊያጋቡኝ ያዘጋጁልኝ ። »

« ታዲያ አክስትሽ ይህን ሁሉ የት ያውቃሉ ብለሽ ነው ? እሳቸው የሚያውቁት አባትየውን » ሲሉ ሊሞግቷት ሞከሩ ።

« አይ እቴቴ በላይነሽ ! ስለዚህ ልጅ አብጠርጥረው ነው የሚያውቁት ። ሆኖም እሳቸው ምን ቸገራቸው አገባሁ ብሎ የእኔን ዕድል አበላሽቶ ቢተወኝ ። መሄጃ የሌለኝ እንደገና ወደ እሳቸው ቤት ገብቼ መጫወቻቸው ለማድረግ ነው እቅዳቸው ። እንዲያውም እኔን ጥሩ ትዳር ሊመሰርት ከሚችል ሰው ጋር እንድጋባም አይፈልጉም ። ምክንያቱም ከጥሩ ሰው ትርፍ አያገኙበትም ። እሳቸው ሁለንተናቸው የተመሠረተው በመቸርቸር ላይ ነው ።ህይወታቸውስ የተመሠረተው እንካ አትርፈህ አምጣ በሚለው ዘይቤ አይደል ! » ስትል እያንገሸገሻት ተናገረች ።

« እሺ ! ሒሊና ያልሽው ሁሉ ይሁን እንበል ። ዞሮ ዞሮ ማግባት አለብሽ እኮ » አሏት ። ሒሊና ፈገግ ለማለት እየሞከረች ፣ እጆችዋን ወደኋላዋ አጠላልፋ ዓይኖችዋን ኮርኒሱ ላይ ተክላ « እቴቴ በላይነሽ አሁን ተማሪ ነኝ ፣ ስለዚህ ጉዳይ አስቤም አላውቅም ። ግን አንድ ነገር አውቃለሁ ። በህይወቴ ከጋሼ ያሬድ የሚለየኝ ነገር ቢመጣ በክፉ ነው የምቀበለው ። ለማንኛውም ጊዜ ይፈታዋል » ብላ ባለበት በልጅነት ዓይነት ስሜት አንገታቸው ላይ ተጠመጠመች ። እሳቸውም እንደ ቀልድ አድርገው « አንቺ ከያሬድ አልለይም ትያለሽ ከኔስ ጋር እንዴት ነው ? መቼ ነው የምንለያየው ? » በማለት ሲጠይቋት ደነገጠች ።

« እርስዎና እኔማ ተለያይተን ተገናኝተናል ፤ ሁለተኛ መለያየት ግን አይኖርም » አለቻቸው በእርግጠኝነት ስሜት ።

* * *

ክረምቱ አለፈ ። መስከረም ጠባ ። የአደይ አበባ በየቦታው ፈካ ። የጠዋት ፀሐይ ምድሩን በብርሃንዋ አድምቃዋለች ። ከታክሲ እንደወረዱ ሀሰን በሁለት እጁ ሻንጣ አንጠልጥሎ ፣ ሕሊና አንድ ተንጠልጣይ ባለ ጌጥ ዘንቢል ይዛ ተከታትለው ወደ ግቢው ዘለቁ ። በበሩ ላይ በተሰራው ቀስተደመና « የኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ » የሚል ጽሑፍ በትልቁ ተጽፏል ።

ሀሰን ፊትለፊት ከቆመው ዘበኛ ጋር የተወሰነ ጊዜ ያህል ተነጋገረና ወደ ሕሊና ዞር ብሎ እንድትከተለው ምልክት አሳያት ። ተያይዘው የተማሪዎች ጉዳይ ክትትል ቢሮ ቀረቡ ። የተጠየቀችውን ማስረጃ ካቀረበች በኋላ የተመደበችበትን የመኝታ ክፍል የሚገልፅ ደብዳቤ ተሰጣት ። ጓዟን ተሸክመው ወደዚያው ሲያመሩ ወደ አዲስ ኑሮ በመግባትዋ ትንሽ ቅሬታ የተሰማት ይመስል ነበር። ሆኖም ምንም አማራጭ አልነበራትም ። መማር አለባት ። የተመደበላትን መኝታ ተረክባ ዕቃዎቿን እስከምታስናዳ ሀሰን የትምህርት ቤቱን ግቢ እየጎበኘ ጠበቃት ።

« በይ እንግዲህ እዚህ መግባት ነው የምፈልገው ብለሻል ። ይኸው መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ » አለና ለጥቂት ጊዜ ሊያጠናት ሞከረና « ምነው ቅር አለሽ ? በምርጫሽ ተፀፀትሽ እንዴ ? » ሲል ጠየቃት ። እሷም አንገቷን ቀና አድርጋ ፈገግ አለችና « እንዲያውም! በምርጫዬ በመመደቤ በጣም ነው ደስ ያለኝ ። ነገር ግን እኔን ያሳሰበኝ ከእቴቴ በላይነሽ መለየቴ ነው ። አሁን እንዴት አድርጌ ልለምደው ነው ? » አለችው አንገቷን ቀና አድርጋ በፈገግታ እያየችው ።



« እንግዲህ ሆድ አይባስሽ ? እሳቸው ምን ይሆናሉ ብለሽ ነው? ይልቁንስ ለራስሽ አስቢ በዚህ ላይ በየሣምንቱ እየተመላለስሽ መጠየቅ ትችያለሽ ። » ሲል አፅናናት ፈገግ እንዳለ ። « አይ ጋሼ ሀሰን እኔማ ወድጄ የገባሁበት ነው ። ከእንግዲህ ወዲህ ልጅነት አይመለስም ። ትምህርቴን መከታተል ነው እንጂ ። »

« መቼ መጥቼ ልውሰድሽ ? የእኛን ቤት ማየት አሰብሽ እነእማዬ ካላመጣሀት እያሉ አስቸግረውኛል » አላት ።

« እንግዲህ መጀመሪያ እስኪ ከትምህርቴም ከኑሮውም ጋር ልለማመድና እናስብበታለን » አለችው ። ቀጥላም « ጋሼ ሀሰን መቼም በጣም ነው የማመሰግነው ፤ በል እንግዲህ ለከሰዓት ሥራ እንዳይረፍድብህ ። » ስትል ለስንብት ሰላምታ እጅዋን ዘረጋች ። እሱም በጥሞና እያያትና እጇን እንደጨበጠ « አይዞሽ ሕሊና በርቺ ። የሚቸግርሽ ነገር ካለ በሰጠሁሽ ስልክ ቁጥር ደውይልኝ » አለና መንገዱን ጀመረ ።

« ደህና ዋል ። ለእቴቴ በላይነሽ በደህና መድረሴን ንገራቸው። አይዞዎት አታስቡ ሳምንት መጥቼ እጠይቅዎታለሁ በልልኝ » አለች እንዲሰማው ድምጿን ከፍ አድርጋ ። ሕሊና ወደ ሴቶች የመኝታ ህንፃ ስትመለስ ፣ ክፍሎቹ ሁሉ በገቢ ተማሪዎች ተወረው ነበር ። በአጭር ጊዜ ጓደኝነት ፣ እርስ በእርስ መተዋወቅ ፣ አልጋ ማንጠፍ ፣ መተጋገዝ . . . ተጀምሯል ።

ሕሊና ክፍሏ እንደገባች ከአንደኛው ሻንጣዋ ውስጥ አንሶላና የአልጋ ልብስ አውጥታ የተመደበላትን አልጋ ማንጠፍ ጀመረች ። በዚህ ወቅት አንድ ጠየም ያለች መልከ መልካም ልጃገረድ ሕሊና የምታነጥፈውን አንሶላ ከአንድ በኩል እያገዘቻት ንግግር ጀመሩ ።

« አሁን ገና ነው የመጣሽው ? » ስትል ሕሊናን ጠየቀቻት አዲሷ ልጅ ። « አዎ ቤቴ ቅርብ ስለሆነ ለምን ከዘመዶቼ ጋር ትንሽ

አልቆይም ብዬ ዛሬ መጣሁ ። አሁንም በስንት መከራ ሳልፈልግ በግድ ነው የመጣሁት » አለች ።

« የት ነው ሰፈርሽ ? »

« አቃቂ ። »

« ውይ ታድለሽ እኔ የመጣሁት ከከንባታና ሐዲያ ነው ። ቤተሰቦቼ የሚኖሩት ሆሳዕና ነው ። »

« ሥሜ አልማዝ ኤርሞሎ ይባላል እንተዋወቅ » በማለት እጇን ዘረጋችላት ።

« እኔ ደግሞ ሕሊና እባላለሁ » በማለት ተጨባበጡ ።

ከዚያን ቀን ጀምሮ አልማዝና ሕሊና ጓደኞች ሆኑ ። የሕሊናና የአልማዝ ፀባይ በአብዛኛው ይመሳሰላል ። ሁለቱም ቢሆኑ ሰውን በቶሎ መልመድ አይችሉም ። የእነሱ የራሳቸው ግንኙነት እንኳን ከጊዜ ብዛት እየደረጀ መጣ እንጂ በመጀመሪያው ሰሞን ያዝ ለቀቅ ያለ ፣ በቀዘቀዘ መሠረት ላይ የተጣለ ነበረ ። ሆኖም ቀስ በቀስ እየሞቀና ግንኙነታቸው እየተጠናከረ መጣ ።

ሕሊና የመጀመሪያው የትምህርት ቀን በጣም ከብዷአት ነበር። በኮሌጅ የሚሰጠውን የትምህርት ዓይነትና ብዛት በስሙ ብቻ በመስማት በጣም ፈርታ ነበር ። በዚህ ላይ በእሷ የትምህርት ዘርፍ የተመደቡት በሙሉ ወንዶች ነበሩ ። ወንዶቹን ለመቅረብ ፍላጎት አልነበራትም ። እናም ሀሳቧን እንኳ በመካፈል የምትረዳት አንድ የሴት ጓደኛ አጠገብዋ አላገኘችም ። ነገር ግን ይህ ሁኔታ ለብዙ ጊዜ አልቀጠለም ። ትምህርቱ ተጀምሮ ጥቂት ቀናት እንደተካሄደ ሕሊና በትምህርት ክፍሏ የሚገኙትን ወንዶች ልጆች እንደማገኛቸውም የሴት ጓደኛ በመቅረብ አብሮ መወያየትና የሚሰጡአትን ሥራዎች ተባብሬ በመሥራት ቀደም ሲል የነበራትን ፍርሃት አስወግዳ በብዙ ነገር ተለወጠች ።



የመጀመሪያዎቹን ሁለት ሣምንታት ከኮሌጅ ቅጥር ግቢው ሳትወጣ ቆየች ። አልፎ አልፎ ከአልማዝ ጋር ግቢው ውስጥ ደስ ወደአላቸው ቦታ በመሄድ ለመዝናናት ይሞክሩ ነበር ። ሁለቱ ጓደኛ ሞች ከመመገቢያ ሰዓትና ከትምህርት ውጪ ያለውን ጊዜያቸውን አብረው ነበር የሚያሳልፉት ።በወል የትምህርት ዘርፍ ላይ ሲገናኙም አንድ ላይ ቦታ ፈልገው ይቀመጡ ነበር ። ራሳቸውን ከኮሌጁ ባህሪ ጋር ካላመዱ በኋላ አቃቂ ሄደው አንድ ቀን አድረው ተመለሱ ። ሕሊና በትምህርት ቤት ውስጥ ባለው የክልል ወጣት ማህበር ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረግ ጀመረች ። በስብሰባዎች ላይ በምታቀርበው የበሰለ ሀሳብና በሥነ ምግባርዋ የተሰጣት አክብሮት ከፍተኛ ሆነ ። የት/ቤት መሠረታዊ የወጣቶች ማህበር ውስጥ በኮሚቴ አባልነት እንድትሠራ ተመረጠች ። በትምህርቷ ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ በቃች ። በመምህሮቿ ዘንድ እንደ ምሳሌ የምትጠቀስ ተማሪ ሆነች ።

አንድ ቀን አልማዝ ከምሳ በኋላ ባለው የዕረፍት ጊዜ ለሕሊና ከውጭ የተላከ የታሸገ ፖስታ ሰጠቻት ። ሕሊና የያሬድ እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀባትም ። ልቧ እየዘለለባት በችኮላ ቀዳ ማንበብ ጀመረች ።

*« ሕሊና በችኮላ የፃፍኩት ደብዳቤ ስለሆነ አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ ። ሆኖም በፈተና ላይ ስለሆንን ጊዜ ስለአጠረኝ መሆኑን ከተረዳሽ የጠየኩትን እንደማትነሽኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። ይሄውልሽ የመጨረሻ ፈተናችንን እየወሰድን ነው ። ለመምጣት ከእንግዲህ የሚቀረን ጊዜ በወራት አነስተኛ ጊዜ መሆኑን ልገልፅልሽ እወዳለሁ ። ሕሊና ከአንቺ ጋር መገናኘቱ ህልም ህልም ነው የሚመስለኝ። ጊዜው እየረዘመ ሲመጣ ሰው የተለየውን እየረሳ ይሄዳል ። ሆኖም የኔ በተቃራኒው*

*መርሳት ሳይሆን ማስታወሱ ነው ያገረሸብኝ ።*
*ሕሊና እንቺም እኔ ስመጣ ፈተናሽን ጨርሰሽ*
*የክረምት የዕረፍት ጊዜ ስለሚሆን ናፍቆታችንን*
*ለመወጣት ብዙ ጊዜ እንደሚኖረን ተስፋ አደርጋለሁ።*
*ሕሊና ጤናዬ የሰጋር ፈረስ ያህል ገስግሶ ለመምጣት*
*ከመዘጋጀት በስተቀር ጤንነቴ የተሟላ ነው ። ሀሳቤ*
*ዘወትር ከእናንተ ጋር ነው ። ለማንኛውም ስመጣ*
*በሠፊው እናወራዋለን ። ጤንነትሽን ጠብቂ ፤*
*ትምህርትሽን በርቺና ተማሪ ። መልካም የትምህርት*
*ጊዜ ።*

*ያንቺው ያሬድ ።*

ሕሊና ደብዳቤውን ከጨረሰች በኋላ ቀና ብላ ወደ ደረቷ አስጠጋች ። « እፎይ ታድዬ ! » ብላ በረጅሙ ስትተነፍስ ሁሉ አጠገቧ ቆማ የነበረችው አልማዝን አላየቻትም ። አልማዝ ጠጋ ብላ ሕሊናን እየተመለከተች « እጮኛሽ ነው ? » ስትል ቀስ ብላ ጠየቀቻት አጠገቧ አልጋው ጫፍ ላይ እየተቀመጠች ። ዞር ብላ አልማዝን ለጥቂት ጊዜ ካየቻት በኋላ « ወንድሜ ነው ። አቃቂ ፎተግራፉን ያሳየሁሽ » አለቻት ።

ሕሊና አቃቂ ተመልሳ የክረምት ዕረፍቷን የመጀመሪያ ሣምንት አገባደለች ። ወ/ሮ በላይነሽ የሕሊናን ተመልሶ መምጣት እንደ ትልቅ ደስታ ነበር የቆጠሩት ። መቁጠር ብቻ ሳይሆን በየጊዜው ለቀሰብ ከሚሰጣቸው የወር ሂሳብ ላይ ቀናንሰው አንድ ትልቅ በግ ገዝተው መቀበያ ደም አፍስሰዋል ። ሕሊና እንደዚህ ዓይነት ድግስ ይሆናል ብላ አላሰበችም ነበር ። በመጀመሪያው ቀን ሀሰን በወ/ሮ በላይነሽ ትዕዛዝ አዘል ልመና ለእራት ግብዣ አቃቂ መጥቶ ነበር ።



የቅርብ ጎረቤቶቻቸው ፣ የኩቻ እናትና አባት የደስታቸው ተካፋይ ሆነዋል ። ይኸ ሁሉ የእቴቴ በላይነሽ ስሜት ነው ። ለሕሊና ግን ምንም አልነበረም ። ጋባዥዎችዋን ለማስደሰት ስትል ከምታደርገው እንቅስቃሴ የዘለለ አይደለም ። የእሷ ደስታ ያሬድ ሲኖር ነው ። እናም ደስታዋ ደስታ ይሆን ዘንድ የያሬድን መምጣት በመጠበቅ በተስፋ ተሞልታለች ።

ሐምሌም እንደ ሰኔ ሊሰናበት አንድ ሳምንት ቀረው ። የያሬድ ነገር ግን ሽታውም በአካባቢውም አልደረሰም ። ሕሊና እጅግ ተረበሸች ። ሀሰን ጭንቀቷን ተረድቶ ስለነበር ለትምህርት ከያሬድ ጋር ከተላኩት አንዱ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ አግኝቶት ስለያሬድ ሁኔታ ጠይቆት ነበር ።

« ሕሊና ያሬድ ሐምሌ 27 ነው የሚመጣው ። አብሮት የነበረው ጓደኛው የአውሮፕላን ትኬት በማጣቱ ነው ወደ ኋላ የቀረው ብሎኛል » ሲል ሊያፅናናት ሞከረ ። ለሕሊና ግን የጊዜ ሆድ እንደ ላስቲክ በመሳብ ሐምሌ 27ን ያራቀው መሰላት ። ቀኑ እንዲመሽላትና የሚቀጥለው ቀን በቶሎ እንዲሰወጥ እራስዋን በስራ ጠመደች ።

የጊዜ ዕርዝመትና እጥረት እንደባለቤቱ ነው ። ለሕሊና እንደ ላስቲክ የሚሳበው ጊዜ ለሌላ ሰው ደግሞ ቀኑ አጥሮ ሳያውቁት ሊያልፍባቸው ይችላል ። ሆኖም ተፈጥሮ ለማንም አታዳላም ሁደቷን ጠብቃ በጊዜ ቦይ ስትፈስ ቆይታ ሐምሌ 27 ላይ ስትደርስ ጭራሽ የቆመች መሰለች ።

*        *        *

እንዳይነጋ የለም ነጋ ። ጊዜ ጊዜን አምጦ ጊዜን ወልዶ አደረሰ ። ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ሲሆን ሕሊና እራስዋን አስማምራ ጉዞዋን ወደ አዲስ አበባ አመራች ። ከአቃቂ በታክሲ ቦሌ ስትደርስ በየቦታው በርካታ ሰዎች ተሰብስበው ታዩዋት ። ሲቃና ጉጉት እየተናነቃት ፤ ከቦታ ቦታ እየተሯሯጠች ሀሰንን ለማግኘት ሞከረች። ሀሰን ግን በቦታው የለም ። ዋናው መግቢያ በር ላይ መጠበቅ ጀመረች። መኪና በቆመ ቁጥር ሀሰን የሚወጣ እየመሰላት ፤ ግን ደግሞ ሌላ ሰው እየሆነባት ሺህ ዓመታት የሆነባትን ያህል በትዕግስት ጠበቀችው ። እየቆየች ፤ እራሷን እያረጋጋች ስትሄድ የሆነ ስጋት በአዕምሮዋ ውስጥ አንዣበበ ።

« ጋሼ ሀሰን ለእኔ በማዘን ዋሽቶኛል ማለት ነው ። አሁን የማይመጣው በነገሩ ስላፈረበት ይሆን ? » ስትል አሰላሰለች ።

« የለም አያደርገውም ፤ ለምን ይዋሻል ? ውሎ አድሮ ለሚገለፅ ነገር ! ጋሼ ሀሰን እንደዚህ ዓይነት ቀላል ሰው አይደለም » እያለች እራሷን ለማሳመን ታገለች ። በእርግጥ ሀሰን ቃልአባይ አልነበረም ። ከቀጠሮአቸው ሰዓት ቀድሞ ደርሶ ከአንድ ሌላ ሰው ጋር ከመኪና ሲወጡ ሕሊና በሩቁ አየችው ። ሕሊና ሰውነቷ ሁሉ በድን ሆነባት ። መንቀሳቀስ አልቻለችም ። ባለችበት ደርቃ ቀረች ። ዓይኖችዋ ብቻ የሰዎቹን ወደእሷ መቅረብ ተጠባበቁ ። ሀሰን አጠገቧ እንደደረሰ ሠላምታ አቀረበላት ። እራሷን ስታረጋጋ ሁኔታው ተገለጸላት ።

ቀጠሮአቸው ሀሰን ያሬድን ሊያመጣላት ሳይሆን አብረው ለመቀበል ነበር ።

« ተዋወቁ ፤ የእኔም የያሬድም የጋራ ጓደኛችን ነው » አለ ሀሰን ።



« ፀጋው እባላለሁ » አለና ለሕሊና እጁን ዘረጋ ።

« ሕሊና »

ጊዜው ገና ነበር ። ሦስቱም ለመቆያ ያህል አቅራቢያቸው ወደ ነበረው ካፍቴሪያ አመሩ ። ሀሰንና ፀጋው ቡና በወተት አዘዙ ። ሕሊና ግን ምንም መቅመስ ባትፈልግም ደረቅ ሻይ ብቻ እንዲመጣላት አዘዘች ። ሠዓቱ ነጎደ ። አራት ሰዓት ደረሰ ። የሕሊና መንፈስ መረበሽ ጀመረ ። በዚሁ መካከል የትልቅ አውሮፕላን ድምጽ ተሰማ ። ሕሊና ባለችበት ቆማ የሰማችውን ድምጽ ለማረጋገጥ ጆሮዋን አቀናች ። ፀጋው እነ ሕሊና ወደ ቆሙበት እራመድ እራመድ ብሎ « ኢንተርፍሎግ ነው » በማለት አበሰረ ።

ሕሊና በውበት ጥበብ እንደ ጠዋት ጮራ ፈካች ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የፈዘዙት ዓይኖችዋ እንደብርሃን መብራት ጀመሩ። ሕሊና ያሬድ ከአውሮፕላን ሲወርድ የሚታይበትን ቦታ መርጣ በጉጉት ሲቃ ተይዛ ቆመች ። አውሮፕላኑ መንገደኞቹን ማውረድ ሲጀምር ፀጋው ፤ ሀሰንና ሕሊና ዓይናቸው እስኪደክም ድረስ በርቀት የሚወርዱትን ሰዎች አንድ በአንድ ተመለከቱ ።

መጀመሪያ የወረደው የውጭ ሀገር ዜጋ ነበር ። ሁለተኛ፣ ሶስተኛ አሁንም የለም ። የሕሊና የልብ ትርታ እየጨምረ መጣ ። መላ ሰውነቷ ሲርገፈገፍ ለተመለከተ ሰው የበሽታ እንጂ የጤና ነው ለማለት አያስደፍርም ። ሰባተኛ . . . ፤ ስምንተኛ ሰው በአውሮፕላኑ ተንቀሳቃሽ ደረጃ በመውረድ ላይ ነበር ። አሁንም ያሬድ የለም ። የሕሊና ፊት በወረደው ሰው ቁጥር ልክ እንደ ሲኒማ ቤት መብራት ቀስ እያለ እየጨለመ ፤ ፊቷ እየጠወለገ ፤ ዓይኖችዋ ከዳናቸውን እየለበሱና እያነሱ ሲሄዱ ተሰማት ። የቀራት የሞኝ ተስፈኝነት ብቻ ነበር። . . . አሥራ አራት . . . አሥራ አምስተኛ ሰው በመውረድ ላይ እንዳለ ሕሊና እንደ ሕፃን ልጅ እየዘለለች « ጋሽ ያሬድ . . . ጋሽ ያሬድ ! » እያለች ጮኸች ።

ሕሊናና ወ/ሮ በላይነሽ ደስታቸውን ለመግለፅ ፣ « እንኳን ደህና መጣህ » ለማለት የሚመጡትን የሥራ ጓደኞቹንና ጎረቤቱን ሳይታክቱ በማስተናገድ ለአንድ ሳምንት ያህል ቆዩ ። የሰው ብዛት ሕሊናን ከያሬድ ጋር ለብቻ ለመጫወት ዕድል አልሰጣትም ። ሌላው ቀርቶ የዓይኖቿን ረሃብ ለማስታገስ አልቻለችም ። መቼም ሥራ ሥራ ነውና ያሬድ ወደ አዲስ አበባ ሄዶ ለመሥሪያ ቤቱ መድረሱን ማስታወቅ ነበረበት ። ቅሬታ እየተሰማት በሳምንቱ መጀመሪያ ሰኞ ዕለት ያሬድን እስከ መኪና ተራ ሸኝታው ተመለሰች ።

ያሬድ በፊት የነበረው ጸባዩ አልተለወጠም ። ሆኖም ዝምታን አበዛ ። ጎትጉታ እንዲያጫውታት ካላደረገችው በስተቀር እራሱ የጨዋታ መነሻ ፈጥሮ መቀጠል አይፈልግም ። ነገር ግን ሕሊና እንዲናገርና እንዲያወራት ስትል ብቻ ስለ ጥቃቅን ነገሮች ሳይቀር ለማንሳት ብትሞክርም የሚያስደስት ውጤት አልነበረውም ።

በዚህ ሁኔታ ናፍቆትዋን ሳትወጣው አዲስ አበባ ሄደ ። ከአዲስ አበባ ሲመለስ ይበልጥ ተለውጦ ፣ ጠቁሮ ፣ ከስቶ ፣ ገርጥቶ ነበር ።

« ሕሊና መቼም አሁንም ደስ አይልሽ ይሆናል ። ሆኖም መሆን ያለበት ነገር ነው . . . » አለና ሀሳቡን ሳይጨርስ ወንበር ጎተት አድርጎ ተቀመጠ ። ሕሊና በማታውቀው ጭንቀት ጭንቅላቷ እንደተወጠረ አጠገቡ አረፍ አለች ።

« እንዴት አድርጌ ልንገርሽ ? »

« እንደዚሁ ዝም ብለህ ንገረኝ ጋሼ ያሬድ ሙት አልፈራም » አለችው ።

« አትፈሪም ? እውነትሽን ነው ! »

« በቃ አዎ ! ብፈራስ የት እደርሳለሁ ። »

« ይኸውልሽ እንደገና ወደ ሌላ ቦታ ተቀይሬ መሄዴ ነው » አላት ።



« ደግሞ የት ልትሄድ ነው ? ትፈራለች ብለህ ነው የምትቀልድብኝ ? » በማለት ሆድ ባሳትና እንደማኩረፍ አለች ።

ያሬድ የጀመረውን ቶሎ ለመጨረስ ስለፈለገ « እውነቴን ነው አሁን የተመደብኩት ኮምቦልቻ ወሎ ውስጥ ነው ። አስቸኳይ ነገር ሳይፈጠር አይቀርም ። አለቃዬ እንዲያውም አርፍደሃል ነገውኑ እንድትሄድ ብለው ነው ያዘዙኝ » አለና ፀጥ አለ ። ከዚህ በኋላ ሕሊና የምትወደው ዘመዷ እንደሞተባት ሁሉ የለቅሶ ጩኸትዋን ማልቀስ ጀመረች ። ያሬድ አቅፎ ሊያባብላት ሞከረ ።

« ወይኔ ዕድሌ ! ወይኔ ዕድሌ ! » ልቧ ተሰብሮ ነበር ። እጆቿን ጠረጴዛ ላይ አስደግፋ ፊቷን በእጆቿ መሃል ቀብራ ለረጅም ሰዓታት ስታለቅስ ቆየች ። ወ/ሮ በላይነሽና የኩቻ እናት ሊያስቆሟት ታገሉ ፤ አልቻሉም ። በመጨረሻ ያሬድንም ሆድ ባሰው ።

« እኔ አንቺ ስታለቅሺ ሆድ ይብሰኛል ። እንደዚሁ ሳልናገር ብጠፋ ኑሮ ይሻልሽ ነበር ? » ሲል ተቆጣ ። ቁጣው ፈጣን መልስ አስከተለ ። ለቅሶዋን ለመቆጣጠር ሞከረች ። ሆኖም ተረጋግታ መቀመጥ አልቻለችም ። በህይወቷ አንድ ጊዜ ብቻ ነበር የዚህ ዓይነት ራስ ምታት ያመማት ። ያሬድና በላይነሽ ደጋግፈው አልጋ ላይ አስተኟት ።

ከእንቅልፏ የቀሰቀሳት ያሬድ ነበር ። የእራት ሰዓት በመድረሱና የጤንነቷም ሁኔታ ስላሳሰበው ነበር እንድትነሳ ያደረገው። አልጋዋ ላይ ተኝታ ትንሽ እንቅስቃሴ ካደረገች በኋላ ፈጠን ብላ ወረደች ። ያሬድ በእጁ አቅፎ ወንበር ስቦ አስቀመጣት ። ወ/ሮ በላይነሽ ምግብ አቀረቡና ሕሊናን በማጉረስ እራቷን አበሏት ። እራት ከተበላ በኋላ ያሬድ እንድትተኛ ለመናት ።

« አንተ ነገ እሄዳለሁ እያልክ ለምኑ ነው መኝታ ? » አለችው በቅሬታ ።

« እራስሽን ያምሻል ተኝተሽ እንጫወታለን » አላት ።

« አልፎልኛል ። የራስ ህመምም እንቅልፍም የለብኝ » አለችው ።

« እንግዲያውስ ተቀምጠን እናውራ ? » በማለት የለበሰውን ጋቢ እያስተካከለ « በይ ጨዋታውን አምጪ » አላት ።

ሕሊና የፈለገችው ጨዋታ ሳይሆን ያሬድን ቁጭ ብላ ማየት ነበር ። ፊቷን በሁለት እጆቿዋ መሀል ቀብራ ክንዷን በጠረጴዛው ላይ አንተርሳ አተኩራ ዓይን ዓይኑን ማየት ጀመረች ። ያሬድን ቀደም ብሎ ውጪ ከመሄዱ በፊት የነበረውን ፀባይ በማንፀባረቋ እየተገረመና እየተደሰተ ፊቷን በዓይኖቹ ሊዳስላት ቢሞክርም ብዙ ለመቆየት አለቻለም ። የሕሊና የራስ ህመም ምቀኛ ሆነበት ። በህመም ስሜት እራሷን ስታወዛውዝ ከሄደበት ሀሳብ ነቃ ።

« ምነው አመመሽ ? ሄጂና ጋደም በይ » አላት ። ነገ የምትሄድ ከሆነ ከአንተ ጋር እያወራሁ ነው የማድረው » አለችው ጠንከር ባለ አነጋገር ።

« አይሆን . . . አይሆንም ብያለሁ . . . » እራሱን እየነቀነቀ ተናገረ ።



* * *

ያሬድ የአቃቂ ቤቱን ለቀበሌው አስረክቦ ኮምቦልቻ ከገባ ስድስተኛ ወሩን ያዘ ። የሚኖርበት ቤት መንግስት ነበር የሰጠው ። አልፎ አልፎ ወደ አዲስ አበባ ብቅ ብሎ ከሕሊና ጋር ቆይቶ ይመለሳል ። ኮምቦልቻ ሄዳ ቤቱን ያየችው በፋሲካ የዕረፍት ጊዜዋ አምስት ቀናት ብቻ ነበር ። ይህን የፋሲካ በዓል ያሬድ ከውጭ የመጣበትን ዕለት ያህል ነበር በጉጉት የጠበቀችው ።

በፋሲካው ዝግ ሰሞን ያሬድና ሕሊና ተያይዘው ቀኑን ሙሉ ሲዞሩ ነበር የከረሙት ። ለሕሊና ሲል የአምስት ቀን ፈቃድ ወሰደ ። የፈለገችውን ሁሉ በማድረግ ጊዜውን አሳለፈ ። ስለሕሊና እያሰበ ከራሱ ጋር የውጣ ውረድ ትግሎችን አካሄደ ። አምስቱን የዕረፍት ቀናት በደስታ አሳልፋ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰች ። አዲስ አበባ እንደ ያሬድ የቅርብ ረዳት ሆነው የሚቀርቧት ሀሰንና ቤተሰቦቹ ነበሩ:: በሀሰን በጎ አድራጎትና አቀባበል ከያሬድ ጋር ያላቸውን የፀባይ አንድነት ታደንቃለች ። ሆኖም ሀሰን ችኩልና በሚያደርገው ነገር ሁሉ በጣም ፈጣን በመሆኑ ከያሬድ ይለያል ። ቢሆንም ሕሊና በዚህ ጠባዩ ሀሰንን አልጠላችውም ።

አንድ ቀን ሀሰን ሕሊናን ለማዝናናት በሣምንቱ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ወደ መምህራን ማሠልጠኛ መጣ ። ቀጠሮው ቀደም የተያዘ ስለነበር ሕሊና እራስዋን በደንብ አዘጋጅታ ነበር የጠበቀችው ። በቅርብ የገዛትን አሮጌ ቮልስ መኪና ይዞ ኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ፊት ለፊት ቆሞ ጠበቃት ። በትልቁ በር በኩል ስትወጣ ሀሰን ከመኪናው ወርዶ እንደእንግዳ ሴት ተመለከታት ። አለባበሷ ለሀሰን አዲስ ነበር ።

የፀጉር አሰራርዋና አለባበስዋ እጅግ ዘመናዊ የሚሉት ዓይነት ሆነበት ። ሕሊና ውብ ሆና ታየችው ። መኪናውን ከፍቶ ሕሊናን ካስገባት በኋላ ይዟት ከነፈ ። ቃል ሳይተነፍሱ ብዙ ከሄዱ በኋላ « ዛሬ ደግሞ ልዕልት መስለሻል ሕሊና » በማለት ዘወር ብሎ መልከት አደርጋት ።

« ስለ አስተያየትህ እመሰግናለሁ » አለችው ውስጧን ሀፍረት እየተሰማት ። ሀሰን የመኪና አነዳዱን ፍጥነት ጨመረ ። መኪና ውስጥ ከሕሊና ጋር ብዙ ውይይት አላስፈለገውም ። ከከተማው ውጪ ወደ አምቦ መንገድ ጥቂት ከተጓዙ በኋላ ወደ ቀኝ በመታጠፍ ከአንድ ግቢ ውስጥ ገባና መኪናውን አቆመ ።

« በይ እንግዲህ እዚህ ትንሽ እንቆይና ወደ እነ እማዬ እወስድሻለሁ » ሲላት ሕሊና የመኪናውን በር ከፍታ ወጣች ። ትንሽ ዘግየት ብሎ የመኪናውን መዝጊያ በደንብ መዘጋቱን ካረጋገጠ በኋላ እንሂድ በሚል ዓይነት ጭንቅላቱን አወዛወዘ ። ወደ አንዲት ብቸኛ ጎጆ ቤት ውስጥ ገብተው ፊት ለፊት ተቀመጡ ። ሀሰን በጎጆው ምሰሶ ላይ የተንጠለጠለውን መጥሪያ እየተጫነ « እንግዲህ ዛሬ ከቢራ በስተቀር ይነስም ይብዛም መጠጣት አይፈቀድም » አላት ።

« ጋባዥ ነው ተጋባዥ የመጀመሪያ ምርጫ የሚሰጠው ? » በማለት ፈገግ እንዳለች ተመለከተችው ።

« ይቅርታ ይደረግልኝ የአንቺ ግብዣ ሲሆን ምርጫውን እሰጥሻለሁ » ከማለቱ አስተናጋጁ ከተፍ አለ ። ሀሰን ከኪሱ ቦርሳውን አውጥቶ « አራት ቢራ » በማለት አሥር ብር መዘዘና ለአስተናጋጁ ሰጠው ። ሕሊና አፏን በድንጋጤ ከፍታ « አንዴ ይሄ ሁሉ ለእኔ ? እኔ አንድ ይበቃኛል » በማለት ወደ አስተናጋጁ ዞረች ።

« ሁለት ብቻ » አለችው ።

« ብድሬ ዓይነትን እንጂ ብዛት አይጨምርም » በማለት ወደ አስተናጋጁ መለስ ብሎ « ተስማምቻለሁ ፤ ሁለት ለመንደርደሪያ



ይበቃል » ሲል አዘዘው ። ከዚያም ሕሊናን እየተመለከተ « እንግዲህ መምህርት ሕሊና ትምህርትዎን ሊጨርሱ ወር ብቻ ነው የቀረዎት » አላት ።

« እፎይ » በማለት በረጅሙ ከተነፈሰች በኋላ « ልገላገል ነው» አለችው ።

« ከትምህርቱ ዓለም የሥራው ዓለም ይሻላል ብለሽ ነው ? የሥራው ዓለም ይሰለቻል ፤ ይደክማል ፤ ኑሮውም ብዙ ያሳስባል ። ተማሪ ግን ምን አለበት ? እንዳይሰለቸው በየቀኑ የሚቀርብለት ትምህርት አዳዲስ ነው ። እንዳይደክመው ለማወቅ ያለው ፍላጎት ከድካሙ እንዲወገድ ብርታት ይሰጠዋል » በማለት ንግግሩን ጀመረ።

« እሱስ ልክ ነው አሁን ይመስላል እንጂ የትምህርት ቤት ጊዜ አልቆ ወደ ሥራ ስንሰማራ እንዴት እንደሚያስጠላ ይታየኛል ። ሌላው ቀርቶ በት/ቤት ያፈራናቸውን ጓደኞቻችንን ተለይተን አዲስ የሥራ ጓደኞች መመሥረት ከባድ ነው የሚመስለኝ » አለችው በሀሳቡ በመስማማት ።

ሀሰን የሕሊናን ፊት ቀረብ ራቅ እያለ በመፈተሽ « ሕሊና አሁን ከጨረሽ የወደፊቱ ዕቅድሽ ምንድነው ? » አላት ። ዓይኖችዋን ከሀሰን ወደ ሌላ አቅጣጫ በማንከራተት ረዘም ላሉ ሴኮንዶች ካለበች በኋላ « ምን ዕቅድ አለኝ ። እንደ እኔማ ከነጋሼ ያሬድ ጋር ተደባልቄ እንደድሮዬ መኖር ነው » አለችው ።

« መቼ ሰው ሁሉ እንደተመኘው ይሆንለታል ። የሁሉም ምኞት የተለያየ ነው ። ምኞትና ሥራ ታዲያ እንደ አጋጣሚ አልፎ አልፎ በአንድ ላይ ተቀናጅተው ይገኙ እንጂ አብዛኛውን ጊዜ ሁለቱ ለፈላጊው አራምባና ቆቦ ናቸው » በማለት ትንሽ አመነታና « ሕሊና ይቅርታ አድርጊልኝና ለእኔ ተገቢ መስሎ የታየኝን ግን የማይገባ ጥያቄ ልጠይቅሽ ፤ ምንመሰለሽ ጥያቄዬ ግራ እንዳይሆንብሽ በማለት ነው » አላት ።

« ጠይቀኝ የማውቀው ከሆነ እመልስልሃለሁ » አለችው ጥያቄውን ለመስማት በመጓጓት ። ወደ መሬት አቀርቅሮ « ጥያቄው አንቺንና ያሬድን የሚመለከት ነው ። እም . . . ም. . . .ም. . . ስለአንቺና ስለ ያሬድ ግንኙነት ልትነግሪኝ ፈቃደኛ ነሽ ? » አለና ያስጨነቀው ይመስል ተነፈሰ ። « አልገባኝም ፣ ግንኙነት ስትል ምን ማለትህ ነው ? » በማለት ጥያቄውን በጥያቄ መለሰችለት ፣ አቀራረቡ ግራ ገብቷት ።

« ግንኙነት ማለቴ እንግዲህ አለ አይደል . . . . . . . » በማለት ጥቂት በማለሳለል አቅማማና « ግንኙነት ማለቴ . . . . አሁን ትምህርትሽን ስትጨርሺ ከያሬድ ጋር ትጋባላችሁ ? » በማለት ሲፈራ ሲቸር ጠየቃት ። ሕሊና ከልቧ ከት ብላ በመሳቅ ደጋግማ ሀለንን ተመለከተችው ። « ጥያቄው የሚያስቅ ነው እንዴ ? » አለና የምንተዕፍረቱን አብሮአት በመሳቅ አይነት ፈገግ አለ ።

« አይ አንተ ! » አረፍ እንደማለት አለች « ለመሆኑ ለምን ጠየከኝ ? » ስትል ጠየቀችው ።

« መጀመሪያ ለጠየኩት መልስ ስጪኝና እኔ እቀጥላለሁ አላት።።

« እኔና ጋሼ ያሬድ እህትና ወንድም ነን ። ለወደፊቱም የዚህ አይነት ግንኙነት የሚኖረን ይመስለኛል » ።

« እስኪ ሙት በይኝ ! » ሲል መሀላ እንድታደርግለት የቀኝ እጁን ዘረጋላት ።

« መሀላው ለምኑ ነው ? በእውነት የነገርኩህ ሀቅ ነው አለችው ፣ ሀለን አመናት ። » ከዚህ በኋላ ያለውን ጊዜ በሳቅና በቀልድ፣ በጨዋታ አሳለፈ ። ድሮ ሕሊና ከምታውቀው በላይ የውስጥ ስሜቱን በማውጣት እሷን ለማሳቅና ለማስደሰት ሞከረ ። ሕሊና ሳታስበው ሶስተኛ ቢራ በማገባደድ ላይ ነበረች ።



* * *

የሕሊና የምረቃ ቀን በመቃረቡ ያሬድና ወ/ሮ በላይነሽ ከኮምቦልቻ ከመጡ ሁለት ቀን ሆኖአቸዋል ። ሕሊና በግቢው ውስጥ በነበረችቦት ወቅት የተረከበቻቸው የትምህርት መሣሪያዎችና የወጣት ማህበሩን ንብረት ለማስረከብ ወዲያና ወዲህ ስለምትራወጥ ከነያሬድ ጋር በውጉ ተገናኝታ ለመጫወት ጊዜ አልነበራትም ። ማታ ማታ ፣ ከሥራ በኋላ ሀለንና ያሬድ በሀለን መኪና ሕሊናን ወደ ከተማ ወስደው ትንሽ አመሻሽተው ወደ ት/ቤት ስለሚመልሷት በዚህ ለመፅናናት ሞከረች ።

የምረቃው ቀን ያሬድ ፣ ሀለንና ወ/ሮ በላይነሽ የክት ልብሳቸውን ለብሰው ከሌሎች የተማሪ ቤተሰቦች ጋር በመሆን በአዳራሽ ውስጥ እንደተቀመጡ ሕሊና የተሰጣትን የመመረቂያ ልብስ ለብሳ ከጓደኞችዋ ጋር አብራ ስትገባ ያሬድ በዓይኑ ቃኘት ። የዲፕሎማ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ከመጀመሩ በፊት መናገር የሚገባቸው የተቋሙ የበላይ አካሎች ንግግር አድርገው በመጨረሻ በትምህርት ዘመናቸው ከትምህርት ቤቱ የሥራ መስክ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ተማሪዎች ሽልማት ሲሰጥ የሕሊና ሥም በሶስተኛ ደረጃ እንደተጠራ በአዳራሹ የተሰበሰቡት ተማሪዎችና መምህራን ከፍተኛ ጭብጨባ በማድረግ አድናቆታቸውን ሲገልጹላት ያሬድ መላ ሰውነቱን ደስታ ነዘረው ። ሽልማቱን ከተቀበለች በኋላ መለስ ብላ ወደ እነ ያሬድ አቅጣጫ ቆማ ስትመለከት ያሬድ በሩቁ ሲከታተላት ነበረና ከመቀመጫው ተነስቶ አጨበጨበ ።

አጠገቡ ከተቀመጡት ከወ/ሮ በላይነሽ አበባና አንድ በወረቀት የተሸፈነ ስጦታ ተቀብሎ አገላብጦ ከሳማት በኋላ አበረከተላት ። ሕሊናም ጎንበስ በማለት ስጦታውን ከተቀበለችው በኋላ እሷም በተራዋ ያሬድን አቅፋ ጉንጮቹን አገላብጣ ሳመችው ።

የሕሊና የምረቃ በዓል በጣም የተዋበ ነበር ። በትምህርቷ የክብር ዲፕሎማ ተሸላሚ ነበረች ። በጣሙን ደስ ያሰኛት ግን ያሬድ ያበረከተላት ስጦታ ነበር ። ሕሊና ዕቃዋን ሰብስባ እነ ያሬድ ያረፉበት ሆቴል ደርሳ ያሬድ የተከራየላት መኝታ ቤት እንደገባች ሦስቱ ሰዎች የሰጡአትን ስጦታ እየፈታች ማየት ጀመረች ።

የያሬድ ስጦታ ሁለት ከወርቅ የተሠሩ ጌጦች ነበር ። የአንገት ሀብልና የጆሮ ጉትቻ ። የሀሰን ስጦታ ደግሞ የወርቅ ቀለበት ሆኖ በላዩ ላይ በጥቁር ድንጋይ የእሷ ሥም የተፃፈበትና ከሥሩ የሀሰንን ሥም የያዘ ነበር ። ሦስተኛው ስጦታ የወ/ሮ በላይነሽ ሲሆን መጠኑ ከሁሉም የሚበልጥ በስጦታ ወረቀት የተጠቀለለ ነበር ። በጥሩ የእጅ ፈትል የተሰራና በጥሩ አዋቂ የተጠለፈ ቀሚስና ነጠላ ነበር ። ሕሊና የሦስቱንም ሰዎች ስጦታ አልጋዋ ላይ ዘረጋጋችና ከወዲያ ወዲህ እየተሽከረከረች አስተዋለች ። የያሬድን ሀብል እያጠለቀች በመስታወት ውበቷን አስተዋለችና ፈገግ አለች ። በሀሰን ቀለበት ደስ ተሰኘች ። የወ/ሮ በላይነሽን ስጦታ ወደ መስኮቱ አስጠግታ አየችና በመገረም አይነት እራስዋን ነቀነቀች ።

በነጋታው ጠዋት ሀሰን አውቶቡስ ተራ አድርሶአቸው ለመመለስ ሊሰናበታቸው ሕሊናን በተለየ ዓይን አስተዋላት ።

« እንግዲህ ቶሎ እንድትመጪ ድልድላችሁ በነሐሴ ውስጥ ነው ። ጥሩ ጥሩ ዕጣ ይወጣና ዝቃጩ እንዳይደርስሽ ። » በማለት ቶሎ መጥታ ለማየት ያለውን ፍላጎት በተዘዋዋሪ መንገድ ገለፀላት ። ሕሊና በአውቶቡስ ጉዞዋ ወቅት እያሰላሰለች የምትሄደው ስለተደረገላት ስጦታና ስለትርጉማቸው ነበር ። ያሬድ የሰጣት እንደጠበቀችው እህትነቷን የሚያረጋግጥላት ነበር ። ወ/ሮ በላይነሽም እናትነታቸውን የሚያረጋግጥ ስጦታ ነበር ያደረጉላት ። ሀሰን የሰጣት ስጦታ ትርጉም ግን ለሕሊና ግራ ነበር ። በቀለይ የስሙ በቀለበቱ ላይ መስፈር ጥርጣሬዋን አሰፋው ።



ሕሊና በኮምቦልቻ ቆይታዋ የሐምሌ ወር አልቆ ነሐሴ ሲጀምር መሄጃዋ እየተቃረበ በሄደ ቁጥር የፍርሃትና የሀዘን ዳመና አንገዋበበባት ። ብዙ ጊዜ ስለ ያሬድ ስታስብ በመማርዋ ትበሳጫለች። ለያሬድ ምግብ አብሳይ ሆና እንደ ወ/ሮ በላይነሽ አብራው ብትኖር ምኞትዋ ነበር ። የያሬድም ሀሳብ ተመሳሳይ ቢሆንም አብሮ ለመኖር የመረጠው አቅጣጫ ግን ትምህርቷን ጨርሳ እንዳትለየውና በሌላ መልኩ ነበር ።

አንድ ቀን ያሬድ ከሥራ ተመልሶ ወደቤቱ ሲመጣ እንደተለመደው አብረው ሲስቁና ሲጫወቱ ከቆዩ በኋላ በቤቱ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሰፈነ ። ወ/ሮ በላይነሽና ያሬድ ተያይተው በዓይን ቋንቋ ሲነጋገሩ ወ/ሮ በላይነሽ ያሬድንና ሕሊናን ሳሎን ትተው « ሕሊና እንግዲህ ትምህርቱ አለቀ አሁንስ ? » አሉና ወደ ጓዳ ገቡ።

ያሬድ ሕሊናን ትኩር ብሎ በመመልከት ፈገግ አለና ዓይኖችዋን እያነበበ ሳለ ሕሊናም ይህ አስተያየቱ አዲስ ባለመሆኑ በተለመደው ፈገግታዋ አፀፋውን መለሰችለት ። አመለካከቱ የመሰያያ ቀናቸው መድረሱን የሚነግራት መሰላት ። ለያሬድ ግን ለዘለአለም አንድ ላይ የሚሆኑበት ቀን መቃረቡ እየታየው ፤ « የምረቃ ስጦታሽን በሙሉ አልሰጠሁሽም ። ዛሬ ልሰጥሽ ወሰኛለሁ » በማለት ብድግ ብሎ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባና በእጁ ሁለት ትንሽ ነጫጭ ሳጥን መሳይ ነገሮችን ይዞ ጠረጴዛው ላይ ነጣጥሎ አስቀመጣቸው ።

ቀና ብሎ ሕሊናን እየተመለከተ « በይ እንግዲህ ምረጭ » አላት ። የያሬድ ሁኔታ ግራ አጋባት ።

« ምኑን ነው የምመርጠው ? » በማለት ወደ ሳጥኖቹ መልከት አድርጋ ቀና ብላ ያሬድን አስተዋለችው ።

« ከእነኚህ ከሁለት ሳጥኖች አንደኛው ለአንቺ ነው ። መርጠሽ ውሰጅ » በማለት ሳጥኖቹን እንደዕጣ ዓይነት በማለዋወጥ ሕሊናን በሚያደነጋግር ሁኔታ አስቀመጣቸው ።

« በይ ምረጭ » አላት ::

እጇን ዘረጋችና አንደኛውን ሳጥን ብድግ አድርጋ «ይሄው» ስትል ለያሬድ እንደመስጠት ዘረጋችለት :: ያሬድ የቀረውን ሣጥን ለራሱ እየወሰደ « ከፊቸው እንጂ ምን ትጠብቂያለሽ ? » አላት በፈገግታ ::

ሕሊና የሸጦታውን ክዳን ከፍታ ውስጡ ያለውን ቀለበት እንዳየችው ትርጉሙ ወዲያውኑ ገባት :: ፊቷ በአንድ አፍታ ተለዋውጦ ዓይኖቿዋ የሀዘን ዳመና ጋረዳቸው :: አጠገብዋ የቆመውን ሰው በጥላቻ ለማባረር የተዘጋጁ መሰሉ :: ሳጥኑን እንደነበር አድርጋ ከደነችና ወደነበረበት ቦታ መልሳ በዝምታ እንባዋን እያፈሰሰች ወደ ወ/ሮ በላይነሽ ሸሸች :: ያልጠበቀችው ነገር ስለተፈጸመ የህይወቷ መሠረት የተናጋ መሰላት ::

ሌሊቱን ወ/ሮ በላይነሽ በማባበልና በማፅናናት አሳልፈው ሲነጋ በጠዋት ዕቃዋን ጠቅልላ ለጉዞ ተዘጋጀች :: ያሬድ ከሳሎን መኝታ ቤት እየተመላለሰ ዕንቅልፍ ሳይወስደው ነበር የነጋለት :: መነሳቷን ሲመለከት ወዳለችበት ክፍል ገባ :: ልታየው አልወደደችም:: አንገቷን ወደ መሬት አቀርቅራ እጆቿን እያሻሸች ቆማ ያሬድ የሚለውን ጠበቀች ::

« ሕሊና ይቅርታ አድርጊልኝ በጣም ቸኩልኩ መሰለኝ » ሲል ለመናት ::



* * *

ጊዜው መሸትሸት ሲል አዲስ አበባ አውቶቡስ መናኸሪያ ከሌሎች ተሳፋሪዎች ጋር በመሆን ደረሰች :: ወቅቱ ክረምት ስለነበረ ዝናቡ እያካፋ ፣ ሰው በየፊናው መጠለያ ለመፈለግ በመሯሯጥ ላይ ነበር :: ታክሲዎች በአካባቢው ቆመው ከክፍለሀገር የሚመጡትን እንግዶች ለመቀበል ተራ ላይ ናቸው ::

ሀሰን ጃንጥላ ይዞ አዲስ የደረሰውን አውቶቡስ የሰሌዳ ቁጥር ለማንበብ ተጣደፈ :: በሰሌዳው ላይ « ደሴ አዲስ አበባ » የሚል ፅሁፍ ነበረበት :: ወደ አውቶቢሱ ተጠግቶ ከሌሎች እንግዳ ተቀባዩች ጋር ተቀላቅሎ ፣ በሁለቱም በር የሚወርዱትን ተሳፋሪዎች ተመለከተ:: እያት የሆነ ስሜት ወረረው :: በአካባቢው ያሉትን ሰዎች እየገፈታተረ ወደፊት ሄደ :: « ሕሊና ! ሕሊና ! ቆይ እስኪ መንገድ ! ሕሊና ! እዚህ ነኝ ! ወደዚህ » ሲል ድምፁን ከፍ አድርጎ ተጣራ :: ከላይ ደረብ ያደረገችውን ነጠላ መሳይ ድሪያ ወለቅ አድርጋ የሀሰን ድምፅ ወደሰማችበት አቅጣጫ ፊቷን መለስ አደረገች ::

ሀሰን እንደ አበያ በሬ ፊቱ የቆመውን ሁሉ እያስወገደ ወደ እርሷ ሲገሰግስ አየችው :: ምንም ጊዜው ጨልሞ ለዓይን ድንግዝግዝ ቢያደርግም የሕሊናን ደስታ ለመለየት አላዳገተውም ::

« ጋሽ ሀሰን መልዕክቱን ቶሎ አገኘህ ? እኔኮ አታገኘውም ብዬ ፈርቼ ነበር :: . . . . .» አለችው ሕሊና ንግግሯን አጠር አድርጋ ::

« ሁሉም ደርሶኛል :: ስምቻለሁ :: ዕቃሽን እንሰብስብ » አላት ፣ ተረጋግቶ ለመጫወት አልተመቸውም ነበር :: ዕቃዋን በሀሰን መኪና ጭነው ጉዞዋቸውን ወደ ቤት ቀጠሉ ::

« ምነው አዲስ አበባ ናፈቀሽ ? እረፍቱን ሳትጨርሺ ተመለሽ» አላት ፣ የተወሰነ ርቀት ከሄዱ በኋላ ::

« ገጠር ምኑ ደስ ይላል ? » አለች ::

« ኮምቦልቻ ገጠር ከሆነ የምትሄጅበትስ ምን ይሆን ? »

« አባባሌ ፣ ገጠርን በመጥላት ወይም በመፍራት እንዳይመስልህ :: »

« ሒሊና የምትይው የገባኛል :: ግን ለምን እውነቱን አትናገሪም ?

« ምኑን ነው የምነግርህ ? » በቁጣ ነበር የተናገረችው ::

« አይ ሒሊና ፣ ለምን እንደ ልጅ ትሆኛለሽ ? ሁሉንም ነገር ለምቼዋለሁ :: »

« ምንድን ነው የሰማህው አለችው ግንባሯን ቋጥራ

ሀሰን የጀመሩትን ንግግር አቋርጦ « እንማማ መቼም ደጅ ቆመው ነው የሚጠብቁን አላት ::

« ውይ ! እረስቼ ሳልጠይቅህ ፣ ፋጡማ ወለደች ? »

« ያውም ባለ አራት ኪሎ ጠንበለል :: »

« እንኳን ደስ ያለህ ! » መቼም ምንም ወንድ ብትሆን ለእህትህ መጨነቅህ አይቀርም :: ደስታውን ተቀብያለሁ :: ጭንቀቱ ግን በእናንተ ቢበቃ ይሻላል :: አለ ሀሰን የመኪናውን ጡሩምባ ደጋግሞ በማጮህ :: የግቢው በር ተከፈተ :: በስንብት የተለያዩት በመሳሳም ተገናኙ :: የሒሊናን ስም የሚጠሩ ብዙ ሆኑ ::

ሒሊና ከኮምቦልቻ መልስ ሦስተኛውን ሌሊት አገባደደች :: ከሀሰን ጋርም ውል የሌለው ግንኙነት ፈጠሩ :: በጠዋት ስትነሳ በዕለቱ ከሀሰን ጋር የነበራትን የሽርሽር ጉዞ እያሰበች ነበር ::

« በጣም ነው የምትገርሚኝ » አላት ሀሰን ፤ መኪናውን ጥግ አስይዞ እያቆመ ::



« ሽርሽሩ ቦታ ደረስን እንዴ ? » አለችው የተናገረውን እንዳልሰማች ሁሉ ::

« ከመድረሳችን በፊት ትንሽ እንነጋገር ብዬ ነው :: ሒሊና ለምን ነበር ያኔ የደበቅሽኝ እስኪ በአባትሽ ንገሪኝ :: »

« ምኑን ? »

« ከያሬድ ጋር ስለነበራችሁ ግንኙነት ? »

« ታዲያ የደበኩህ የትኛውን ነው ? »

« እሺ ፤ ግን ለምን ተቀያየማችሁ ? ምስጢር ካልሆነ ብትነግሪኝ ? »

« ምን ያደርግልሃል ? ጋሼ ያሬድ የነገረህ አይበቃም ? »

« እሱማ ያለኝ እም . .ም. .ም» ቃላቶቹን ለማውጣት ተናነቀው ውስጡ ነደደ ::

« በቃ ! ተይው ምን አስጨነቀን » አላት በስጨት ብሎ ::

« ታዲያ ምን አበሳጨህ ? » አለችው በግርምት

« እንዴት አልበሳጭ ሒሊና ? » ሒሊና እንዴት አይገባሽም ? ያሬድኮ ጓደኛዬ ነው :: ይህን ሀሳቡን ቀደም ብሎ ቢነግረኝ ኖሮ ለሁላችንም ጥሩ ነበር :: የዛን ቀን የነገረኝን ለማመን አልቻልኩም :: እንዴት ብዬ ልግለፅልሽ ሒሊና » ከመምህሩ መልስ የሚጠብቅ ተማሪ መስሎ ነበር የጠየቃት ::

« እኔ እንጃ » አለችው ::

« አይ ሒሊና ! ሒሊና ! እንዴት አድርጌ ላስረዳሽ ? » በማለት ወንበሩ ላይ ደገፍ ብሎ ወደ መኪናው ጣሪያ ተመለከተ ::

እጇን ወንበሩ ላይ አሳርፋ በመንተራስ ፊቷን ወደ ሀሰን መልሳ በትኩረት እንቅስቃሴውን አየች :: ጭንቀቱ ከየትኛው አቅጣጫ እንደመነጨ ለማወቅ የነበራት ጉጉት በውስጧ ይበልጥ እያንሰራራ መጣ :: ግን እሷ ቀድማ ልታነሳ አልፈለገችም :: ሀሰን በቀጥታ ለሚጠይቀው ጥያቄ መልስ ራሷን አዘጋጀች ::

« ስሚ ሕሊና ያሬድን አላገባም አልሽ ፡፡ ለምን ብዬ መጠየቅ አግባብ የለውም ፡፡ የሆነው ሆኖ ፡፡ ከነጭራሹ ሳታገቢ ትኖሪያለሽ ብዬ አላምንም » አላት ፡፡ « ጋሼ ሀሰን ፣ ሀሳብህ ይገባኛል ፡፡ ለእኔ እንደ ጋሼ ያሬድ በሁለንተናው ምቹ የሆነ ባል ማግኘት አልችልም ፡፡ ነገር ግን ጋሼ ያሬድ ለሰራልኝ ውለታ አፀፋውን በጉዳት እንድመልስለት አልፈልግም ፡፡ እሱ ጥሩ ባል ሲሆን ይችላል ፡፡ እኔ ግን ለሱ ጥሩ ሚስት ለመሆን መቻሌን እጠራጠራለሁ ፡፡ » አለችው፡፡

የመጀመሪያ ፍቅር መቼም በደስታ ባህር እንደመዋኘት ሊያጓጓ ይችላል ፡፡ ፍቅር ሲያረጅና ቀኑ እየረዘመ ሲሄድ እየቀዘቀዘ ያልፋል ፡፡ በወንድምነትና በእህትነት የዳበረውን መውደድ በአዲሱ የባልና የሚስት ፍቅር ሲተካ እንዳይጠወልግብን ፈራሁ ፡፡ ለምሳሌ እንበል ጋሼ ሀሰን አሁን ፋጡማን አግባ ቢሉህ እሺ ትላለህ ? » አንገቷን ሰብር አድርጋ አየችው ፡፡

« ምን ማለትሽ ነው ? እንዴት ተደርጎ ? » ዓይኑን ጨፍኖ እራሱን እየነቀነቀ ቀጠለ « ሕሊና እዚህ ላይ ተሳስተሻል ፣ የፍቅርን ምስጢር የተረዳሽ አልመሰለኝም ፡፡ ለጤነኛ ባልና ሚስት ፍቅር እንደ ጤዛ አይረግፍም ፣ አይጠወልግም ፡፡ ፍቅር በዕድሜ ከአንዱ አይነት ወደ ሌላው ይሸጋገራል » ተክዛ የምታየውን ሕሊናን ትኩር ብሎ በመመልከት ነበር ያሚናገረው ፡፡ « ሕሊና ለሁሉም ሂደት ዕድሜ አለው ፡፡ ዕድሜ ያልተገኘለት ለራሱ ለጊዜ ብቻ ነው ፡፡

« ጋሼ ሀሰን ፣ ጋሼ ያሬድን በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ አስበልጬ እወደዋለሁ ፡፡ ነገር ግን ይህ መውደድ ለሱ እንደገባው ለእኔ አልተከሰተልኝም ፡፡ እንግዲህ ጋሼ ያሬድ እንደተመኘው ሁሉ ለማድረግ ወንድምነቱን ፍፁም መርሳት ይኖርብኛል ፡፡ ወንድምነቱን ትቼ ፍቅሩን ሳውቅ ያኔ ለሚስትነት እበቃ ይሆናል ፡፡ ጊዜ የማይሽረው ትዝታ የለም ፡፡ ከሀዘኑ እንዲፅናና እሰላ እንደደረስኩ ደብዳቤ እፅፍለታለሁ » አለችው ፡፡



# ምዕራፍ አምስት

ሕሊና ከሀሰን ጋር ከአዲስ አበባ ተነስታ አሰላ ገባች ፡፡ አብረው አካባቢውን ተዘዋውረው ጎበኙ ፡፡ « ደስ የምትል ከተማ ነች» አለ ሀሰን አካባቢውን ዞር ዞር ብሎ እያየ ፡፡

« ከተማውስ ደስ ማለት ደስ ይላል ፤ ግን ምን እንደሆነ አላውቅም ብቸኝነት ፣ ባዶነት ይሰማኛል » አለችው ፡፡

« አዲስ ቦታ ሲገቡ ሁልጊዜ ማንኛውም ሰው የሚሰማው ስሜት ነው ፡፡ አይዞሽ ፤ እየቆየሽ ስትሄጂ ትለምጃለሽ » አለ ሀሰን በማፅናናት መልክ ፡፡ ግን ሕሊና ራሷን ማፅናናት አልቻለችም ፡፡ የሀሰን ንግግር ይበልጥ ሆዷን አባባው ፡፡ ሳታስበው እንባዋ ገነፈለ ፡፡ ሀሰን የራሱ ስሜት እየታገለው ፤ ሕሊናን ለማበረታታት ሲል ወደ ውስጥ ለመዋጥ እየጣረ « ደስ ሲልሽ ሲገባ ማልቀሱን ምን አመጣው ሕሊና ? ! » ሲል የቁጣ ዓይነት ንግግር ተነፈሰ ፡፡ « ወድጄ አይደለም ሀሰን ፡፡ ዝም ብሎ እምባዬ ይመጣል ፡፡ ላለማልቀስ ወስኜ ነበር ግን እንባዬን ልገታው አልቻልኩም » አለችና ሁለት እጆቿን ፊት ለፊቷ ዘረጋች ተስፋ በመቁረጥ መልክ ፡፡ ሀሰን እጆቹን በደመነፍስ ዘረጋላት ፡፡ የሚያደርገው ሁሉ ከቁጥጥሩ ውጪ ነበር ፡፡ በሕሊና ፊት ላይ እየገነፈለ የሚፈሰውን እንባዋን በእጆቹ ጠራረገላት፡፡ ፊቷን ወደ ራሱ ጠጋ አድርጎ ጉንጯ ላይ ሳም አደረጋት፡፡

እጆቹን በአንገቷ አሳልፎ አቀፋት ፡፡ ሕሊና እንደ ህፃን ልጅ ፊቷን አንገቱ ስር ቀብራ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ፡፡ ከቆይታ በኋላ ከህልሟ የነቃች ይመስል ሀሰን በሰጣት መሀረብ ፊቷን እየጠራረገች ፤

« አሁን ደህና ነኝ . . . እንሂድ » አለች ፡፡

ሀሰን መኪናውን አስነሳ ለመንዳት ግን አልሞከረም ፡፡ ለጥቂት ጊዜያት የሕሊናን ፊት በዓይኖቹ ዳሰሰ ፡፡

« መቼም ያሬድ ላይ አልፈርድበትም » አለ ሰራሱ በመናገር መልክ ። ዓይኖቿ ከዕንባ ያልፀዱት ሕሊና ሀሰንን በፈገግታ ገርመም አደረገችው ። በመሀከላችው ዝምታ ሰፈነ ። ሀሰን ወደ ሕሊና ፊቱን ሳይመልስ መንገድ መንገዱን አያየ ሰብዙ ጊዜ ነዳ ። በሀሳብ ተውጦ ነበር ። ከሕሊና ጋር የተፈጠረው ስሜታዊ መቀራረብ እውን ሆኖ ታየው ። ያሬድን አሰበው ። በደፈናው እንደሚወዳት ነው የነገረው ። እሷም ወንድሜ ነው ብላዋለች ። ከዚህ በላይ ምን ማወቅ ያስፈልጋል ? እራሱን ለማሳመን ሞከረ ።

« እኔ አላምንም ! ከእንግዲህ እዚህ አዲስ ከተማ አዲስ ህይወት ጀመርኩ ማለት ነው ? » ስትል ሕሊና እራሷን ጠየቀች ።

« አይዞሽ ! እንዲህ እየተባለ ነው የሚለመደው » አላት ሀሰን ቃሉን ከፍ አድርጎ ፤ እኔም ለሦስት ቀን ከአንቺ ጋር ነኝ « እውነትህን ነው ? » ስትል በጉጉት መልክ ጠየቀችው ።

« አዎ እውነቴን ነው አንቺን ደስ የሚልሽ ከሆነ ? » አለ ሀሰን በጥያቄ መልክ ። « በጣም ነው ደስ የሚለኝ » አለች በረጅሙ ተንፍሳ ጭንቀቷን በመገላገል ዓይነት ። ሕሊና የተከራየችው ጠበብ ያለ ሁለት ክፍል ያለው ቤት ነው ። ጐረቤቶቿ እንግዳ መሆኗን ስላወቁ የተቻላቸውን ድጋፍ ለመስጠትና ለማለማመድ ሞከሩ ። የሕሊና ጐረቤቶች ብዙዎቹ መምህራን ናቸው ። ሕሊና ጥቂቶቹን በት/ቤት አካባቢ ተዋውቃቸዋለች ። መምህርት ከበቡሽ ከሕሊና ቀደም ብላ ከአንድ ዓመት በፊት ከኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ ተመርቃ በአርሲ ክፍለ ሀገር አርባ ጉጉ ከተማ ተመድባ ለአንድ ዓመት ስታስተምር ከቆየች በኋላ የዝውውር ዕድል አግኝታ አሰላ ተመደበች ።

ከሕሊና ጋር በማሰልጠኛ ት/ቤት በዓይን ይተዋወቁ እንጂ ንግግር አልነበራቸውም ። የመምህራን የትውውቅ ስብሰባ ተጠርቶ መምህራን በመሰብሰብ ላይ እንዳሉ ሕሊና ከከበቡሽ ጋር ተገናኘች ።



በፊት በዓይን ከመተያየት በስተቀር ቅርርብ አልነበራቸውም ። አሁን ግን ሲተያዩ እንደአብሮ አደግ ጓደኛሞች ተቃቅፈው ተሳሳሙ። ቀጥላ ከሁለት ወንድ መምህራን ጋር ተዋወቀች ።

« አበራ » ፣ « ታከለ » ብለው ተዋወቋት ።

« መቼም ይህ ይሆናል ብዬ አልጠበኩም » አለች ከበቡሽ ፈገግታ በፈገግታ ሆና ።

« ይኸውልሽ የማያልቅ ነገር የለም ትምህርቱን ጨርሼ እዚህ ተመደብኩ » አለች ሕሊና ።

« መቼም ዕድለኛ ነሽ ቀጥታ እዚህ መመደብሽ ። . . . . »

« ወደ ስብሰባ ክፍል ! ወደ ስብሰባ ክፍል ! » በማለት እጃቸውን ያጨበጨቡት ምክትል ርዕስ መምህሩ ነበሩ ።

« አሁን ታዲያ የት አረፍሽ ? » አለች ከበቡሽ ።

« ቤት ተከራየሁ እነ መምህር ድሪባ ሠፈር » አለች ሕሊና ።

« እንዴ ምን ማለትሽ ነው ? ከግራ ሦስተኛው ክፍል የእኔ ቤት እኮ ነው ። እኔ አላምንም » አለቻት ከበቡሽ ።

« ታዲያ ዕቃዬን ሳጓጉዝ ለምን አላየሁሽም ለማደሩ እንኳ ዛሬ የመጀመሪያ ቀኔ ነው » አለች ሕሊና ።

« ሰሞኑን ሠፈር ውስጥ አልነበርኩም ። አዳሬም ውሎዬም ውጪ ሆኗል ። » አለች ከበቡሽ ፤ ፊት ለፊቷ የተቀመጠውን አበራን በዓይኗ እየቃኘች ።

የት/ቤቱ አጠቃላይ ስብሰባ የዓመቱ መጀመሪያ በመሆኑ አጠር ያለ ውይይት ነበር ። ዓላማውም አዲስና ነባር መምህራንን የት/ቤት የሥራ ዘርፍ ማስተዋወቅና የአዲሱን ዓመት የትምህርት አጀማመር ፕሮግራም ያጠቃልላል ። ከስብሰባ በኋላ ለመምህራን ነፃ ጊዜ ተሰጥቶ የግል መሰናዶ እንዲያደርጉ ርዕስ መምህሩ ፈቀዱ ።

« እንደ ድሮ መስሎሻል ። አሁንማ ተግ ብዬ አታይም አሰባበሴም አነጋገሬም ተለውጦ ። » አለች ከበቡሽ የለበሰችው ረዥም

ቀሚ.ስና የተጫመተችው ነጠላ መሳይ ተረከዝ አልባ ጫማ ለሕሊና እያሳየች ::

« አየሁ እኮ :: መጀመሪያ ሳይሽ እንኳ ሳላውቅሽ ጥቂት ጊዜ ፈጅቶብኝ ነበር :: ቢሆንም ያምርብሻል :: » አለቻት ሕሊና የከበቡሽን ስሜት እንዳትጎዳ በፍርሃት ዓይነት ::

« አምሮብሻል ! ሕሊና አብደሻል እንዴ ? ምን ያምርብኛል የገጠር ኑሮ ሰባብሮኝ :: አይዞሽ አትፍሪ እውነቱን ብትነግሪኝ አይቆርጠኝ ፤ አይፈልጠኝ :: ድሮ እንደ መጣሁ ነበር ቀን ከሌሊት ለቅሶ :: አንድ ወቅትማ ሥራውን ሁሉ ትቼ ከዘመዶቼ ጋር ተቀላቅዬ ልረፈው ብዬ ነበር :: ለሁሉም ልምድ ያላቸው መምህራን ምክር አዳነኝ » አለች ከበቡሽ አጠገቧ አብሯት በመራመድ ላይ ያሰውን አበራን በፈገግታ እየተመለከተች ::

« ምን ታይኛለሽ ? አንቺ ራስሽ ቀላል ሰው ነሽ እንዴ . . . እኛ ቢበዛ የሞራል ድጋፍ እንጂ ምን አደረግን ? » አለ አበራ ውለታውን በማቃለል ዓይነት ::

« የሞራል ድጋፍ እኮ ነው ትልቁ ነገር ! ሌላው ሁሉ ሁለተኛ ደረጃ ነው :: » አለች ሕሊና ::

« በሉ እንግዲህ እራት ዛሬ እኔ ጋ ነው የምንበላው :: ከአሁኑ ልንገራችሁ ብዬ ነው :: ሁላችሁም እንድትመጡ ተጋብዛችኋል » አለች ከበቡሽ ::



*　　*　　*

ወይዘሮ በላይነሽ በያሬድ እርዳታ በመጨረሻው የአሰላ በራሪ ተሳፍረው ጉዞአቸውን ቀጠሉ :: ዕድሜ የተጫናቸው አዛውንት አጠገባቸው የተቀመጡትን ወ/ሮ መኪናው በቆመ ቁጥር « የት ነው ያለነው ? ይህ ከተማ ማን ይባላል ? » በማለት ለመረዳት እየሞከሩ አቃቂ ሲደርሱ የእርሳቸውና የሕሊና የአቃቂ ጉዞ ትዝ አላቸው :: ወ/ሮ አባይነሽም አቃቂ በሀይወት እንዳሉ ከያሬድ ሰምተው ነበር ::

« ምንኛ የታደሉ ናቸው » ብለው ስለወይዘሮ አባይነሽ አሰቡ:: በዓለም በደስታ ኖረው ሲበቃቸው ደግሞ በቃኝ ብለው መነኮሱ :: እግዚአብሄር ለንሰሀ አበቃቸው :: » አሉና መልሰው የራሳቸውን ሁኔታ አሰላሰሉ :: ከሕሊና ጋር በዓይነ ሥጋ ከተገናኙ ዘጠኝ ወራት አለፈ :: አልፎ አልፎ ያሬድ ለሕሊና የሚፅፍላትን ደብዳቤ ያነብላቸዋል :: የሱን ሀሳብ ሰምተው ፤ የግላቸውን ስሜት ውጠው ያለምንም ተጨማሪ አስተያየት መለያየትን ልምድ አድርገውት ነበር ::

ለወ/ሮ በላይነሽ የያሬድና የሕሊና ጥል ግልፅ ነበር :: ጣልቃ መግባቱ ነገሩን ማባባስ መስሎ ስለታያቸው ጉዳዩን በውስጣቸው እያመነዠኩ ኖሩ :: ያሬድ ከእርሳቸው ጋር ያለው ግንኙነት አልተለወጠም :: ሆኖም የሕሊና ሥም በየምክንያቱ በተነሳ ቁጥር የያሬድ ስሜት መልካም እንዳልነበረ ያውቁታል :: ሕሊናን ለማየት በጉጉት እየጠበቁ ፤ በሀሳብ ተውጠው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ::

« ዕቃዎቻችሁን ፤ ቦርሳና ሻንጣዎቻችሁን ሸክፉ ፤ አሰላ ደርሰናል:: » በማለት ግራና ቀኝ እየተመለከተ ወደ ወይዘሮ በላይነሽ አመራ የሾፌሩ ረዳት ::

« እማማ አሰላ ማለት ይሄ ነው :: ልጅዎ አደራ ብሉኛል ::

አደራ በላተኛ እንዳልሆን ። » በእጃቸው ይዘውት የነበረውን ቋጠሮ ተቀበላቸው ። ከመኪናው በመውረድ ላይ እንዳሉ ሕሊና ሮጣ አቀፈቻቸው ።

« እማማ በላይነሽ ! እኔ አላምንም . . . » ወ/ሮ በላይነሽ መናገር አልቻሉም ። ተቃቅፈው ተላቀሱ ። አገላብጠው የሕሊናን ፊት ቃኙ ። ሕሊናም አፀፋውን መለሰች ።

« ጎብዘዋል እዚህ ድረስ ብቻዎትን መጡ ! » አለች ሕሊና እፏን በእጇ ይዛ ያየችውን ባለማመን ።

« ሕሊና አንቺ በህይወት እስካለሽ እኔ ምን እሆናለሁ ። ብቻ እግዚአብሄር ውለታሽን ይክፈልሽ ። . . . ሳይደግስ አይጣላም ። » አሉ በተቆራረጠ ስሜት ሕሊናን በስስት እየተመለከቱ ።

« እርሶም እኮ እማማ በላይነሽ ለእኔ እናቴም አባቴም ነዎት። ስለእኔ እርሶዎ የሚያውቁትን ያህል ማን ያውቃል ? በሞት እና በህይወት መካከል እያለን ፤ አባቴና እኔ ቤትዎትን እንደቤታችን አድርገን ፤ በሉ ይተውት በሉ ይተውት ! . . . » ሕሊና ፊቷን ወደምድር ደፋች ።

« በይ እንግዲህ ያለፈው አለፈ ፤ ተመስገን ነው የሚባለው » አሉ የሕሊናን እጆች በእጃቸው ይዘው ። « ጥሩ ቤት አግኝተሻል ። ደግሞ እውቶብስ ማቆሚያ አጠገብ ። ሀገሩም ጥሩ ነው ። የስንዴና የቅቤ ሀገር መሆኑን ድሮ እሰማ ነበር ። » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ ሕሊናን ከገባችበት የሀሳብ እዘቅት ለመመለስ በመጣር ።

« ሀገሩስ ደህና ነው ። ግን ከእናንተ ተለይቼ እርቄ መኖሬን በጣም ነው የጠላሁት ፤ ምን ያደርጋል ? » አለች ሕሊና ።

« እሱም እግዚአብሔር ይስጠው ፤ አዲሳአበባ ድረስ ነድቶ አደረሰኝ ። » አሉ ስሙን ሳይጠቅሱ ። ያሬድ ማለታቸው ነበር ።

« ለመሆኑ ደህና ነው ? እስካሁን ሳልጠይቅዎት » አለች ሕሊና መልሱን ከንግግራቸው ይልቅ ከገፅታቸው ለማንበብ በመጣር።



« በጣም ደህና ነው ። ወደዚህ መምጣቴን እንዳወቀ ዛሬ እፅፋለሁ ነገ ሲል ሥራ በዝቶበት ጊዜም አላገኝም ። » በማለት በፍጥነት ፊታቸውን ከሕሊና አዞሩ ።

« ወደ እዚህ ልመጣ ስል ፤ ሴሊቱን በሙሉ ወረቀትና ብዕር ይዞ ምግብ ቤት ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ አደረ ። ጠዋት ተነስተን ወደ አዲስ አበባ ስንመጣ የፃፈው ለአንቺ ከሆነ ይሰጠኛል ብዬ ጠብቄው ነበር ግን የሰጠኝ ነገር አልነበረም » አሏት ። ቀጥለውም « የአክስትሽን የእማሆይን ወሬ ትሰሚያለሽ ? » ሲሉ ጠየቋት ።

« አዎ እሰማለሁ ። ሁለት ጊዜ ሄጄ አይቼአቸዋለሁ ። አሁን ወደ ቤተክርስቲያን ተጠግተዋል ። ከተማ ለመኖር አልፈልግም አሉ። ለጤናቸው በጣም ደህና ናቸው ። » አለች ሕሊና እፍንጫዋን በእጇ መዳፍ እየጠራረገች ።

ወ/ሮ በላይነሽ ከያሬድ ተለይተው ሕሊና ጋር መኖር ከጀመሩ አራት ወራት አለፉ ። በእነኚህ ወራቶች ውስጥ የሕሊና ህይወት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ቢጥሩም ፤ ካወቁአቸው ነገሮች የኑሮዋ ምስጢር እንደሚበዛ ገመቱ ።

ሕሊና አልፎ አልፎ ቅዳሜና እሁድ እሳቸው እንዳይሰጉ አፅናንታ ፤ የምትመለስበትን ጊዜ ነግራ ፤ ለአዳር ከመውጣቷ ውጪ የሚያውቁት ነገር አልነበረም ። ሆኖም ከጓደኛዋ ከከበቡሽ ጋር ሲያወሩ ለጆሮአቸው የሚደርሳቸው ወሬ ይቀፋቸው ነበር ። ስለሁሉም ነገር አንስተው ለመጫወት ብዙ ጣሩ ። ሆኖም ጊዜ ሲኖራት ሕሊና ብቻዋን ሆና አታውቅም ። ከበቡሽ ስትጠፋ አበራ ፤ አበራ ከሌለ ደግሞ ታከለ ወይንም ሌሎች መምህራን ከጎረቤት እየመጡ አስቸገሯቸው ።

« ሕሊና መሄጃዬ እንግዲህ እየተቃረበ ነው ። ያሬድ ቶሎ እንድመለስ ነግሮኝ ነው የሸኘኝ ። በወጉ ሳናወራና ሳንጫወት ጊዜው አለፈ ። እኔ መቼም አንድ ቀን እንኳን ያደርኩ አልመሰለኝም ። »

ሲሉ ወ/ሮ በላይነሽ መውደዳቸውንም ቅሬታቸውንም ገለጹ ። ሕሊና በሰማችው ተደናግጣ ያነሳችውን ቦርሳ ጥላ አጠገቧ ወደ አለው ወንበር ተራምዳ ተቀመጠች ።

« ለምን ይሄዳሉ ? እኔ እኮ ወደዚህ የመጡት ከእኔ ጋር ይኖራሉ ብዬ ነበር ። ምን ተፈጠረ ? » በማለት ሕሊና ጠየቀች ።

« ልጄ ! ምንም ነገር አልተፈጠረም ። መጀመሪያ አመጣጤ ለሦስት ወር ብቻ ካንቺ ጋር እንድቆይ ነው » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ ጥቂት አሰብ አድርገው ። « ያሬድም ፈቃድ የሰጠኝ ለሦስት ወር ነበር ። ይኼው አሁን አምስተኛ ወሬን ይዣለሁ ። » ብለው ወንበር ላይ አረፍ አሉ ።

« ምርጫዎ እርሱ ከሆነ እንግዲህ ምን አደርጋለሁ » አለች ሕሊና ስለማን እንደምትናገር ድፍን አድርጋ ።

« ልጄ ! ልጄ ! ምርጫዬስ አይደለም ግን ቃል ቃል ነው ። እንደምመለስ ነግሬዋለሁ ። » አሉ የሕሊናና የያሬድ መጨረሻ እንዲህ መሆኑ ውስጣቸውን እየበላቸው ። ለተወሰነ ጊዜ በቤቱ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ ። ወ/ሮ በላይነሽ ወደ ሕሊና ቢመለከቱም ሕሊና ግን ዓይኖቿን አሸሸች ። እጇን ጨብጣ ማለት የምትፈልገውን በውስጧ አምቃ ያዘች ።

« ልጄ ሆይ ሕሊና መቼም ተራራቅን እንጂ አልተለያየንም ፤ ፍላጎትሽ ምን እንደሆነ ይገባኛል ። አሁን ጉልበቴ ዝሎ አልታዘዝ አላለኝም ። ሠርቼ መብላቱን አላቆምም ። ግድ የለሽም የጡረታዬ ጊዜ ሩቅ አይደለም ። ያኔ እስለችሻለሁ ። » አሉ ሕሊናን ለማረጋጋት በመፈለግ ። « ይልቁንስ ፈጠን ፈጠን ብለሽ ባሉን አምጪና ሠርጉን ልደግስ ። »

« አይ እማማ በላይነሽ ፤ እኔ የሚገርመኝ ይህ ደግ ልብዎ ዕድሜ በጨመረ ቁጥር እየታደሰና እየጎለበተ ነው የሚሄደው ። » አለች ሕሊና መርበትበቱ ትቷት ፈገግታ ተላብሳ ።



« ይልቁንስ በይማ ንገሪኝ እርሱ ማን ነው ? » ብለው ጠየቁ። ሕሊናን በትኩረት እያዩዋት ። ሕሊና መልስ መስጠት አልቻለችም ። መሬት መሬቱን እያየች ፤ እጇን እያፍተለተለች በሁለት ጉልበቶቿ መሀከል ጨብጣ ያዘች ። ወ/ሮ በላይነሽ ጉዳዩ እንዳስጨነቃት ተረዱ ።

« ልጄ ግድየለም ለመንገር ካልፈለግሽ ። » በማለት ከተቀመጡበት ለመነሳት ሞከሩ ። ሕሊና በእጇ ይዛ ከተቀመጡበት እንዲቆዩ ጋበዘቻቸው ።

« ለመንገር አለመፈለግ አይደለም ፤ ብነግርዎት ደስ አይልዎትም ብዬ ነው ። » አለች ሕሊና በሀፍረት ዓይነት ።

« ልጄ አንቺ ያደረግሽው ደግሞ ምኑ ይጠላል ። ግድ የለሽም ተናገሪ ልስማው » አሉ ። ፊታቸውን አስገው በጉጉት መልክ ወደ ሕሊና እየተመለከቱ ።

« ያውቁታል ! » ከማለቷ ወ/ሮ በላይነሽ ኩምሽሽ አሉ ። ላፍታ ሁኔታቸው ተለዋወጠ ። የሰሙትን ባለማመን አንዳች ነገር እንደጠፋበት ሰው ከግራ ወደ ቀኝ ቃኙ ።

« ጠርጥሬያለሁ አንቺና ጓደኛሽ ስታወሩ ። ሀሰን የእኛው ነው ? » ከንፈራቸው እየተርበተበተ ፤ ምላሳቸው ተሳስሮ ወ/ሮ በላይነሽ የጠሩትን ሥም በግድ ተናገሩ ። ሕሊና አንገቷን ወደመሬት ደፋች ።

*  *  *

ወ/ሮ በላይነሽ ከአሰላ ወደ ያሬድ ተመለሱ ። ሕሊና ከወ/ሮ በላይነሽ ጋር መለያየቱ ከባድ ሆኖ ብታገኘውም ቅሉ ከሀሰን ጋር ለጀመረችው ግንኙነት ብቸኝነቱ ስለሚሻላት ተፅናናች ። ሆኖም ከእንግዲህ ከሀሰን ጋር ያላት ግንኙነት ለብዙ ጊዜ ምስጢራዊ ሆኖ እንደማይቆይ ተረዳች ። ወ/ሮ በላይነሽ ለእርሷ ባላቸው አክብሮትና ፍቅር ሲሉ ጉዳዩን በሽማግሌ ለማስተካከል ሀሳብ አቅርበው ነበር ። ሆኖም ሕሊና የእርሷንና የያሬድን መቀያየም ከእነ ምክንያቱ የግል ምስጢሯ አድርጋ በመውሰድ ሽማግሌ በመላክ ላይ አልተስማማችም ። በሌላ በኩል ደግሞ በእርሷና በሀሰን መሀከል ያለው ግንኙነት ሊያብብና ሊፈካ አልቻለም ። በቤትና በአልቤርጐ ብቻ ተወስኖ መቅረቱ አሳሰባት ።

ሕሊና አንድ ቅዳሜ በሀሰን ጋባዥነት ወደ አዲስ አበባ መጣች። ሀሰን ሕሊናን ከአውቶቡስ ተራ ተቀብሎ ወደ ሾላ ጉዞአቸውን አቀኑ ።

« ዛሬ በጣም ነው አውቶቡሱ የዘገየው ምነው ምን አጋጠማችሁ ? » ሲል ጠየቀ ሀሰን ወደ ሕሊና ሳይዞር ፣ የሚሄድበትን አቅጣጫ ላለመሳት ።

« የግል መኪና መሰለህ አውቶቡስ እኮ ነው ። » አለች ኮስተር ብላ ፣ መቀመጫዋ ላይ እየተስተካከለች ።

« እንዲያውም ላለመምጣት ወስኜ ነበር ። አንተን ላለማስቀየም ብዬ መጣሁ እንጂ ። » እኔ እኮ ለአንቺ በማሰብ ነው ! ለምን ዘገየ ብሎ መጠየቅ ይህን ሁሉ ውርጅብኝ አያስከትልም ። »



ሀሰን በፈገግታ ሕሊናን አየ ። እጁን በሕሊና ትከሻ ላይ ጣል አደረገ ። ሕሊና ትከሻዋ ላይ ያረፈውን የሀሰንን እጅ በቀስታ አስወገደች ። ቀሪው የሾላ መንገዳቸው በዝምታ ተውጦ አለፈ ።

« ዛሬ ላስመብላት የወሰንሽ ይመስላል ። » አለ ሀሰን አልጋው ጫፍ ላይ ወደተቀመጠችው ሕሊና እየተመለከተ ።

« እስከመቼ ነው ዝም የምንባባለው ? ምን ተፈጠረ ? ኧረ አንድ በይ እንጂ ! » ብሎ ጉንዋ ሄዶ ተቀመጠ ። ክንዱን አንገቷ ላይ አሳረፈ ። ዓይኖቿን በዓይኖቹ ፈለገ ። ሕሊና በሀሳብ ርቃ ስለነበር አልሰማችውም ። በዓይኗ ገርምማው እጁን አስወግዳ ከተቀመጠችበት ተነስታ በነጭ ስስ መጋረጃ ወደ ተሸፈነው መስኮት በቀስታ አመራች ። ሀሰን ተስፋ ባለመቁረጥ ተከተላት ። እኮ በይ እንጂ ምን አደረኩ ? አለ ለሁለተኛ ጊዜ ። ድንገት ፊቷን ወደ ፊቱ መለሰች ። ዓይኖቻቸው ተፋጠጡ ።

« እስቲ ንገረኝ በርግጥ ትወደኛለህ ? » ስትል ጮኸችበት ።

«አዎ እወድሻለሁ። ምን ዓይነት ጥያቄ ነው የምትጠይቂኝ?» የሀሰን ዓይኖች ተርገበገቡ ። ከንፈሮቹ ተርበተበቱ ።

« በእርግጥ እወድሻለሁ » አለ በለሰለሰ ድምጽ ። ዓይኖቹን ከድኖ ወደ ሕሊና ተጠጋ ። ከንፈሩ ከከንፈሯ ፣ ትንፋሹ ከትንፋሿ ጋር ተዋሃደ ። ስሜታቸው አሸንፏቸው ተያይዘው አልጋው ላይ ወደቁ ። ያነሱትን ጉዳይ ረሱ ። አካላቸው አንድ ሆነ ። እኩል ሌሊት አለፈ ። ሕሊና አልጋው ላይ ተጋደመች እንጂ ዕንቅልፍ አልወሰዳትም ። የእርሷ መገላበጥ ደግሞ ሀሰንን ዕረፍት ነሳው ። ድካሙና የሰውነት ዝለቱ አለቀቀውም ።

« ምነው አልደከመሽም ፣ ለምን አትተኚም? በማለት ተንጠራራ ። ፊዘዝ ባለው መብራት የሒሊናን ፊት ለማየት ሞከረ ።

« ዕንቅልፍ እንቢ አለኝ » አለች ። ፊቷን ወደ ግድግዳው አዙራ ጀርባዋን ለሀሰን ሰጠች ።

« ምን እያሰብሽ ነው ? ለምን ብቻሽን ትጨነቂያለሽ ? » ሀሰን የራሱ ጥያቄ ከእንቅልፉ ሙሉ ለሙሉ አነቃው ።

« ሀሰን ምንም ሳትደብቅ ንገረኝ ፣ እማማ በሳይነሽ አሰላ ከመጡ በኋላ እንደድሮህ አይደለህም ። እመጣለሁ ብለህ ትቀራለህ ። እኔ ካልደወልኩ ስልክ እንኳን መደወል ትተሃል ። ይህ ከምን የመጣ ነው ? » በማለት ፊቷን በእጆቿ አንተርሳ ወደ ሀሰን ተመለከተች ። ሀሰን ለጥያቄዋ መልስ ለመስጠት አልቸኮለም ። ጥቂት አሰብ አድርጎ ፣

« ሒሊና ምክንያቱን ደግሜ ደጋግሜ ነግሬሻለሁ ። ሥራ ስለሚበዛብኝ ነው ብዬሻለሁ ። የሌለ ምክንያት አልፈጥር ፣ እንግዲህ ምን ብዬ ልንገርሽ ? » አለ ትርጉም በማይሰጥ አመለካከት ሒሊናን እያስተዋለ ።

« ድሮም ሥራ ይበዛብኛል ትላለህ ፤ ሆኖም የአሁኑ ለብቻው ነው » አለች የተናገራትን ባለመቀበል ። « እንግዲህ ከዚህ የበለጠ ምንም ማድረግ አልችልም ። በሌለ ነገር መጨነቅ ከፈለግሽ መቀጠል ትችያለሽ » አለ ሀሰን ቆጣ ብሎ ። ፊቱን ከሒሊና አዙሮ ራሱን ለመኝታ አመቻቸ ።

« እሺ ያልከውን ልቀበለው ፣ ነገር ግን ለምንድነው የእኛን ግንኙነት ጋሼ ያሬድ እንዲያውቅ የማትፈልገው ? » አለች ። « ዛሬ



ሒሊና ምን ነካሽ ? ደግሞ ምን ብዬ ነው የምነግረው ? እሱ፡ እንቺም አስቢው » በማለት ቆጣ ብሎ መለሰላት ። « ምንም አልነካኝ ። ምን የነካኝ ይመስልሃል ? ያለውን የተደረገውን ለምን አትነግረውም ነው ያልኩት ። ጓደኛህ ነው ። እኔም ሆንኩ አንተ ልናከብረው ይገባል » አለች እሷም ቆጣ ብላ ።

ሀሰን ሒሊናን ረሳና ውስጡን ለማየት ሞከረ ። አልጋው ላይ በጀርባው ተንጋሎ ዓይኖቹን ኮርኒሱ ላይ ተክሎ በሀሳብ ተዋጠ ። ውስጡ የሒሊና ሀሳብ ትክክል እንደሆነ ሹክ አለው ። ግን እውነት አይደለም ። ሒሊናን ከድብብቆሽ ጨዋታ በላይ እጅግም አስቧት አያውቅም ። ስለትዳር ፣ ስለቁምነገር ባሰበ ቁጥር ሙና ትመጣበታለች ። የያሬድ ጉዳይ ያሳስበዋል ፤ ለሒሊና ይፈራል ።

* * *

ፊንጠር ካለው ወንበር ላይ ተቀምጦ በሳሎን በር በኩል የሚወጣ የሚገባውን ሰው በታዛቢነት የሚመለከት ይመስል ነበር ። የቀረበለትን ለስላሳ ለማንሳት እጁን ሲዘረጋ ከአስተናጋጅዋ ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጩ ። በሀፍረት ፈገግታ ፊቷን አድምቃ የሚስለመለሙ ዓይኖቿን የግዷን ከዓይኖቹ ላይ ነቀለች ። ግራ በመጋባት ለአፍታ ቆም ብላ ወደሚቀጥለው እንግዳ አመራች ። የመስፍን ዓይኖች አብረዋት ተንከራተቱ ።

የመስፍን የቤት እያት ወ/ሮ ባልከፋሽ ካረፉ አራተኛ ቀናቸው ነበር ። ለመስፍን ከመላ ቤተሰቡ ጋር በመሆን ለሀዘን ተካፋይነት የመጡትን እንግዶች መቀበልና ማስተናገድ ብሎም ማለናበት እንደ አዲስ የህይወት ልምድ ነበር ። በአንድ ቦታ ተቀምጦ የባጡን የቆጡን፣ ያለውንና የሚመጣውን መወያየት ከተለየው ዓመታት አለፉ ።

መስፍን በ16 ዓመቱ የፈረንሳይ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪ እያለ አባቱ ቀኝአዝማች ደርብ ወደ ፈረንሳይ ሄዶ ትምህርቱን እንዲቀጥል ወሰኑ ። በፈረንሳይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ ታላቅ ወንድሙ ሙሉጌታ ደርብ ወደ አሜሪካ ጋበዘው። መስፍን የአሜሪካ ኑሮ በጣም ስለአጓጓው ትምህርቱን አሜሪካ እንዲጨርስ ከወንድሙ ከሙሉጌታ ጋር ተስማሙ ።

በኢትዮጵያ የመንግስት ለውጥ ተካሄደ ። ቀኝአዝማች ደርብ ለውጡን ባለመቀበል ኮብልለው ወደ ጫካ ገቡ ። መስፍን የአባቱን ሁኔታ ሲሰማ የመመለሱን ጉዳይ አዘገየው ። የሀገር ቤት ሁኔታ እስከሚረጋጋ አሜሪካ ለመኖር ወሰነ ። ወደ ሀገሩ ሳይመለስ ሃያ ሰባት ዓመታት ቆየ ። በእናቱ በወ/ሮ እጅጋየሁ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ምክንያት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ነበር ። ሆኖም ወደ ሀገር ከገባ በኋላ አንዳንድ ነገር ሌላው ሲጎትተው ለጥቂት ወራት ለመቆየት ወሰነ ። ከሁሉም በላይ ያብከነከነው የአባቱ ጉዳይ ነበር ።

ከለውጡ በኋላ ጫካ እንደገቡ ይነገር እንጂ መሞት መኖራቸው ሳይታወቅ በእንጥልጥል መቅረቱ ዕንቅልፍ የነሳው ትልቅ በሽታ ነበር ። ነገር አዋቂዎች ቢጠይቅ ፣ ጓደኞቻቸውን ቢያወያይ የተጨበጠ መልስ አላገኘም ። በቤተሰቡ ላይ የደረሰውን መበታተንና መንሳቀል አሜሪካን ሆኖ የሰማውና በተቻለው ሁሉ ድጋፍ ለመስጠት ጥረት ያደረገ በመሆኑ በመጠኑ የህሊና ሠላም ለማግኘት ችሏል ። ወንድሞቹና እህቶቹ ከአካባቢው ጋር ተመሳስለውና ተጋብተው ድሮ ከነበራቸው የከበርቴ ኑሮና አስተሳሰብ ርቀው ነበር ያገኛቸው ። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሀገሩ እንደገባ የሚያየው ሁሉ የፈራረሰና ያረጀ፣ ሰው ሁሉ እስረኛ ነበር የመሰለው ።

መስፍን ልጅቷን ከዚህ ቀደም ያየበትን ቦታ መልሶ መላልሶ ለማስታወስ ሞከረ ። በሀሳቡ « አበራ አስተዋወቀን ልበል ? በቀደም የቀብሩ ዕለት ማሳረጊያው ላይ ነበረች እሷ አይደለችም ። ያቺ ምስጢረ የምትባል የአበራ ጓደኛ ነች ። ግን አይመሳሰሉም ? ኖ . . ኖ . . ይህችኛዋ ዘለግና ረጋ ያለች ቆንጆ ነች ። ምስጢረ ግን ተጫዋች ነች ። ምናልባት እህትማማቾች እንዳይሆኑ . . . » በማለት በሀሳቡ ሲያወጣና ሲያወርድ ቆየ ። ወጣቷ በዝርግ ሰሀን ቆሎ ይዛ ከጓዳ በር ብቅ አለች ። አዲስ ወደገቡት እንግዶች አመራች ። መስፍን ሀሳቡን አላቋረጠም ።

« እግር አጣጣሏ እንኳ ያስታውቃል ፣ ዝግ ያለች ነች። አመለካከቷ ዓይን አፋርነቷ የጨዋ መልክ ስጥቷታል ፣ ይቺን ያፈቀረ ፣ የወደደ መቼም የታደለ ነው ። ኖ . . ኖ . . አይደለም ማፍቀር እንጂ መውደድ አንድ ወጥ ከሆነ አደገኛ ነው . . . » ሊተዋወቃት ወሰነ ። ያለበት የሀዘን ሁኔታ ይፍቀድ አይፍቀድ ግን ተጠራጠረ ።

ሀዘንተኛው በተቀመጠበት ትልቁ ሳሎን አዛውንት እናቶች ፣ ቀሳውስት ፣ ወንደላጤውና ሌተላጤው በየፊናቸው ተከፋፍለው የግል ጭውውታቸውን በደራ ሁኔታ ተያይዘውታል ። አስተናጋጆቹ ከቆሎ፣ ዳቦ ፣ ንፍሮ አንስቶ እስከ ቡና ፣ ቢራና ለስላሳ አቀረቡ ።

የአንዱ ወገን ስብስብ ቀልድ መሳይ ጣል በማድረግ ቤተሰቡ መለስ ብለው መኖር ፣ ማዘን ፣ መደሰት ፣ መተከዝ በሰው ሀይወት ውስጥ ያሉ የተፈጥሮ ህግጋት መሆናቸውን እንዲያጤኑ ፣ እንዲሁም ከሀዘናቸው እንዲፅናኑ ረዳቸው ። ቄሱ የማፅናኛ ቡራኬና የነብስ ይማር ፀሎት ሲያደርጉ ፣ አዛውንቱ ታሪክን ከሟች ጋር በማያያዝ ያሳለፉትን ሀይወት በማወዳደር አነሱ ። ሌላው ተሳታፊ በቀልዱና በቴያትራዊ ድርጊት በመሳተፍ ቤተሰቡን አዝናኑ ።

ከጓዳ በር አንድ መልከ መልካም መሀከለኛ ዕድሜ ላይ ያሉ ወ/ሮ በዝርግ ሰሀን ያልተከፈተ ቢራና ለስላሳ ይዘው ወጣ አሉ ። እርሳቸው በሚያልፉበት በኩል የተቀመጡት አዛውንት ፣ ሽማግሌ ፣

እናቶች፣ አባቶች ሁሉም በአንድነት በሳቅ ፈነዱ ። ሁሉም ትኩረቱን ወደ አሳሳፊዋ ወይዘሮ አደረገ ። የኋላቸውን ለማየት ዕድሉን ያገኙ ሁሉ በሳቅ ፈነደቁ ። ወይዘሮዋ በተፈጠረው ነገር በመደናገጥ ዓይናቸውን ወደ ራሳቸውና ወደሚስቀው ሰው መለስ መለስ በማድረግ « ምን የሚያስቅ ነገር ተገኘ ? » በማለት ጠየቁ ። እንደሳቸው ግራ የተጋባው መስፍን ብቻ ነበር ። ከመቀመጫው አፈፍ ብሎ ተነስቶ ከኋላቸው በመርፌ ቁልፍ ነጠላቸው ላይ የተያያዘውን ጅራት መሳይ የአሻንጉሊት ቁራጭ ለማንሳት ሞከረ ። ግራ የተጋቡት ወይዘሮ « ምን ልታደርግ ነው ? » በማለት ቀሚሳቸውን ወደ ራሳቸው ሰበሰቡ ።

« እላይዎ ላይ አንድ ነገር አለ ። እርሱን ለማንሳት ነው » አላቸው መስፍን ። ወይዘሮዋ መስፍንን እየገላመጡ የሳቁን ግርግር አቋርጠው እየተመናጩ ወደ መጡበት ጓዳ ተመለሱ ። መስፍን በቆመበት

« ምን አደረግኩ ? ቆሻሻን ከሰው ላይ ማንሳት ያስነውራል እንዴ ? » በማለት ራሱን ጠየቀ ። ሳያስበው ግራ እንደተጋባ ወደውጪ ወጣ ። ወጣቷ ሁኔታውን ትከታተል ስለነበር ተከተለችው። ወንድሙ አበራም ሠለሰ ።

« መስፍን ምነው ምን ሆንክ ? » ሲል አበራ በመካከላቸው የቆመችውን ሴት እያየ ጠየቀ ።

« ምንም ! ምን የሆንኩ ይመስልሃል ? » አለ መስፍን ።

« በሰው ሳቅ ተቀይመው ነው ? » አለች ። አንቱታዋ ለመስፍን በአክብሮትም ሆነ ፣ በሌላ መልኩ አላስደሰተውም ።

« መስፍን ባህላችንን ታውቀው የለ » አለ አበራ ።

« ተወው አውቃለሁ ። ጥፋቱ የእኔ ነው ። በማላውቀው ነገር ዘው ብዬ መግባቴ ፣ ምን ታደርገዋለህ ለገዛ ባህልህ እንግዳ



ስትሆን ፣ መቼ ይሆን ይህን ባህል ተምሬ የምጨርሰው ? » አለ መስፍን በድርጊቱ በመፀፀት መልክ እራሱን እየነቀነቀ ።

« በነገራችን ላይ ከመስፍን ጋር አልተዋወቃችሁም ? ይቅርታ በቅርብ ከአሜሪካ የመጣው ታላቅ ወንድሜ መስፍን ማለት እሱ ነው . . . ሕሊና ከታወቁት የትምህርት ቤቱ መምህርት አንዷ ናት ተዋወቁ » አለ ።

« በዝና ሰምቻለሁ ። አበራ ስለእርስዎ ብዙ ያወራል » ብላ እጇን ዘረጋች እንደ መጨበጥ ዓይነት ።

« ኧረ አንተ በይ ። እርስዎታው ከበደኝ ። አበራ ስለ እኔ ብዙ ያወራል ። በመጥፎ ነው ወይስ በጥሩ ? » ሲል ጠየቀ በማፌዝ መልክ ።

« ስለአንተ ምን መጥፎ ነገር ይወራል ? የምትኖረው አሜሪካ ፣ የምትሄደው በመኪና ፣ የምትበላው ወደል ሀምበርገር ፣ አንድ መስመር የያዘ ህይወት ፣ ግርግር የሌለብህ ፤ » አለ አበራ ከሕሊና መልስ ቀድሞ ።

« እርሱን ተወው ! . . . » አለና የአበራን ዲስኩር ትቶ ወደ ሕሊና ፊቱን መለሰና « ታዲያ መምህርት ማስተማር እንዴት ይዞሻል ? » አላት ።

« ማስተማር ቀላል ነው ። የተሰበሰቡ ተማሪዎችን በተወሰነ የትምህርት መስክ በተሰጠው መፅሀፍ መሠረት መምራት ምን ያቅታል ? ከማስተማሩ ይልቅ መማሩ ነው ከባድ » አለች አንድ ጊዜ መስፍንን ሌላ ጊዜ አበራን አፈራርቃ እያየች ።

« መምህርት መማር የሰለቸሽ ትመስያለሽ ? እንዴት ታድለሻል ? . . . አለ መስፍን ። « በህይወቴ እንደመማር የምወደው ነገር ያለ አይመስለኝም ። ሆናም ፍላጐቴን ለማሟላት በቂ ሀብት የለኝም እንጂ አለመማር ምንጊዜም ምርጫዬ አልነበረም ፣ አይሆንምም ። » ስትል ሕሊና ነገሩን በጥሞና ለማስረዳት ሞከረች ።

መስፍን የስኩሰውን ሲጋራ አልጨረሰም ። አንድ ኮረዳ ከቤት ውስጥ በበር ወጣ ብላ « ጋሼ አበራ እራት ሊቀርብ ነው » በማለት ተጣራች። ሳሎን እንደገቡ ሕሊናና አበራ በሩ አጠገብ ሲቆሙ መስፍን መሀል ለመሀል አቋርጦ ወደ መቀመጫው አመራ ።

« የሞቱትን ነፍስ ይማርልን ። አቡነ ዘበሠማያት እንበል ።» ብለው ጋቢያቸውን አጣፍተው መስቀላቸውን ደግነው የቆሙት ባለ ነጭ ትልቅ ጥምጣም አዛውንት ቄስ ዓይናቸውን መስፍን ላይ አሳርፈው ነበር ። ቃለቡራኬው እንዳለቀ ሕሊና ወደ ጓዳ ገባች ። አበራ ወደ ቀድሞ መቀመጫው ተመልሶ እራት መብላት ጀመረ ።

« ብዙ ማውራት አልቻልኩም እንጂ መምህርት በጣም ኢንተረስቲንግ ልጅ ሳትሆን አትቀርም » አለው አበራን መኝታቸውን እያዘጋጁ ።

« ሕሊና በጣም ጥሩ ሰው ነች ። የልጅ አዋቂ ነች ። ያወቃት ሁሉ ይወዳታል ። » በማለት አበራ ስለ ሕሊና ያለውን አድናቆት ገለጹለት ።

« ልጅ ማለት ፣ ዕድሜዋ ምን ያህል ቢሆን ነው ? » ሲል መስፍን አበራን ጠየቀው ።

« ዕድሜ ምን ያደርጋል ? አንደበቷና አስተሳሰቧ የሊቅ ያህል ነው ። ከዕድሜዋ በላይ የምታስብ ልጅ ናት » አበራ አድናቆቱን በመቀጠል ተናገረ ።

« እኮ ዕድሜዋ ስንት ይሆን ? »

« ምነው ዕድሜዋን አጥብቀህ ጠየቅከኝ ? ምን አስበሃል ? »

« ምን አስባለሁ ? እንዲሁ ለማወቅ ያህል ነው ። አንተ ምነው . . . በመሀከላችሁ ነገር አለ እንዴ ? »

ሕሊና ወደ ቤት ስትሄድ ስለመስፍን ማሰቧን ማቆም አልቻለችም ። ከስሜቷ ጋር በሀሳብ እየተከራከረች መኖሪያ ሰፈሯ ደረሰች ። የቀኑ ድካም የተጫጫናት ሕሊና አጠገቧ ባለው ሶፋ



ወንበር ላይ በረጅሙ ተንፍሳ ተቀመጠች ። ጣሪያ ጣሪያውን እያየች በሀሳብ ማዕበል ተዋጠች ።

« ትልቅ ሰው ነው አንቱታዬን ለምን ጠላው ? ዝምተኛ ይመስላል ። የአበራ ታላቅ ወንድም ? አበራ ነው ታላቅ የሚመስለው። አበራ መልኩ ተጉሳቁሏል ። ሽበትም ወጋ ወጋ አድርጎታል ። መቼም ድሎት ህይወት ነው ። ገምች ቢሉኝ ከ35 ዓመት ያነሰ እንጂ የበለጠ አላደርገውም ። የተማረ መሆን አለበት ። እንግሊዘኛው . . . ግን በእንግሊዘኛ የተናገረ ሁሉ የተማረ ነው ማለት ነው ? » ሕሊና ለጥያቄዋ ሁሉ መልስ ማግኘት አልፈለገችም። በሀሳቧ ብዙ ለመጓዱት አልቻለችም ። በአለችበት ዕንቅልፍ ይዟት ሄደ ።

* * *

አልጋዋ ላይ አረፍ ብላ ነበር ደብዳቤውን ማንበብ የጀመረችው። ባልጠበቀችው ሁኔታ የልብ ትርታዋ እየጨመረና እጇ እየተርበተበተ ነበር ደብዳቤውን የከፈተችው ።

*« ሃይ ሕሊና እንደምን ሰንበተሻል ። መቼም ይህ ደብዳቤ ሲደርስሽ ሳትገረሚ አትቀሪም ። በቅድሚያ የቤተሰባችን የሀዘን ተካፋይ በመሆንሽና ስለአደረግሽው ከፍተኛ የጉልበትና የኢሞሽናል ድጋፍ በጣሙን አመሰግናለሁ ። እግዚአብሄር ይስጥልኝ ። ሕሊና ታናሽ ወንድሜን አበራን በጣም እወደዋለሁ ። እንዲህ ያለች ውብና አስተዋይ ጓደኛ በማግኘቱ በጣም ደስ ብሎኛል ። በሁለት ቀን ግንኙነት ወቅት የተጫወትናቸው ቁም ነገሮች ሁሉ እስከአሁን ትዝ ይሉኛል ። ከአንቺ ጋር ለመቀራረብ ሁኔታዎች*

« በይ በዚህ ይለፍ . . . ዘለዓለም በዚህ ነገር መቼም እንደተጨቃጨቅን ልንኖር ነው ። » አለች ከበቡሽ ጉዳዩን ላለማንሳት በመወሰን መልክ ። ለጥቂት ደቂቃ አብረው በዝምታ ተጓዙ ።

ከበቡሽ ፊቷን ወደ ሕሊና መለስ አድርጋ « ከነከነኝ እባክሽን፣ ያልሽውን በይ እንጂ ዛሬ ሳልጠይቅሽ ብተው ለሊት ዕንቅልፍ አይወስደኝም ። ከዛ በፊት ግን ለምጠይቅሽ ጥያቄ ምላሽ እንደምትሰጪኝ ቃል ግቢልኝ » አለች ከበቡሽ ።

« ጠይቂኝ እመልስልሻለሁ ። ቃል ግን አልገባም ። ድንገት የማላውቀውን ጥያቄ ብትጠይቂኝና ሳላውቅም ብልሽስ ? » አለች ሕሊና ሀፍረት በተሞላበት ፈገግታ ።

« ምንም ሳትደብቂኝ እስቲ ንገሪኝ በምኑ ወደድሽው ? መልኩ፣ ገንዘቡ ፣ ፀባዩ ወይንስ ለጨዋታ ያህል . . . ከወደድሽው ደግሞ ለምን አታገቢውም ? እስከመቼ ምስጢራዊ ግንኙነት አድርገሽ ትኖሪያለሽ ? » ከበቡሽ የጠየቀቻት ፍጥነት በተሞላበት አባባል ነበር።

« ለመሆኑ መውደዴን እንዴት ገመትሽ ? ለማንኛውም ለጥያቄዎችሽ ለጊዜው አጥጋቢ መልስ የለኝም ። ሆኖም ስለእኔ በመቆርቆርሽ በጣም አመሰግናለሁ » አለች ሕሊና በመልሷ ከከበቡሽ ይልቅ ራሷ በመገረም ።

« ሕሊና ይቅርታ ስለምወድሽና እንደራሴ ስለማይሽ ነው ይህን ያልኩት ። አትቀየሚኝ ። ሁለተኛ ስለዚህ ጉዳይ አላነሳብሽም » አለች በጥያቄዋና በአባባሏ የሕሊናን ስሜት የጎዳች መሰላት ። አበራ ጣደፍ ጣደፍ ብሎ ወደ ክፍሉ በመግባት ላይ ላለ ሕሊና በሥሙ ጠራችው ።

« ቆየኝ ፣ ቆየኝ ፣ ዛሬ ማታ ምን ትሰራለህ ? ለብርቱ ጉዳይ እፈልግሃለሁ » ይመችሃል ? አለችው ።

« አፍኮርስ ሕሊና ምነው በደህና ? » በማለት ግራ በመጋባት መለሰላት ።



« ደህና ነኝ ። ለብርቱ ጉዳይ ማለት የማማክርህ ነገር ስላለኝ ነው » በማለት ስሜቷን ከአበራ ለመደበቅ ወደ መሬት አተኮረች ። ሁለቱም አብረው አልቆዩም ። ፍጹማዊ የመተማመን ገፅታቸውን ተለዋውጠው ወደየክፍላቸው አመሩ ።

ሕሊና በውስጧ ተከድኖ የበሰለውን የሀሰንን ግንኙነት ትርጉም ለመስጠት ካልተመሰሱ ጥያቄዎች ጋር ስትታገል ከቆየች ሰነበተች ። ብቻዋን ያለአማካሪ እነኚህን እንቆቅልሾች መፍታትና ጥያቄዎችን መመለስ አቃታት ። ሆኖም ጥረት ከማድረግ አልተቆጠበችም ። ሀሳቧ ሁሉ ዞሮ ተዳምሮ ወደዚሁ ስለሚያመራ ከውጭው ዓለም ጋር ያላት ግንኙነት ሁሉ የተቆጠበ ሆነ ። የሥራ ጓደኞቿና በቅርብ የሚያውቋት ሁሉ « ምነው ? ምን ሆነሻል ? ሀሳብሽ ርቆ የሄደ ይመስላል ። የሚወራልሽን አትሰሚም ፣ ማዳመጥ ትተሻል ። ግድ አይሰጥሽም ። » በማለት ግንኙነታቸውን እያሳሱ መጡ ።

ሕሊና ጉዳቷን በቀላሉ ለሌላ ሰው የማታወያይና ዕርዳታ መጠየቅ አግባብነት የሌለው ተግባር ነው ብላ የምታምን ሰው ነች ። « ራስን መቻል በሁሉም አቅጣጫ » የሚለውን የአባቷን ምክር የዕለት ተዕለት ተግባሯ ሆነ ። ግን ይሄ ለብቻው ነው ። እራሴን እሳልፌ ለጥቼ መመለሻ ጠፋ . . . ምኑን ነው የወደድኩት ? ደግሞስ እሱ ስለወደፊቱ ቀርቶ ስለነገም ማውራት አይፈልግም ። እኔስ ራሴ ብሆን ስለወደፊት ታይቶኝ ወይም አስቤበት እውቃለሁ ? . . . የቀን ተቀን ኑሮ ብቻ ነው በሀሳቤ የሚመጣው ። እንዴት ሆኖ ነበር እኔና ሀሰን እዚህ ደረጃ ላይ የደረስነው ? . . . ከበቡሽ እውነቷን ነው ። አሁን ሀሰን ላግባሽ ቢለኝ ? . . . ሕሊና ሀሳቧን አልጨረሰችም ፣ ተማሪዎቿ የሰጠቻቸውን የክፍል ሥራ ጨርሰው ወደ ጠረጴዛዋ መቅረብ ጀመሩ ።

« ምን ልበለው ? ይቅርታ አድርጌአለሁ ፣ አላደረግሁም አላልኩም ። በትምህርት ቤቱ ስልክ ስለደወለ ብዙም ለመናገር አልቻልኩም ። አጠገቤ ሰዎች በመኖራቸው እሺ እሺ ብዬ ስልኩን ዘጋሁት ። ግን እርሱ በሚቀጥለው የሳምንት ማለቂያ እመጣለሁ ያኔ እንነጋገርበታለን ብሏል ። እውነት ከሆነ » አለችና ዕንባ ባልተለየው ዓይኖቿ ወደ አበራ ተመለከተች ። አበራ የሕሊና ጉዳይ ምንም ያህል ቢያብከነክነውም ቅሉ በሀሳቡ ሁለት የተለያዩ ቅራኔዎች ነበሩ ።

« በጣም ትወደዋለች ፣ በጣም ትጠላዋለች » ቅራኔዎችን ማረጋገጥ አልሞከረም ። የማብራሪያ ጥያቄዎችን በመወርወር ጣልቃ ሳይገባ ሕሊናን አዳመጠ ።

« ታዲያ ሲመጣ ዕቅድሽ ምንድነው ? » በማለት ሕሊናን ጠየቀ ።

« እኔ እንጃ ፣ ግራ ገብቶኛል ። በእውነት ሀሰን ችግሩ ምን እንደሆነ ለመረዳት እፈልጋለሁ ። በሌላ በኩል ደግሞ እርሱ የሚለውን ብቻ ከማዳመጥ እኔም ራሴ ማድረግ የምችለውን ማወቅ አለብኝ ብዬ ገመትኩ ። . . . . እሱ ግድ የለውም ብዬ እንዳልደመድም ይሄው ውሎ አላደረም ስልክ በአስቸኳይ ደወለ ። ይሁን ብቻ በእርግጥ ጭንቀት አለበት ። ጭንቀቱ ግን ለክፉ ይሁን ለደግ ለይቼ ለማወቅ አልቻልኩም ። የእርሱ ጭንቀት ነው ወደ እኔ ተጋብቶ ግንኙነታችንን ሁሉ ጥርጣሬ ላይ የጣለው » ብላ ከመጨረሷ አበራ ፂሙን አሸት አሸት አድርጐ አቋረጣት ።

« አንቺ ትጠረጥሪዋለሽ ወይንስ እርሱ ይጠረጥርሻል ? » ሲል ጠየቃት ። ሕሊና መልስ ለመስጠት አልቻለችም ።

« የእርሱን አላውቅም . . . እኔ ግን ግንኙነታችን ትክክል ነው አይደለም ብዬ እጠራጠራለሁ ። ሌላው ግንኙነታችን የእኔ ፍላጎት ብቻ ይመስለኛል ። ሀሰን ግን እኔን ላለማስቀየም ብሎ ቀጠለበት» በማለት አንገቷን ገደድ አድርጋ ወደ አበራ ተመለከተች።



« እውነትም ውስብስብ » አለ አበራ በረጅሙ ተንፍሶ በመንጠራራት ዓይነት ።

« ለመሆኑ ልትቀርቢው የምትችይ ጓደኛ የለውም ? » ሲል አበራ ጠየቃት ።

« ያሬድ ነው ፣ እኔ የማውቀው የቅርብ ጓደኛው ። ከያሬድ ሌላ ማንንም አላውቅም ።ባውቃቸውስ ምን ብዬ ልነግራቸው ነው? » አለች ሕሊና ለራሷ በመናገር ዓይነት ።

ሕሊና እኔም ግራ ገባኝ ። በነገርሽኝ ላይ ተመርኩዤ ምክሬን ብለግስሽ እንዳላሳስትሽ ፈራሁ ። የሰማሁት አንቺን ብቻ ነው ። ከሀሰን ጋር እምብዛም ተነጋግረን አናውቅም ። ለማውራትና በቅርቡ ለመተዋወቅ እንኳን አልበቃንም ። ታዲያ በዚህ ላይ ምክር መስጠት ማለት ነገርን ሳይበስል በአጭሩ መቅጨት እንዳይሆን ሰጋሁ ። » አለና ስሜቷን ለማንበብ ወደ ሕሊና ዓይኖች አተኮረ ።

« እሮይ ! » በማለት ሕሊና በረጅሙ ተነፈሰች ።

« ለአንተ በመናገሬ ትንሽ ቀለል አለኝ ። አበራ ምን ያህል እንዳስጨነቀኝ አታውቅም ። የማይርቁት ወዳጅ ሆነብኝ ። ራሴ ተቸግሬ አንተንም አስቸገርኩ ። ከአንተ አልፎ ከበቡሽ እንኳን ተጨንቃ ልትሞት ነው ። » ከማለቷ አበራ ዘና ብሎ « ለከበቡሽ ነገርሻት እንዴ ? » ሲል ጠየቃት ።

« እንዴት እንደሆነ አላውቅም ከበቡሽ ስሜቱን በሙሉ ታውቃለች ። ሀሳቤን እንዴት እንደምታነብ ግን ማግኘት አቃተኝ ። አንዳንዴ መስማት የማልፈልገውን እንዳትነግረኝ እፈራለሁ ። »

* * *

ሕሊና በትምህርት ቤቱ በኩል የተላከላት ደብዳቤ ከማን እንደሆነ ለማወቅ ጓጓች ። ቀደም ሲል ደብዳቤ የሚደርሳት በፖስታ ቤት በኩል በተከራየችው ሳጥን ነበር ። በትምህርት ቤቱ በኩል ፖስታ መለዋወጥ ያቆመችው ቀደም ሲል የሚላኩላት ደብዳቤዎች ያለ አድራሻ እየተሰወሩ በመቸገሯ ነው ። ሥሟ በተለጠፈው ዝርዝር ውስጥ መኖሩን የነገረቻት ከበቡሽ ነበረች ።

ከበቡሽ ትቀልዳለች ። . . . ይኼ ደግሞ ሌላ የመመርመሪያ ዘዴዋ ነው ብላ በማሰብ የከበቡሽን ንግግር አልተቀበለችውም ነበር ።

« እውነቴን እኮ ነው የምነግርሽ ! ሂጂና ተመልከቺ ። » አለች ከበቡሽ ኮስተር ብላ ። ሕሊና እየሳቀች ቀና ብላ ከበቡሽን አየቻት ። ፊቷ ላይ የቀልድ ምልክት እንዳለ ለማወቅ በትኩረት አጤነቻት ። የዛሬው አቀራረቧ ከሌላው ቀን ለየት አለባት ።

ሕሊና ደብዳቤውን እስከምታገኝ አላመነችም ነበር ። ደብዳቤውን ለማግኘት የጠዋቱን አጋማሽ የዕረፍት ጊዜ መጠበቅ ነበረባት ። አማራጭ አላገኘችም ። ወደ ክፍሏ ገባች ። ፖስታ አዳይ ወደሆኑት የትምህርት ቤቱ ፀሃፊ ቢሮ ስትቀርብ እርሷ የመጀመሪያ ሰው ነበረች ። ፖስታውን እንዳገኘች ወዲያውኑ አድራሻውን ለማየት ሞከረች ። ፍጹም ያልጠበቀችው ደብዳቤ ! ተገረመች ። ፖስታው የተላከው ከአሜሪካ ነበር ። ፀሀፊውም መስፍን ነው ። ሕሊና ቀደም ሲል ለፃፈው መልስ አልመለሰችም ። በአጠቃላይ ሁኔታው ግራ በመጋባት በዝምታ ለማለፍ ወሰነች ። ይህ ሁለተኛ ደብዳቤ ሲደርሳት መስፍን ጠበቅ ያለ ግንኙነት መፈለጉን ገመተች ። ባለችበት ቆማ ግራ በመጋባት ደብዳቤውን ከፍታ ማንበብ ጀመረች ።



« ሠላም ሕሊና እንደምን ሠንብተሻል ። ስለጤንነትሽ አበራ ሁልጊዜ ከሚፅፍልኝ ደብዳቤ መረዳት ችያለሁ ። እስከ አሁን አበራ ከሚሰጥሽ መልዕክቶች የእኔን ደህንነት እንደተረዳሽ እርግጠኛ ነኝ ። የፖስታ ሣጥን ቁጥርሽን ባለማግኘቴ በትምህርት ቤት በኩል ልፅፍልሽ ወሰንኩ ። « ሕሊና አለላ የመጣሁ ጊዜ ብዙ ነገሮች ሳይገቡኝ ላይ ላዩን ጋልቤ ነው የተመለስኩት ። በችኮላ ብዙ ስመሥራት ጣርኩኝ። አሁን ከአበራ ጋር ስንፃፃፍ ነው ስለ እንቺና አበራ ግንኙነት በከፊል ለመረዳት የበቃሁት ። »

« ሕሊና ! ምነው ሙጥኝ አለብኝ አትበይኝና የፃፍኩልሽ መፃፍ ስለፈለግኩና በማላውቀው መንገድ አንዳች ግፊት ስለሚገፋፋኝ ነው ። ይህ ግፊት ምንድነው ብትይኝ ልነግርሽ አልችልም ። ሕሊና አዚህ ኑሮዬ ጥሩ ነው ። እሰራለሁ ፣ እኖራለሁ ፣ አልፎ አልፎም እማራለሁ ። ሕሊና እባክሽን ፃፊልኝ። በመፃፍሽ ደብደቤዬን ለመቀበል ፈቃደኛ እንደሆንሽ ለመረዳት እችላለሁ ። በተረፈ ለውለታሽ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ በአበራ በኩል ትንሽ ስጦታ ልኬልሻለሁ ። እንግዲህ ደብዳቤሽን በጉጉት እጠብቃለሁ ።

አድራሻዬም፣ **Mesfin Derib**

**6540 N. Willson St.**

**Chicago, IL .70313**

**U.S.A**

ያንቺው ናፋቂ መስፍን ደርብ ።

ሕሲና ፊቷ በፈገግታ ተሞላ ። በሀሳቧ « ከዚህ በኋላስ . . . የሚቀጥለው » ስትል አሰበች ። ጊዜም አላጠፋች ። ወዲያውኑ ወደ አበራ ክፍል ሄደች ። ቤቷ ቀጠረችው ።

አበራ እንደወትሮው ሠላምታውን አጋኖ « እዚህ ቤቶች » በማለት ወደ ሕሊና ቤት ገባ ። ሕሊና ተቀምጣ ከተማሪዎቿ የሰበሰበችውን ወረቀት በማረም ላይ ነበረች ። « ሃይ አቤ ግባ » በማለት ከመቀመጫዋ ተነሥታ ተቀበለችው ። ሻይ ቡና በመጠየቅ ለማስተናገድ ሞከረች ። ሆኖም አበራ ግብዣዋን አልተቀበለም ።

« ከበቡሽ ትጠብቀኛለች ፤ ቶሎ እንድትመለስ ስላለችኝ ሌላ ጦርነት ከመከፈቱ በፊት » በማለት ወደ ሕሊና ተመለከተ ።

« አበራ ዛሬ ከመስፍን ደብዳቤ ደረሰኝ ። » ፊት ለፊት ተከማችተው ከሚገኙት ወረቀቶች መሀከል ገልበጥ ገልበጥ አድርጋ ፖስታውን ለአበራ ሰጠችው ። አበራ ደብዳቤውን ሲያነብ በትኩረት ተመለከተች ። በሚያነብበት ሰዓት ከፊቱ ላይ ስሜቱን ለማንበብ ሞከረች ። አንብቦ እንደጨረሰ ደብዳቤውን በማቀበል መልክ እጁን ወደ ሕሊና ዘረጋ ።

« አዎ መስፍን በደብዳቤዎቹ ላይ ስለአንቺ አንስቶ የማያውቅበት ጊዜ የለም » አለ የመስፍንን የደብዳቤ ሃሳብ በማረጋገጥ ። « ምን እንደነካው አላውቅም ። አንቺን ካየ ጀምሮ ወሬው ሁሉ ሕሊና ሕሊና ነው ። በጣም ያሳዝናል ። ቀደም ብዬ ፅፌለት ነበር ። ስለአንቺ ለማስረዳት ሞከርኩ ። ግን የሰማኝ አልመሰለኝም ። ሕሊና ለዚህ አሳፋሪ ድርጊት በጣም ይቅርታ አድርጊልኝ ። እኔ ነኝ በገዛ እጄ አስተዋወቂ እዚህ ውስጥ የከተትኩሽ ። » አለ አበራ ወደ መሬት አቀርቅሮ በወንድሙ ድርጊት እየተፀፀተ ።

« ምን ማለትህ ነው አበራ? የወንድምህ ድርጊት እኮ ትክክለኛ ነው ። ልታፍርበት ወይንም ልትፀፀትበት የሚገባ ነይደለም ። ተዋወቅኝ ፤ የበለጠ ለመተዋወቅ ደግሞ ፈለገ ። በግድ ይሁን ሁኚ ብሎ አላስገደደኝም ። » አለች ሕሊና ወደ አበራ በቀዘቀዘ ስሜት እየተመለከተች ።

« እውነትሽን ነው ? » አበራ የሰማውን ባለማመን ዓይኖቹን ፈጠጥ አድርጎ በድንጋጤ « እኔ ምን ትለኛለች ብዬ ያለውን ሁሉ ደብቄ ነበር ። በአንቺና በሀሰን መሀከል ያለውን ግንኙነት የሚያደፈርስ መስሎኝ ነው እስከሁን መስፍን ያለውን መግለፅ ያልቻልኩት ። ሌላው . . . » የተናገረውን አልጨረሰም ።

ሕሊና ማለት የፈለገውን እንዲጨርስ « ምን አሳፈረህ ? እኔ እኮ ልጅ አይደለሁም። ይልቅስ ንገረኝና ልስማው » በማለት ገፋፋችው ።

« ሕሊና መስፍንን አታውቂውም ። አንቺ በጣም ጥሩ ሰው ነሽ ። በማይሆን ነገር እንዳያስቀይምሽ ለአንቺ በማሰብ ነው የፃፈውን ያላሳየሁሽ » በማለት ኮስተር ብሎ ነገራት ።

« ወንድምህ ለእኔ መጥፎ እንደማይመኝ አውቃለሁ ። ደግሞስ ደብዳቤ መፃፃፍ ምንም ማለት አይደለም ። መስፍን ከፃፋቸው ሁለት ደብዳቤዎች እንደተረዳሁት በሁለታችን መሀከል የምንፈጥረው ግንኙነት በመፃፃፍ ላይ የተመሠረተ ጓደኝነት ነው ። አንተ የምታውቀው ሌላ ነገር ካለ ንገረኝ » አለች ሕሊና ።

አበራ ጥቂት አመንትቶ « የመስፍን ጥያቄ ከዚያ በላይ ሳይሆን ይቀራል ብለሽ ነው ? » ጥያቄዋን በጥያቄ መለሰላት ።

« አበራ ! አበራ ! » አለች ሕሊና እራሷን በአሉታ እየነቀነቀች ። « ምንድነው ምስጢሩ ? ለምንድነው ወንድምህን የማታምነው ? ለእኔ ለመንገር ያልፈለግከው ነገር አለ ። በእውነት ጓደኛሞች ከሆንን ለምን ደፍረህ አትነግረኝም ? » አለች በቁጥታ ወደ አበራ እተኩራ ።

እምነቷ ነው ፡፡ ከሥራ እንደገባች « እማማ በላይነሽ የዛሬው ደግሞ ለብቻ ነው ፡፡ ቤቱ ሁሉ እንዴት ደስ ደስ ይላል ? » አለች የሚማርከውን የዕጣን ሽታ በአፍንጫዋ እየሳበች ፡፡

« ታዲያ ጎረቤቶቹ ተጠሩ ? » ብላ ጠየቀች ፡፡

« የመባቻን ቡና ከሰው ጋር አይካፈሉም ፡፡ የቤተሰብ ቡና ነው » አሏት ፡፡ ሕሊና የያዘችውን አስቀምጣ ፣ የሥራ ልብሷን ቀይራ ፣ ዱካዋን አቅርባ ፣ ወ/ሮ በላይነሽ ፊት ለፊት ተቀመጠች ፡፡ ቡናው የሆነ ነገር እንዳለበት ከወ/ሮ በላይነሽ ሁኔታ ተረዳች ፡፡

« እንግዲህ ልጄ ዕድሜዬ እየገፋ ጉልበቴ እየሸሸ ነው ፡፡ ምኞቴ የአንቺን ሠርግ ደግሼ ልጅሽን አቅፌ ለማየት ነበረ ፡፡ ሆኖም አንቺ ትዳር ያሰብሽ አትመስይም » አሉ ሕሊናን በትኩረት እያዩ ፡፡

« ለመሆኑ ከሀሰን ጋር እንዴት ናችሁ ? » ብለው ጠየቋት፡፡

« አይ እማማ በላይነሽ ! » አለች ፈገግ ብላ መሬት መሬት እያየች ፡፡ « ባሉ መች ተገኘ ብለው ነው ? የሀሰንን ነገር ተውት ፡፡ ተወርቶ አያልቅም ፡፡ » አለች ሁለት እጆቿን አጣምራ በመንጠራራት ዓይነት ፡፡

« ልጄ ከአንቺ እስኪመጣ ነበር የጠበኩት ፡፡ ያለ አቻ ጋብቻ» አሉ ዝግ ብለው ለራሳቸው በመናገር ፡፡ የእርሱ ሃይማኖት እኮ ከሁለት ሚስት በላይ ማግባት ይፈቅድለታል ፡፡ ለጥቂት ጊዜ አሰብ አድርገው « አባትሽ ጥሩ ክርስቲያን ነበር ፡፡ የእግዚአብሔርን ሥም ከአፉ ነጥሎ አያውቅም » አሉ ዓይናቸውን ከሕሊና ላይ አንስተው ወደመሬት በመመልከት በትዝታ ወደኋላ ተጉዘው « ሀሰን ለመሆኑ ሌላ ሴት እንዳለው ነግሮሻል ? » ሲሉ ጥያቄአቸውን በማመንታት ሰነዘሩ ፡፡

የሕሊና ዓይኖች ፈጠጡ ፡፡ የወ/ሮ በላይነሽ ጥያቄ ከእንቅልፏ እንዳባነናት ዓይነት « ምን አሉ እማማ ? » ብላ ጮኸች ፡፡



« ምነው እንግዳ ሆንሽ ? » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ በመጠራጠር፡፡

« አውርቶልሽ አያውቅም ማለት ነው ? ማን ነበር ያሉኝ እቴ? » ፊታቸውን ዞር ዞር አድርገው ለማስታወስ ሞከሩ ፡፡

« እማማ ማን ነገረዎት ? » ስትል በኃይል ተነፈሰች ፡፡

« ኸረግ ኸረግ ሁሉ የሚያወራውን ? እኔ እኮ እንዲህ ሞኝ አትመስይኝም ፡፡ ግና ምን ያደርጋል ጆሮ ለባለቤቱ ባዕድ ነው ይባል የለ » አሉ ፡፡

ለሕሊና የወ/ሮ በላይነሽ አባባል በሁለንተናው ብዙ እንቆቅልሾችን የሚፈታ በመሆኑ ብዙ ጥያቄ አልጠየቀችም ፡፡ በውስጧ ትርጉም ልትሰጠው የማትችለው አንዳች ስሜት ተሰማት ፡፡ ከተቀመጠችበት በመነሳት ተንደርድራ መኝታ ቤቷ ገብታ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች፡፡

« እኔ አፈር ልብላ ! አፈር ልብላ ! ምን አደረኩ ? » አሉ ወ/ሮ በላይነሽ በድርጊታቸው ተፀፅተው ፡፡ ወደ ሕሊና መኝታ ቤት ፈጠን ብለው ገቡ ፡፡ ወ/ሮ በላይነሽ ቀደም ሲል የተናገሩትን በመሻረር ሕሊናን ለማጽናናት ሞከሩ ፡፡ « ሲሉ ሰማሁ እንጂ መች አረጋገጥኩ? አሉባልታ ነው ፡፡ በቅናት ሰዎች የሚያስወሩት ሊሆን ይችላል » በማለት ዘላበዱ ፡፡ ነገር ግን ሕሊናን ከማልቀስ ሊያግዷት አልቻሉም፡፡

« ቀድሞውኑ አውቄአለሁ እርሶም የጠረጠርኩትን ነው ያረጋገጡልኝ » በማለት አምርራ አዘነች ፡፡

« ኸረ ጎረቤት ምን ይላል ? በይ ዝም በይ » ዓይናቸውን በነጠላቸው ጫፍ እየጠራረጉ በማፅናናት መልክ የሕሊናን ፀጉር አሻሹ፡፡ የወ/ሮ በላይነሽ ቁልፍ ቃል የሕሊናን ለቅሶ ለጊዜው ገታው፡፡ በቤቱ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ ፡፡ « በይ ተነሽ ፊትሽን ታጠቢ ፡፡ ይልቁንስ ነቃ በይና ቡናችንን እንጠጣ ፡፡ በመባቻ ያለቀሰ እስከ

ባለእግዝአብሄር አይፈታም ይባላል ፤ ይቅር ያብልሽ ። » አሉ አመስካከታቸውን ወደ ሰማይ ፤ እጆቻቸውን ወደ ፊት ለፊት አጣፍተው እምላክን በመለመን መልክ ።

ሒሊና ከተጋደመችበት ከወ/ሮ በላይነሽ ጭን ላይ በረጅሙ ተንፍሳ ተነሳች ። በእጆቿ ዓይኖቿን ጠራርጋ ወ/ሮ በላይነሽን በመተከዝ መልክ አትኩራ ተመለከተች ። ፊቷን ታጥባ ነቃ ነቃ በማለት ዱካዋ ላይ ተቀምጣ ቡና መጠጣት ጀመረች ።

ወ/ሮ በላይነሽ አቦል ቡና ከመቀዳቱ በፊት የቀረበውን የእንጀራ ቡና ቁርስ በፀሎት አስቀድመው ቆረሱ ። « በል እስቲ አንተ ታውቃለህ ። ለምትለውና ለምትሰራው መቼም ምክንያት አለህ ። ከአንተ የሚሰወር ምን አለ ? » በማለት በሚቀዱት ቡና ጣልቃ ወደ ሠማይ እያንጋጠጡ እምላክን ተማፀኑ ።

« መቼም እማማ በላይነሽ የእግዜር መላክተኞች በምድር ላይ አሉ ቢባል እርስዎ አንዷ ነዎት እል ነበር ። በዛሬው ቀን የነገሩኝ መልዕክት ከምንጊዜውም የበለጠ ነፍስ አድን ነው ። በወቅቱ የመጣ መልዕክት ነው እግዚአብሄር ይስጥልኝ ። ሌላ ምን እላለሁ ። » አለች ሒሊና ወ/ሮ በላይነሽን በትኩረት እያየች ።

« ምን አደረግኩ ? አሳዘንኩሽ ልጄን በማያገባኝና በማላውቀው ነገር ገብቼ ይቅር በይኝ » አሉና ቡናቸውን ፉት ብለው አጣጣሙ።

« ለዓመታት ሲያስጨንቀኝ የነበረውን በሽታ ነው ምህረቱን የሰጡኝ ። ለዓመታት ትልቅ እንቆቅልሽ ሆኖብኝ ብመከር ፤ ብዘክር፤ መልስ ላገኝለት ያልቻልኩትን ጥያቄ እርስዎ ከመቅፅበት ፈቱት ።

እማማ የዛሬው የእኔ ለቅሶ በብዛት የደስታ በጥቂቱ የሀዘን ስሜት ነው ። የተደለትኩት ከገባሁበት አዘቅት እራሴን ነፃ ለማድረግ መቻሌ ነው ። ያመንኩትና የወደድኩት ሰው የማይታመን ፤ የማይወደድ መሆኑን ሳውቅ ምን ያህል ሞኝና ተላላ እንደነበርኩ ተገንዘብኩ ። አብሬው ያሳለፍኳቸውን ጊዜያቶች ስገመግም አዘንኩ ።



በህይወቴ ውስጥ እንደ አንድ ትልቅ ትምህርት ነው የምቆጥረው ። » በማለት ጎንበስ ብላ የወ/ሮ በላይነሽን ሁለት እጆች በእጆቿ ያዘች ።

« እማማ ! ነፍሴ ስትጨነቅ ምህረት ያመጡላት እርስዎ ነዎት ። ውለታዎን ምን ጊዜም ልከፍለው አልችልም ። እግዚአብሄር ይክፈልዎ ። » በማለት ጉንጮቻቸውን አገላብጣ ሳመቻቸው ።

« ልጄ ! ምን አደረኩልሽ ? አንቺ ነሽ እንጂ የተባረክሽ ከልብስ ልብስ አልቀረ ፤ በየጊዜው ገንዘብ ሳይቀር ምንም ሳይጎድልብኝ በአንቺ ሥም እኮ ነው የምኖረው » በማለት ወ/ሮ በላይነሽ በተራቸው ጉንጮቿን አገላብጠው ሳሙ ።